# ይኸውና መልሴ!

**ሙስሊም ጸሐፊያን ከ10 በላይ በሚሆኑ መጻሕፍታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ላነሡዋቸው ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ**

*አሁንም ደግመን ደጋግመን ስለ ሁለቱ ትንቢቶች ማለትም ኢሳይያስ 40 እና 60ን በተመለከተ ክርስቲያኖችን በጥሞና የምንጠይቀው ትንቢቶቹ ተፈጽመዋልን? ከተፈጸሙ ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንጻር ሲታይ ምን ጠቀሜታ አላቸው? አፈጻጸማቸው ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንጻር ሲታይ ምን ያህል በአምልኮ ሥርዓት ውስጥ እየተሠራባቸው ነው? የማይሠራባቸው ከሆነ ለምን?*

ዳንኤል ተሾመ 2002 የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው። ለማንኛውም ማጣቀሻነትና ለምርምር ሥራ ከሚወሰዱ አጫጭር ጥቅሶች ውጭ የዚህን መጽሐፍ የትኛውንም ክፍል በምንም መልኩ መውሰድና ማባዛት የተከለከለ ነው። *ጽሑፍ አርማትና አርትኦት፡-*

**በዳንኤል ተሾመ**

2002 የመጀመሪያ እትም

danielshlom@yahoo.com

**በሥነ አፈታት ጥበብ የዐቃቤ እምነት ተግባርን በቀላሉ ማከናወንን ይማሩ!**

**Hermeneutics-2 & Apologetics-1**

**1st edition 2009-2010**

# ምስጋና

እግዚአብሔር ሰው የሚያስነሳው ከቤተሰብ ነው። ቤተሰብ እግዚአብሔር ለሚያስነሣው ሰው አውድማ ነው። ስለዚህ፣ በቅድሚያ የተገኘሁበትን ቤተሰብ (መላው የቤተሰቦቼ አባላትን) ላመሰግን እወድዳለሁ።

ከመንፈሳዊው ቤተሰቤ ደግሞ በጌታ ታላቅ ወንድሜ የሆነውን፣ በድካምም በብርታትም፣ በማጣትም በማግኘትም ከጎኔ የሆነውንና በአገልግሎቱና በሥነ ጽሑፍ ሥራዬ የላቀ እገዛና ድርሻ ያለውን ሳሙኤል ኃይሉን፣ እንዲሁም ባለቤቱ ሕይወት ኃይለ ማርያምን፣ ደግሞም ጸሎታቸው መሰማት ብቻ ሳይሆን ፈጣን ምላሽ እንደሚያስገኝላቸው ቀምሼ ያየሁላቸውን፣ ባላቸው ነገርም ሁሉ ያገለገሉኝን አልቃሽ ሴቶችን በእራሴና በአንባቢያን ሁሉ ስም ላመሰግን አወድዳለሁ።

ወንድሜ ሮቤል ተስፋዬን እና ዳንኤል ቱራትን ዘወትር ስለሚያደርጉልኝ ድጋፍ ላመሰግን እወዳለሁ።

# መታሰቢያ

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነት በቅድሚያ በነገር ሁሉ ከጎኔ ለተሰለፈችው እና ከግምት በላይ የሆነ ዋጋን ዘወትር ለምትከፍለው ለውዷ ባለቤቴ ለወ/ሮ አክበረት አብርሃም (ሻሎም) ይሁንልኝ።

በመቀጠልም፣ ቅንነት እና ትጋት፣ ሠርቶ ማሠራት እና አገልግሎ እንዲያገለግሉ ማድረግ፣ እንዲሁም ለመልካም ሥራ ተነሥቶ ማነሣሣትን ከጌታ ዘንድ ለታደለው፣ ለተወደደው ወንድሜ ለሺፈራሁ ሰይድ ይሁንልኝ።

# መቅድም

የጽሑፉ ሂደት በአጠቃላይ ከ1500 ዓ.ዓ እስከ 100 ዓ.ም ጊዜን በመውሰድ ከ1900 ዓመታት በፊት ሁሉም ክፍሉ ተጽፎ የተጠናቀቀ መጽሐፍ እንደ መሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለዛሬዎቹ አንባቢያን መረዳት በመጠኑም ቢሆን አስቸጋሪ መሆኑ እንግዳ ነገር ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

በእነዚያ ዘመናት ከነበሩ ሰዎች ጋር ያለ ይህ ሰፊ የዘመናት ልዩነት፣ ከባህልና ከንጽረተ ዓለም እንዲሁም ከቴክኖሎጂ፣ ከሥልጣኔ ደግሞም ከአጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎች መለያየት የተነሣ ለዛሬው ዘመን አንባቢያን አንብቦ መረዳትን አስቸጋሪ ማድረጉ አልቀረም።

በዚህ ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው የሥነ አፈታት የሙያ ዘርፍ ነው። ሥነ አፈታትን በትክክል ከተረዳነውና በአግባቡም ከተጠቀምንበት በዐቃቤ እምነት ተግባራችን ውስጥ የሚጫወተው ልዩ ሚና ዕለት ዕለት በማጣጣም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚነሡ ጥያቄዎችን በበቂም ሆነ አርኪ በሆነ መልኩ መመለስ እንችላለን።

ሙስሊም ጸሐፊያንም ሆኑ ሌሎች ወገኖች የሚያነሡዋቸው ጥያቄዎች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከሥነ አፈታት ጋር የሚገናኙ በመሆናቸው ይህን መጽሐፍ በዚህ መልኩ ለማዘጋጀት ጥረት አድርጌአለሁ። ጌታ ጥናታችሁን ወይም ንባባችሁን ይባርክላችሁ!

## ማውጫ


I. ሙስሊሞች በአጠቃላይ፣ ሙስሊም ጸሐፊያን በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብቡ የሚገጥሙዋቸው ችግሮች፦ የሚፈጠሩባቸው ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የሚገጥማቸው ግራ መጋባት መንስኤ....6

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መንገድና ሂደት ለመረዳት አለመቻልና አለመሞከር (አለመቻል፦ ባለማወቅ፣ አለመሞከር- ባለመፈለግ)....6

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት መንገድና የጽሑፉ ሂደት....6

1. የተጻፈበት መንገድ....6
2. የተጻፈበት ሂደት....14
   - ትውስታዎች (Memories)....14
   - በሰብሳቢያን አማካይነት የተሰበሰቡ ትምህርቶች (Collectors)....16
   - ታሪኮች (Ministrels)....19
   - በተከታዮች የተጠበቁ ትምህርቶች (Disciples)....20
   - መልእክት አሠራጮች መልእክቱን ያደረሱበት ሁኔታ (Transmiters)....20
   - መልእክቱ ወደ መላው ዓለም የደረሰበት ሁኔታ (Translation and Transmission)....21

ለ. የሥነ አፈታት እውቀት ማጣት፣ ለማወቅም ሆነ በዚህ ለመጠቀም ደንታ ቢስ መሆን (Lack of Hermeneutical Knowledge)....22

የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችና የትርጉም ዘዴዎች....22

የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች........................22

1. ትረካዊ አጻጻፍ..........................23
   - ትረካዊ አጻጻፍን በተመለከተ ልብ ልንላቸው የሚገቡ መመሪያዎች..25
   - ታሪካዊ መጻሕፍትን ስናነብብ ልንወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች..........................26
2. ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ..........................27
3. ትምህርታዊ አጻጻፍ..........................29
4. አቡቀለብሲሳዊ (ራእያዊና ሕልማዊነት የተላበሰ) አጻጻፍ..........................30
5. ፍልስፍናዊ አጻጻፍ..........................32
6. ትንቢታዊ አጻጻፍ..........................35
   - የንስሐ ጥሪ..........................35
   - ወደ እግዚአብሔር አሳብ የሚመልስ ጥሪ..........................35
   - የተስፋ ቃል..........................36
   - ልዩ ልዩ መረጃዎችና ትምህርቶች......36
7. ስብከታዊ አጻጻፍ..........................37
8. የድንቅና የተአምራት ዘገባዎች (ሰላምታ እና ስንብቻ)..........................38

የትርጉም ዘዴዎች..........................39
1. ቀጥተኛ (Literal)-(Historical, Grammatical and Literary) (HGL).......39
2. ሥዕላዊ (Figurative)..........................40
3. ውስጠ ወይራዊ (Allegorical)..................40
4. ሰምና ወርቅ (Wax and Gold)..................41
5. ጥላና ምሳሌያዊ (Shadow and Copy)..41
6. ታይፖሎጂ (Typology)..........................42
7. መንፈሳዊ (Spiritual) ..........................43
8. ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ (Historical, Gramatical and Literary) (HGL) ..........................43
9. ዐውደ ንባብን ማዕከል ያደረገ አተረጓጐም (Context) ..........................44
10. ምጸታዊ አተረጓጐም (Irony)..................45

የትርጉም ቅኝቶች..........................46
1. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ እውነት..46
2. የእግዚአብሔር ዓላማ..................47
3. የድነት (የደኅንነት) መንገድ..........47
4. ልዩ ልዩ ገዥ የሆኑ መመሪያዎች..47
5. የወንጌሉ ምሥጢር (ዳግም ልደት)..48

ሐ. ወደ ክርስትና እምነትም ሆነ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጨለምተኛ አስተሳሰብን ይዞ መምጣት (Pessimistic Approach)..........................49
መ. መጽሐፍ ቅዱስን በቁርኣን እይታና መስፈርትነት ለመመልከትና ለመገምገም መሞከር..........................49
ሠ. ስትቶች የሚነሡ ሙስሊም ጸሐፊያን ስሜታዊነትንና ወገንተኝነት በውስጣቸው መያዛቸው፣ ይህንንም ልብ አለማለታቸው......51

II. ሙስሊም ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብቡ የሚያነሡዋቸው ጥያቄዎችና የሚቸገሩባቸው ጉዳዮች..........................60

ሀ. የሥላሴ ትምህርት..........................60
ለ. የክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች......62
ሐ. ሊቀበሉዋቸው የሚከብዱ እውነታዎች..........................66
- ተአምራት..........................66
- ታሪካዊ ክንዋኔዎች..............67
- ለዚህ የተሰጠ መልስ...........67
መ. የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በቁርኣን መልእክት መስፈርትነት ለመመዘን መሞከር..........................72
- ለዚህ የተሰጠ መልስ..........................74
ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጋጩ ነገሮች እንዳሉ መቍጠር..........................81
- የአሳብና የአሃዛት ግጭቶች እንዲሁም የስም ግጭት.........81
- ለዚህ የተሰጠ መልስ............82
ረ. የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ቆንጽሎ መውሰድ..........................85
- ለዚህ የተሰጠ መልስ..........88

III. ስለ ሙስሊም ጸሐፊያን ማወቅ የሚገባን መሠረታውያን ጉዳዮች....................................92

ሀ. የእስልምና እምነት ብዙ ነገሮችን ከአይሁድና ከክርስትና እምነት የመውሰዱ ሁኔታ፣..............................................92

ለ. ቁርዓን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ አይሁድ እምነትና ስለ ክርስትና እምነት ትክክለኛነት መመስከሩ፣..................................................93

ሐ. ሙስሊም ጸሐፊያን ከታላቁ ነቢያቸው ይልቅ ያወቁ ይመስል የአይሁድ እምነትንና የክርስትና እምነትን ብሎም መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተሳሳተ ወይም ብዙ ስሕተት እንዳለበት መቍጠራቸው፣...........................................94

መ. ሙስሊሞች ቁርዓንን እንደ ፍጹም እውነት በመውሰድ እስልምናን፣ የአይሁድ እምነትም ሆነ የክርስትና እምነት ማረሚያ (Correction) አድርገው መመልከታቸው፣..............................94

ሠ. ለክፍል ሦስት የተሰጠ መልስ................95

IV. ሙስሊም ጸሐፊያን ልብ የማይሉዋቸው ወይም ልብ ሲሏቸው የማይወዱ ጉዳዮች......................................98

ሀ.ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ክፍል እንደ እውነት በመውሰድ የቁርዓንን /የእስልምናን/ አስተምህሮ በማስረጃ ለማስረገጥ እየጠቀሱ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደ ተበረዘ አድርጎ ማሰብ - እእነዚህ ሁለት አኪያሄዶች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ተግባራት መሆናቸውን ልብ አለማለት፣...........98

ለ. መጽሐፍ ቅዱስን በቁርዓን እይታ ለመመልከት መሞከራቸው የዋህነት መሆኑ፣..................................................99

V. ሙስሊም ጸሐፊያን የሚያነሡዋቸው ተጨማሪ ጥያቄዎችና ለዚህ የተሰጠ መልስ..........................................................100
- ጥያቄዎች...........................100
- መልስ...............................109

**I. ሙስሊሞች በአጠቃላይ፣ ሙስሊም ጸሐፊያን በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብቡ የሚገጥሙዋቸው ችግሮች፦ የሚፈጠሩባቸው ጥያቄዎችና ግራ መጋባት መንስኤ**

በክርስቲያን - ሙስሊም ውይይቶችም ሆነ ሙስሊም ጸሐፊያን በሚጽፉዋቸው መጻሕፍቶች ውስጥ በግልጥ የሚታይ ግራ መጋባት እንዲሁም በአእምሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ጥያቄዎች አሉ:: እነዚህም ሙስሊም የሆኑ ምእመናንም ሆነ ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነብቡበት ጊዜ የሚፈጠሩባቸው ጥያቄዎችና ግራ መጋባት ናቸው::

ለመሆኑ ለግራ መጋባቱም ሆነ፣ በብዙ ዓይነት ጥያቄዎች ለመሞላት መነሻ የሆኑ ወይም መንስኤ የሆኑ ነገሮች ምንድን ናቸው? ብለን የጠየቅን እንደሆነ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች በምላሽነት ማግኘትም ሆነ መመልከት እንችላለን::

**ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መንገድና ሂደት ለመረዳት አለመቻልና አለመሞከር (አለመቻል፦ ባለማወቅ፣ - እንዲሁም አለመሞከር ፦ ባለመፈለግ)**

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት የራሱ የሆነ መንገድም ሆነ ሂደቶች አሉት:: የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በተሳሳተ መልኩ ሳይጠመዘዝ፣ በመሰለኝ ሳይተረጎም፣ በቅጡና በትክክል ለመረዳት የተጻፈበትን መንገድና ሂደት በተገቢው ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል::

**መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት መንገድና የጽሑፉ ሂደት**

**1. የተጻፈበት መንገድ**

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትና ወደ አሁኑ ትውልድ የተላለፈበት መንገድ በጣም ቀላል ያልሆነና ብዙ ደረጃዎችን ያለፈ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል:: መጽሐፉ ስለ ተጻፈበት መንገድ ለመነጋገር በቅድሚያ የመገለጥን አመጣጥ መመልከት ይኖርብናል::

ለረጅም ዘመን ተደብቆ ሳይገለጥ የኖረ ነገር ሲገለጥ፣ በሰዎችም ዘንድ መታየት ሲችል፣ መገለጥ ተገኘ



ይባላል:: ወይም ይህ ነገር አሊያም ያ ጉዳይ ተገለጠ ይባላል:: እግዚአብሔር አምላክ ሰዎች እንዲያውቁት ባሕርይውን፣ ማንነቱንና ዓላማውን ሲያስታውቃቸው፣ እግዚአብሔር እራሱን ገለጠላቸው ይባላል:: እግዚአብሔር፣ ብዙውን ጊዜ እራሱን የሚገልጠው በእርሱ ከመታመንና እርሱን ከመታዘዝ አኳያ ነው::

እግዚአብሔር አምላክ፣ በዘመናት መካከል ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድና ሁኔታ ውስጥ ሳሉ፣ እራሱን ይገልጥላቸዋል:: በዚህ በመገለጡ ውስጥ ሁለት መሠረታውያን ነገሮች አሉ:: የመጀመሪያው፣ በእርሱ ያምኑ ዘንድ ወደ እምነት የሚጠራ መልእክት ሲሆን፣ ተከታዩ ደግሞ ስገለጠላቸው እውነት እንዲኖሩ ወይም በሌላ አባባል ቃል ኪዳኑን እንዲጠብቁ የሚያስታውቅ መልእክት ነው:: እነዚህ ሁለቱ የመገለጥ መሠረታውያን ሥራዎች ወይም ዓላማዎች ናቸው:: ይህም እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ፣ የመገለጡ እውነታዎችና ዓላማዎች እግዚአብሔርም የሚያደርጋቸው ድርጊቶች ሁሉ በአንድ ላይ የሕዝቡን አኗኗርና ባህል አጠቃላይ ሁኔታ ይሰውጠዋል:: መገለጡም ታሪካቸውና የሕልውናቸውም ክፍል ይሆናል::[1]

እግዚአብሔር አምላክ ሥራውን በመገለጥ ጀምሮታል:: ሕዝቡም መገለጡን ተቀብለው በአዲስ አስተሳሰብና መረዳት ውስጥ ገብተው በተገለጠላቸው እውነት ውስጥ መኖር ጀምረዋል:: ያገኙት መገለጥም ስለ ሁሉም ነገር ያላቸውን መረዳት ቀይሮታል:: በተለወጠ ማንነት ውስጥ ይመላለሳሉ:: ባህላቸውና የዕለት ተዕለት ልምምዳቸው ሁሉ ባገኙት መገለጥ አማካይነት ተቃኝቷል:: በዚያም መገለጥ ውስጥ ሲመላለሱ ሰዎች ናቸውና ከመገለጡ ጋር ያላቸው ግንኙነት አንዳንዴ አሉታዊነት፣ ሌላም ጊዜ አዎንታዊነት ይታይበታል:: መገለጡ በታሪካቸው ውስጥ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ነጥብ ጥሎ ያልፋል::[2]

---

[1] ዳንኤል ተሾመ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ዘዴዎች Hermeneutics 1፣ አዲስ አበባ፣ 1998:: ገጽ 18-19::

[2] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 19::

የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሲመላለሱ የተሰጣቸው መገለጥ መገለጡን ከተቀበሉ በኋላ በተገለጠላቸው እውነት በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ የኖሩበት ኑሮ፣ ታሪካቸው፣ ለእነርሱ ቀጣይ ሕይወት ማስተማሪያነትም ሆነ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ ሲፈለግ ለሁሉ የሕይወት መመሪያ እንዲሆን እግዚአብሔር በመረጣቸው ሰዎች በኩል በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነትና አነሣሺነት ቅዱሳት መጻሕፍት መጻፍ ይጀመራሉ። ወደ ጽሑፉ ሂደት ከማለፋችን በፊት የእግዚአብሔር መገለጥ በተለያዩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤትን ማስከተሉ በጽሑፉ ውስጥ የመካተቱን አስፈላጊነት ልናሰምርበት ያስፈልጋል። አትግደል! አታመንዝር!...ወዘተ የተባሉ ትእዛዛት መሰጠታቸው እሙን ነው። እነዚህ ትእዛዛት የመገለጡ ክፍሎች ናቸው። እነዚህን ትእዛዛት የፈጸሙ ደግሞም የጣሱ ሰዎችን ሕይወት፣ በመታዘዛቸው ምክንያት የገጠማቸውን በረከትና ባለመታዘዛቸው ምክንያት የገጠማቸውን ውድቀትና ቅጣት ሁሉ በምሳሌነት የጽሑፉ ሂደት አካቷቸዋል። ይህም፣ መጽሐፉን የተሟላና እምነት የሚጣልበት፣ እንዲሁም ተግባራዊ እንጂ፣ ንድፈ አሳባዊ ያልሆነ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ነው። ሆኖም፣ ሙስሊም ጸሐፊያን፣ አለመታዘዝና ኃጢአት እንዴት እንደ ዳዊት ባሉ ነቢያቶች ሕይወት ሊገኝ ቻለ? ሲሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ለማጣጣል ይሞክራሉ። የእግዚአብሔር ነቢያት፣ ሰው እንደ መሆናቸው መጠን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሊሳሳቱ፣ ከስሕተታቸውም ተምረው ሊመለሱ የሚችሉ መሆናቸውን ይዘነጋሉ።[3] ፍጹም የሆነ ሰው ከቶ አለመኖሩን ይረሳሉ። ምናልባት፣ ለእንደዚህ ዓይነቱ ግራ መጋባት የሚዳርጋቸው ይህ ሊሆን ይችላል። ቁርዓን የያዘውን ወይም ይገኛዋል ብሎ የሚለውን መገለጥ ነው የሚያስተላለፈው። ከዚህ አለፍ ብሎ በሰዎቹ

[3] ፖል ኢ. ሊትል የተባሉ ጸሐፊ "እግዚአብሔር በብዙ መንገዶች እራሱን ገልጦአል ይላሉ። ሲዘረዝሩትም፦ በፍጥረት ሥራው በታሪክ ውስጥ በተለይም ከእስራኤልና በዙሪያዋ ካሉ ሕዝቦች ጋር ባደረጋቸሁ ግንኙነቶች ውስጥ በሠራቸው ታላላቅ ሥራዎችና ክስተቶች እንዲሁም በነቢያት ስብከቶችና ትንቢታዊ መልእክቶች በኩል የተገለጠ ሲሆን፣ ሙሉ የሆነውን መገለጡን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በኩል ሰጥቶናል ይላሉ።" Paul E. Little, *Know What You Beleve*, USA: Victor Books, 1970, p. 8.



ሕይወት ውስጥ መገለጡ ያመጣው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ታሪክ፣ የተለያዩ ሰዎችን ክህሎቶችና አጠቃላይ ሁኔታዎችን አያስቃኝንም። ለዚህም መሠረታዊው ምክንያት ቁርዓን በአንድ ሰው ጥቂት የሕይወት ዘመን (610-620ዓ.ም) ውስጥ የመጣ መገለጥን የያዘ በመሆኑ ነው።

በመቀጠልም፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉበትን መንገድ ወይም ሁኔታ እንመለከታለን። አስቀድሜ እንዳልኩት እግዚአብሔር ለሕዝቡ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ራሱን ይገልጣል። መገለጡ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ አዲስ አስተሳሰብን፣ አዲስ የኑሮ መመሪያ፣ ዓላማንና አቋምን ያመጣል። ይህ መገለጥ የሕዝቡ መተዳደሪያ ደንብ፣ የታሪካቸው፣ የባህላቸውና የእምነታቸው እንዲሁም የማንነታቸው (Identity) ክፍል ይሆናል። በሕይወታቸው፣ በኑሮአቸውና በአገልግሎታቸው ውስጥም በሰጡት ስፍራ መጠን «መገለጡ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤቶችን ያመጣል።»[4] አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ታሪክን በመካከላቸው ይሠራል። በዚህም ለመልካም, ነገር፣ ማለትም ለመታዘዝ፣ በጎ ተግባራትን ለመፈጸም፣ እንዲሁም ላለመታዘዝ፣ ለዕብሪተኝነት፣ ላለማመንም ሆነ ለውድቀት ምሳሌ ሲሆኑ የሚችሉ ሰዎች ይገኛሉ።

ይህ ሁሉ ተሰብስቦ ለመጭውም ሆነ በዚያን ወቅት ላለው ትውልድ ማስተማሪያ እንዲሆን በእግዚአብሔር ሲታሰብ፣ እርሱ በመረጣቸው ሰዎች በኩል፣ በመንፈሱ ቁጥጥርና አነሣሺነት እንዲጻፍ ያደርገዋል። ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉበት መንገድ አንድ ነው። ይህም በግሪኩ 'ቲዎስኒኘቶስ' የሚሰኝ ሲሆን፣ ትርጓሜውም፦ «እስትንፋስ-እግዚአብሔር» ማለት ነው።

መሠረታዊ አሳቡም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በእግዚአብሔር መንፈስ አነሣሺነት፣ መልእክት ሰጪነት እንዲሁም የበላይ ተቆጣጣሪነት ነው፤ የሚል ነው። ለጽሑፉ ሰዎችን ይመርጣል፤ በመንፈሱ የበላይ ቁጥጥር ውስጥ ያስገባቸዋል፤ መልእክቱን ይሰጣቸዋል።

[4] ዳንኤል ተሾመ፣ *ስለ መጽሐፍ ቅዱስ* 19።

መጻፍ ያለባቸውን ሁሉ እንዲጽፉ ያነሣሣቸዋል:: ኃይልም ይሰጣቸዋል:: የጽሑፉንም ሂደት ከመነሻው እስከ ፍጻሜው ድረስ እየተቆጣጠረ ያጽፋል፤ በሚጽፉ ጊዜም ከመልእክቱ ጭብጥ እንዳይወጡ ድረስ በራሳቸው የቋንቋ ችሎታ፣ የሥነ-ጽሑፍ ብቃት፣ ባላቸው ታሪካዊም ሆነ ባህላዊ ግንዛቤና መረጃ መሠረት እንዲጽፉ ይፈቅድላቸዋል::[5]

ስለዚህም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ደራሲያን ሊኖሩት ችለዋል:: አንደኛው ደራሲ፣ እራሱ እግዚአብሔር ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው:: የእርሱ ሥራ መልእክቱን መስጠትና ከመልእክቱ እንዳይወጡ ማድረግ ነው:: ሁለተኛው ደራሲ፣ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው:: የእነርሱ ተግባር መልእክቱን በተመቻቸው የሥነ ጽሑፍ ዓይነት፣ ለምሳሌም በታሪክ፣ በግጥም፣ በዝማሬ፣ በምሳሌዎች... ወዘተ ማስተላለፍ ነው::

የእግዚአብሔር መንፈስ ፍጹም ስለሆነና በጊዜና በቦታ የማይወሰን ስለሆነ፣ ማለፊያ የሆነና እንከን አልባ የሆነን መልእክት ያስተላልፋል:: ስለዚህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከመልእክቱ አንጻር ፍጹምና ሙሉ በሙሉ እምነት የሚጣልበት መጽሐፍ ነው:: እንከንም ሆነ ስሕተት ከቶ አይገኝበትም:: እግዚአብሔር የሥልጣን ቃል ነው:: ዘላለማዊም ሆነ የማይለወጥ ደግሞም የማይሻር ቃል ነው::

በአንጻሩ ደግሞ ቅዱሳን ሰዎች በጊዜና በቦታ ውሱን ስለሆኑ፣ ሁሉንም ዓይነት እውቀት ለምሳሌም መልክዓ ምድራዊ፣ ሥነ ቋንቋዊ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ ልዩ ልዩ መረጃዎች...ወዘተ ስለማያውቁ (በከፊል ካልሆነ በቀር) በሥነ ጽሑፋቸው ውስጥ እንደ መረጃ ስሕተት፣ የጊዜ አቈጣጠር መዛባት፣ እንደ ታሪካዊ ቅንብር ያለ ጕድለት ሊኖር ግድ ነው::[6]

---

[5] እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍቱን ቃል በቃል እየተናገረ አላጻፋቸውም:: ነገር ግን፣ ጸሐፊዎቹ የእራሳቸው ስብእናና ያላቸውን መረጃ እንዲሁም የአጻጻፍ ችሎታ ወዘተ...ተጠቅመው የተሰጣቸው መልእክት እንዲያስተላልፉ መርቶአቸዋል፤ ተቆጣጥሮማቸዋል:: Paul E. Little, *Know What You Beleve.* USA: Victor Books, 1970, p. 14.

[6] *ዳንኤል ተሾመ! ስለ መጽሐፍ ቅዱስ...!* አዲስ አበባ፣ 1998፣ ገጽ 6:: በተጨማሪም Charles, C. Ryire *የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ትምህርት*



ልዩ ልዩ አሃዛዊ መግለጫዎች፣ ጸሐፊዎቹ ባላቸው መረጃ ልዩነት ምክንያት ተዛንፈው ሊቀርቡ ይችላሉ:: ዓቢይ የሆነው ጉዳይ ክስተቱ እንጂ፣ ቊጥሩ አይደለም:: ለምሳሌ ከወንጌል ጸሐፊያን አንዱ ጌታ ኢየሱስ ሁለት ዕውሮችን በአንድ ስፍራ ላይ እንደ ፈወሰ ሲጽፍ፣ ሌላው ደግሞ በተመሳሳይ ስፍራ ላይ አንድ ዕውር እንደ ፈወሰ ሊዘግብ ይችላል:: እንደዚህ ዓይነት አሃዛዊ ስሕተቶች ከምድራውያን ጸሐፊዎች፣ በጊዜና በቦታ እንዲሁም ከመረጃው ስሕተት ሊመጣ የሚችል ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠበቅም ጉዳይ ነው:: ዋናውና መሠረታዊው መልእክት፣ ጌታ ኢየሱስ ከሰው ችሎታ በላይ ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ ነበረው፣ ደግሞም በሰው ልጆች ተግዳሮትና እንቆቅልሽ ሁሉ ላይ በመለኮታዊነቱና በጌትነቱ ይገዛ ነበር የሚለው ነው::

ስለ ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን ስናስብ ልንመለከታቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ:: በቅድሚያም ስለ መልእክት አምጪው ወይም ስለ መልእክቱ ባለቤት ስለ ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንመልከት::

የእግዚአብሔር መንፈስ ትኩረት የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ላይ እንደሆነ አውስተናል:: ከዚህ አጠቃላይ መልእክት ውስጥ ደግሞ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ማዕከላዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ላይ እንደሚያተኩር መረዳት ይኖርብናል:: ጌታ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ምስክር መሆኑና በመምጣቱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚያከብርም በማያሻማ መልኩ በወንጌላውያኑ ትምህርት (በአራቱ ወንጌላት) ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል::

እዚህ ላይ አንድ በተጨማሪ ልብ ሊባል የሚገባ እውነትም አለ:: ይህም የጌታ መንፈስ ቅዱስ ልዩ ትኩረት፣ ለእኛም ልዩ ትኩረት እንደሚሆን ወይም

---

ጥናት፣ተርጓሚ ሲሳይ ደሳለኝ፣ አዲስ አበባ ላብሲሲ ብሩክ ፋውንዴሽን፣ 1987:: ገጽ 41:: ዳግሞም ዛሬ እእንደምናየው በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ችግር እልነበረም ብለን ሙሉ በሙሉ አንክድም::

ሊሆን የተገባ የመሆኑ እውነታና አስተሳሰባችንን ጨምሮ የትርጉም አቀጣጫችንን ሁሉ (Hermeneutics) የሚቀይር ወይም ቅርጽ የሚያሲዝ መሆኑ ነው:: ለዚህም ነው በአጠቃላይ አነጋገር የፕ ሮቴስታንቱ ዓለም ሥነ አፈታት (Hermeneutics) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መልእክቶችን በክርስቶስ ብርሃን (In the light of Jesus Christ) ወደ መመልከቱ የሚያዘነብለው::[7]

በመቀጠልም፣ የተቀበሉትን መልእክት በጽሑፍ ስላሰፈሩት ምድራውያን ሰዎች ስለሆኑ ጸሐፊያን (ደራሲያን)፣ እንመለከታለን:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚጽፉበት ጊዜ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን መጠቀማቸውን ማጤን ይኖርብናል:: ከእነዚህም መካከል ትረካዊ አጻጻፍ (Narration)፣ ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ (Poetic)፣ ትምህርታዊ አጻጻፍ (Didactic)፣ እንዲሁም ራእይንና ሕልምን ማዕከል ያደረገ አጻጻፍ (Apocalyptic) ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ትረካዊ አጻጻፍ፣ ትረካዊ ሥልተ-አጻጻፍን፣ ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ፣ ሥነ ግጥማዊ ሥልተ አጻጻፍን፣ ትምህርታዊ አጻጻፍ፣ ትምህርታዊ ሥልተ አጻጻፍን...ወዘተ ተከትሎ ነው የሚጓዘው::[8]

በመቀጠልም፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጸሐፊዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ልብ ማለት ያስፈልጋል::[9] ጠቅለል ባለ መልኩ የቋንቋ አጠቃቀማቸው የሚከተለውን ይመስላል:: የመጀመሪያው የቋንቋ አጠቃቀም፣ ብዙሃኑን ማዕከል ያደረገ ነው:: ይህም የሰው ልጆች ሁሉ

[7] ክርስቶስን ማዕከላዊ እውነት ባደረገ መልኩ የሚደረግ ሥነ መለኮታዊ አስተምህሮን ማበጀትን ይመለከታል::

[8] -*Zondervan hand book to the Bible*, P. 22, 51- መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ የአጻጻፍ መንገድ ወይም ዘዴ የተጻፈ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: ከእነዚህም መካከል ታሪክ፣ ጸሎት፣ የፍቅር ግጥሞች ምሳሌዎችና ትንቢቶች የሐዋርያት ተግባራትና ደብዳቤዎች...ወዘተ ይገኙበታል:: በዚህ ጉዳይ ላይ በመጠኑ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ዳንኤል ተሾመ፣ *ስለ መጽሐፍ ቅዱስ...የሚለውን መጽሐፍ ያንብቡ::*

[9] *Christian Doctrine.Vol. 1*, Addis Ababa: Mekane Yesus Seminary, 1960, P. 148-150.



የአምላክን ቃል እንዲያነብቡት የታሰበ በመሆኑ ነው:: ማንም አንብቦ እንዲረዳው ስለታታሰበ፣ ብዙኀኑን ማዕከል አድርጓል::

ሁለተኛው የቋንቋ አጠቃቀም፣ ክስተታዊነትን ማዕከል የማድረጉ ወይም የመላበሱ ሁኔታ ነው:: ነገሮችን ከጸሐፊዎችም ሆነ ከአንባቢያን እይታ አንጻር የሚዘግብ ወይም የሚያስቃኝ ነው:: ክስተታዊ ነው (Situational) ስንል፣ ኢሳይንሳዊነቱን መግለጣችን ነው:: ስለሆነም፣ በሳይንስ እይታ ሳይሆን፣ በዚያን ዘመን በነበሩ ሰዎች የጋራ መረዳትና በየትኛውም ዘመን በሚኖሩ ሕዝቦች ዘንድ በክስተታዊ እይታ ወይም ቅኝት በኩል ነገሮችን የሚያስቀኝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: መሬት በፀሐይ ዙሪያ በዛቢያዋ ላይ ትዞራለች ከሚለው የዘመኑ ሳይንሳዊ አገላለጥ ይልቅ፣ ፀሐይ ወጣች፤ ጠለቀች፣ የሚለውን ተለምዷዊና ዕለታዊ መግለጫን ይጠቀማሉ::

ሦስተኛው የቋንቋ አጠቃቀም ወይም ጠባይ፣ ባህላዊነትን የመላበሱ (Cultural) እውነታ ወይም ጉዳይ ነው:: የሰው ልጆች የሚኖሩት በባህል ውስጥ ነው:: ስለሆነም፣ በሚናገሩት፣ በሚያደርጉትና በሚጽፉት ነገር ሁሉ ውስጥ ባህላቸው ሊንጸባረቅና ሊታይ ይችላል:: አንዱ ባህል ከሌላው የተለየ በመሆኑ ምክንያት የጸሐፊዎቹ ባህል አንዳንድ ጊዜ ከእኛ ባህል ጋር ተጋጭቶ ሊታይ ይችላል:: ከባህል መንጸባረቅ የተነሣ ጽሑፉን ልናጣጥል አይገባም::

አራተኛው የቋንቋ አጠቃቀም ባሕርይ ደግሞ፣ መለኮትን ሰዋዊ በሆነ መልኩ (እንደ ሰው)፣ ለምሳሌም የእግዚአብሔር ዓይኖች፣ የእግዚአብሔር እጅ፣ የእግዚአብሔር ክንድ...ወዘተ በሚል የመግለጥ ልምምድ ነው:: ይህ እግዚአብሔርን ሰዋዊ በሆነ መንገድ የመግለጥ ልምምድ ወይም ሁኔታ (Anthromorphic Expression) እኛ የሰው ልጆች እርስ በርስ ለመግባባትና ልንለው የፈለግነውን ነገር ለመግለጥ የምንጠቀምበት እንጂ፣ እግዚአብሔር እንደ ሰው አካል አለው ለማለት የምንጠቀምበት አለመሆኑ መታወቅ አለበት:: እግዚአብሔር መንፈስ ነውና:: (ዮሐ. 4:24) እግዚአብሔር ለሙሴ፣ «በውኑ ክንዴ አጭር ነውን .»

ሲለው (ዘኁ. 11 :23) የሕዝቡን ጥያቄና መሻት መስጠት የሚችል መሆኑን ገለጠለት እንጂ፣ ክንድ አለኝ ማለቱ አልነበረም:: ነቢዩ፣ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ምድር ሁሉ ይመለከታሉ ሲል፣ የእግዚአብሔርን ተመልካችነትም ሆነ አዋቂነት ለማመልከት እንጂ፣ እግዚአብሔር እንደ ሰው ያለ ዓይን አለው ለማለት አይደለም::

## 2 የተጻፈበት ሂደት

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብብ ወይም የሚያጠና ሰው ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች በተለይም ሙስሊም ጸሐፊያን ልብ ሊሉት የሚገባ ሌላ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ረጅም ሂደት ነው:: እዚህ ላይ የሂደቱ ክፍል የሆኑትን ስድስት መሠረታውያን ጉዳዮች በማውሳት ወደ ትንታኔ እንገባለን:: እነዚህ የሂደቱ ክፍሎች የሰዎች ትውስታዎች (The memories of men)፣ ታሪኮች (Ministrels) በተከታዮች (Disciples) የተጠበቁ ትምህርቶች፣ ወደ አንድ የመጽሐፍ መድብል የተሰበሰቡት ሁኔታ (Collectors)፣ እና አስተላላፊዎች ወይም በአንድ ላይ የተሰበሰበ መልእክት አስራጮች (Transmitters)፣ መልእክቱን ያደረሱበት ሁኔታ ናቸው:: ሌለው ደግሞ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተተረጎሙበትና (Translation) የተሰራጨበት ሁኔታ ነው::[10]

### ትውስታዎች (Memories of men)

ቅዱሳት መጻሕፍት ያለፉበት የመጀመሪያው የሂደት ክፍል፣ ትውስታዎች በመባል ሊጠራ ይችላል:: አብዛኛውን ጊዜ የትኛውም ነቢይ ወይም አስተማሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ በሚሰብክበትና በሚያስተምርበት በዚያው ወቅት ቅዱሳት መጻሕፍት አልተጻፉም:: ነገር ግን፣ ስብከቶቹም ሆነ ትምህርቶቹ በሚተላለፉበት ወቅት በሰዎች አእምሮ ውስጥ ይቀመጣሉ:: አንዳንዶች ትእዛዛት ደግሞ ወዲያውኑ ሊጻፉ ይችላሉ:: ለምሳሌም ያህል አሥርቱ ትእዛዛትን

[10] David Brown, *The Christian Scriptures: Christian and Islam 2*, London:Sheldon Press, 1968. P. 11-19.



ሙሴ ከእግዚአብሔር እጅ መቀበሉ፤ የመጀመሪያው ጽላት ከተሰበረም በኋላ ሙሴ ራሱ እንደገና መጻፉ ወዲያውኑ ለሚጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መናገር ማስረጃ ይሆናል:: በተጨማሪም፣ በአገለግሎቱ መጨረሻ ለእግዚአብሔር ምስክር የምትሆን መዝሙር እንዲጽፍ ሙሴ በእግዚአብሔር ሲታዘዝ እንመለከታለን::

ነቢያትና አስተማሪዎች ከሰበኩና ካስተማሩ በኋላ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ትምህርቶቹና ስብከቶቹ ይቀመጣሉ:: ከዚያም ትምህርቶቹና ስብከቶቹ ተደራሲያን ወይም አድማጮች፣ አንዱ ለሌላው በንግግር ከሚያስተላልፉ ትውስታ የተወሰደ በጽሑፍ የማስፈር ተግባር ይቀጥላል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ትምህርቶችና ያከናወናቸው ድርጊቶች ሁሉ በዚያኑ ጊዜ አልተጻፉም:: ነገር ግን፣ ከእርሱ የሰሟቸውን ትምህርቶችና ያዩአቸውን ድርጊቶቹን የዓይን ምስክሮች እንዳስተላለፉላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና አነሣሽነት በጽሑፍ አስፍረዋቸዋል:: አንዳንዶቹ የዓይን ምስክር (Eye witness) ስላልሆኑ፣ ከዓይን ምስክሮች ትውስታ ተነሥተው ሲጻፉ፣ ሌሎች ደግሞ ራሳቸው የዓይን ምስክር ስለሆኑ፣ ከራሳቸው ትውስታ ተነሥተው ይጽፋሉ::

እነዚህን ሁለት ትውስታዎች በመንተራስ የተጻፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ከዚህ በታች እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን::

***ከሌሎች ትውስታ የተወሰደን የሚያመለክቱ**
«እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ» ( 1ቆሮ. 15:3)

«...ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን ...»(ሉቃስ 1:1)

ሐዋርያው ጳውሎስ በተለይ ለዚህ ተጠቃሽ ምሳሌ መሆን ይችላል:: ይህም ከጌታ የተገለጠለትና የተማረውን ሁሉ ለሌሎች ለማስተላለፍና እነዚህ

የሚያስተላልፍላቸው ሰዎችም ትምህርቱን ለራሳቸው ብቻ እንዳይዙት፣ ነገር ግን ለሌሎች እንዲያስተላልፉት በመምከርም ሆነ በማዘዝ የመለኮትን ትምህርትና መገለጥ በማስፋፋቱ ረገድ እጅግ ወሳኝ የሆነውን ሚና ሲጫወት እንመለከታለን።[11] ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማስረጃነት እንቃኛለን።

«ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።» (2ኛ ጢሞ. 2:2 )

«አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ » (2ኛ ጢሞ. 3:10-11)

«ቃሉን ስበክ፤ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም።» (2ኛ ጢሞ. 4:2)

«አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ መከራን ተቀበል የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ አገልግሎትህን ፈጽም። » (2ኛ ጢሞ. 4:5) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ተራኪው በድርጊቶችና በጉዞዎች ላይ እርሱ እራሱ መኖሩን ወይም መሳተፉን የሚያመለክቱ ቃላትን ይጠቀማል። እነዚህም «ተሰበሰብን፣ ተነሣንና ሄድን» የተሰኙ ቃላት ሲሆኑ፣ የሥነ መለኮት ሊቃውንት እነዚህን ቃላት የያዙ ክፍሎችን «We sections» በማለት ይጠሩዋቸዋል።

**በሰብሳቢዎች አማካይነት የተሰበሰቡ ትምህርቶች (collectors)**

[11] በ700 ዓ.ዓ ኢሳይያስ መልእክቱን ለደቀ መዛሙርቱ ሊያስተላልፈው እንመለከታለን። ይህም ምስክን እሰር በደቀ መዛሙርቶቼም መካከል ሕጉን አትም የሚል ነው። ኢሳ. 8:16 - David Brown, *The Christian*, p. 16.



የነቢያት ደቀ መዛሙርት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በመያዝ ለትውልድ እንዲተላለፉ ጠብቀውታል። ሰብሳቢያን ደግሞ እነዚህን መልእክቶች ወደ አንድ ሙሉ መጽሐፍ እንዲካተቱ ሰብስበዋቸዋል። መልእክቶቹን መጠበቅ አንድ ትልቅ ሥራ ሲሆን፣ ሰብስቦ አንድ ላይ ማስቀመጥ ደግሞ ሌላው ዐቢይ ተግባር ነው። ሥራው እጅግ የተቀራረበ ነው። ስለሆነም፣ ሰብሳቢዎቹ ደቀ መዛሙርት ናቸው ልንል እንችላለን፤ ይህም ሰብሳቢዎቹ ከደቀ መዛሙርት የተቀበሉትን መልእክት እስካመኑበት ድረስ ነው። ነገር ግን፣ ነቢያት በሕይወት ሳሉ የእነርሱ ተከታይ የነበሩት ብቻ ደቀ መዝሙር በሚለው ስም መጠራት የለባቸውም ማለት ነው።

ሰብሳቢዎች ለነቢያትና ለመልእክታቸው ካላቸው ክብር የተነሣ መልእክቶቻቸውን በመሰብሰብ በአንድ ላይ ያስቀምጣሉ እንጂ፣ እርማት ለማድረግ አልሞከሩም። አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ቀጣይነት ለማመልከት የጨመሩት ወይም ድግግሞሻዊ መስሎ የታያቸውን ነገር የቀነሱበት ሁኔታ የለም። ነገር ግን፣ በዚህ ምትክ በዘመኑ አነጋገር «ኮምፓይል» (በአንድ ላይ ሰብስቦ ማስቀመጥ) ነው ያደረጉት።[12]

የሰብሳቢያንን ተግባር በሰፋትና በጥልቀት ለመመልከት ትንቢተ ኢሳይያስንና መዝሙረ ዳዊትን መመልከት ይቻላል። የኢሳይያስ መጽሐፍ ሦስት ክፍሎች አሉት። ይህም ክፍል አንድ ከምዕራፍ 1-39፣ ክፍል ሁለት ከምዕራፍ 40-55፣ ክፍል ሦስት ከምዕራፍ 56-66 ነው። እነዚህን ክፍሎች በይዘትና በአጻጻፍ ስልት ተመሳሳይ ስለሆኑ፣ ሰብሳቢዎች በአንድ መጽሐፍ ውስጥ አጠቃለለዋቸዋል።

መዝሙረ ዳዊትን ብንመለከት በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ ሰዎች (በግለሰብም ሆነ በመዘምራን ቡድን) የተዘመሩ መዝሙሮች የተሰበሰቡበት መጽሐፍ ሆኖ

[12] ይህን መሰል ሰብስቦ የማስቀመጥ ሂደት በቁርዓን ውስጥም ይታያል፤ አንዱ ቁጥር ከተከታዩ ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ በቁርዓን ውስጥ በብዛት ይገኛልና። የመሀመድ ቃል በቅደም ተከተል አልተቀመጠምና።-David Brown, *The Christian*, p.17.

እንመለከተዋለን:: ብዙ የዳዊት መዝሙሮች ስላሉ፣ መጽሐፉ ከዳዊት ጋር የተሳሰረ ተደርጎ ይታያል:: አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ መጽሐፍ ርእስነት የዳዊትን ስም ይጠቀማል:: ነገር ግን፣ በውስጡ የቆሬ ልጆች መዝሙርን፣ የሙሴን ጸሎት...ወዘተ እናገኛለን::

መጽሐፈ ምሳሌንም ብንመለከት በልዩ ልዩ ዘመናት የተመሰሉ ምሳሌዎች ሁሉ ተሰብስበው በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ተቀምጠው እናገኛቸዋለን:: እነዚህ ሁሉ መሠረታውያን እውነታዎች፣ የሰብሳቢያን ሚና የማይናቅም ሆነ ላቅ ያለ መሆኑን ያመለክታሉ::

ይህን መሰል ሰብስቦ የማስቀመጥ ሂደት፣ በቁርዓን ውስጥም ይታያል፤ አንዱ ቁጥር ከተከታዩ ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ በቁርዓን ውስጥ በብዛት ይገኛልና:: የሙሃመድ ቃል በቅደም ተከተል አልተቀመጠምና::[13]

በ700 ዓ.ም ኢሳይያስ መልእክቱን ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተላልፈው እንመለከታለን፤ ይህም «ምስክሩን እሰር በደቀ መዛሙርቶቼም መካከል ሕጉን አትም::»[14] የሚል ነው:: (ኢሳ. 8:16::)

*ከራስ ትውስታ የተወሰደን የሚያመለክቱ

«ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቍረስ ተሰብስበን ሳለን . . . » (የሐዋ. 20:7)

«ከእነርሱም ተለይተን ተነሣን፣ በቀጥታም ሄድን...» (የሐዋ. 21:1)[15]

አንድ ጸሐፊ፣ በአንዱ መጽሐፉ ላይ በሰዎች ትውስታዎች ላይ ተመሥርቶ የጻፈበት አጋጣሚ እንዳለ ሁሉ፣ እንዲሁ በሌላ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ የራሱን ትውስታ የሚጠቀምበት ሁኔታም አለ:: ለምሳሌ ያህል

---

[13] Ibid, p.17.

[14] Ibid, p. 16.

[15] በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ተራኪው በድርጊቶችና በጉዞዎች ላይ እርሱ ራሱ መኖሩን ወይም መሳተፉን የሚያመለክቱ ቃላትን ይጠቀማል:: እነዚህም ተሰብስበን፣ ተነሣንና ሄድን የሚሉኙ ቃላት ሲሆኑ የሥነ መለኮት ሊቃውንት እነዚህን ቃላት የያዙ ክፍሎችን-We sections- በማለት ይጠሩዋቸዋል::



ሉቃስን ብንወስድ ወንጌሉን ሲጽፍ በወንጌሉ ውስጥ ያካተታቸው ድርጊቶች በተፈጸሙ ጊዜ ስላልነበረ በዓይናቸው ካዩ ሰዎች ትውስታ ሲነሣ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በሚጽፍበት ጊዜ ደግሞ በሐዋርያት የወንጌል ሥራ እንቅስቃሴ ወቅት አብሮ የሠራና የተጓዘ በመሆኑ ምክንያት የራሱን ትውስታዎች መነሻ ሲያደርግ እንመለከታለን::

በተመሳሳይ መንገድ ሐዋርያው ጳውሎስ የሌሎች ትውስታ በመጠቀም የተናገራቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ፣ እንዲሁ የራሱን ትውስታዎች ደግሞ በመጠቀም ብዙ መጻሕፍትን እንደ ጻፈ የመጽሐፍ ቅዱሳችንን ምስክርነት እናገኛለን:: እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ (1ቆሮ. 15:3) የሚለው አባባሉ ከሰዎች ትውስታ የወሰዳቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ ያመለክተናል:: በአንጻሩ ደግሞ ሐዋርያው ከሰዎች ትውስታ ያልወሰደውን የወንጌልን ምሥጢር እንደሚሰብክ፣ ደግሞም በሚሰብከው ወንጌል ላይ ከእርሱ በፊት የሐዋርያነት ጥሪ ከደረሳቸውና መሪዎች ከሆኑት ሰዎች እንዳልወሰደው ወይም ባለው ላይ ማንም እንዳልጨመረለት በግልጥ ይናገራል:: ለማስረጃነትም ሁለት ክፍሎችን እናያለን::

«አስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ ይህን ምሥጢር በመግለጥ አስታወቀኝ::» (ኤፌ. 3:3) በመቀጠልም፣ «ይህን ስታነብቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ::» (ቁ.4)

«አለቆች የመሰሉት እንዳች እንኳ አልጨመሩልኝምና::» (ገላ. 2:6 )

## ታታሪኮች /Ministrels/

እንደ ዛሬው ዘመን የታተሙ መጻሕፍት በሌሉበት ጊዜ አስተማሪዎች የነበረተሰቡን የጋራ አስተሳሰብና በአፈ ታሪክ መልክ ይተላለፍ የነበሩ ታሪኮችና የእምነት ትምህርቶች በትረካ መልኩ ለአዲሱ ትውልድ ያስተላለፉ ነበር:: የእነዚህ አስተማሪዎች ተሰጥኦም በአብዛኛው

ነገሮችን እየተረኩ ማቅረብ ነው። እነዚህ ሰዎች ሚኒስትሬልስ በመባል ይጠራሉ።

እነዚህ ሰዎች ከኅብረተሰቡ የጋራ መረዳትና ግንዛቤ የሚወጡ አይደሉም። ነገር ግን፣ ለመልእክቱ ቅርጽን መስጠትና የሚስብ እንዲሆን ማድረግ ዋነኛ ተግባራቸው ነው። ከዘፍጥረት 1-11 ባሉት ክፍሎች ውስጥ የምናገኛቸው ብዙዎቹ ታሪኮች በዚያን ዘመን የነበሩ ሕዝቦች ሁሉ የሚያምኑትን ነገር በታሪክ መልክ እያዘጋጁ ያቀርቡ በነበረበት መልኩ የቀረቡ ናቸው። አይሁዶችም ከዚህ የተለየ ነገር አላደረጉም። አንድን እውነት በታሪክ መልክ መጻፍ ወይም ከታሪኩ ሳይነጥሉ ማቅረብ የተለመደ የአጻጻፍ መንገድን መከተል ከመሆኑም ባሻገር ከሰዎች አእምሮ ውስጥ በትውስታ መልክ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ የሚጠቅምም ነው። ይህ እንግዲህ ጥሩ የማስተማሪያን ዘዴ የማወቅና የመምረጥን፣ መርጦም የመጠቀምን ብቃትና ብልሃተኝነትን የሚያሳይ ነው።

## በተከታዮች የተጠበቁ ትምህርቶች /Disciples/

የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች ለተተኪው ትውልድ በንጽሕና እንዲተላለፉ በመጠበቅ ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎች አሉ። እነዚህን ሰዎች ዲሳይፕልስ ወይም ተከታዮች ስንል እንጠራቸዋለን። ለእነዚህ ሰዎች መግለጫነት ጥሩ ምሳሌን መውሰድ ካስፈለገ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት (ተከታዮችን) መጥቀስ ይቻላል። ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ እየተመላለሰ ባገለገለባቸው ጊዜያት ያስተማራቸውን ትምህርቶቹን በማስታወስ ከእርሱ ዕርገት በኋላ ወደ ክርስትና እምነት ለመጡ ሰዎች አስተላልፈዋቸዋል።

ከእነዚህ ሰዎች መካከል ዋነኞቹ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ናቸው። እነዚህ ሰዎች ያስተማሩዋቸውና ያሠለጠኑዋቸው አገልጋዮችም በተራቸው ለሌሎች አስተምረውታል።

## መልእክት አሰራጮች መልእክቱን ያደረሱበት ሁኔታ (Transmitters)



የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን በተሟላ መልኩ ወደ አንድ ጥራዝ (ብሉይ ኪዳን ወይም አዲስ ኪዳን፣ አሊያም ብሉይንም አዲስንም ጨምሮ የያዘ መጽሐፍ) የማተሚያ ቤት ባልነበረበት ዘመን በእጃቸው እየገለበጡ ያስተላለፉ የነበሩትን ጸሐፊዎች መልእክት አሰራጮች ብለን እንጠራቸዋለን። በዚህ መልኩ የተላለፈን መልእክት ነው ዛሬ በዘመኑ የማተሚያ ቤት ቴክኖሎጂ በመጠቀም እያባዛን ወደ ሰው ሁሉ እጅ ለማድረስ የቻልነው፤ የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድም በሙላት የተገለጠበትን መጽሐፍ ለማግኘት የቻልነው።

ይህ በእጅ እየተገለበጠ ለሌሎች የማስተላለፍ ሂደት ደግሞ ራሱን የቻለ ሂደት ነው። በዚህ ሂደት ወቅት የሚፈጠሩ አንዳንድ መጠነኛ ግድፈቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል «በተደጋጋሚ የተጻፈ ቃላትን ወይም ፊደላትን መድገም አለመቻል፣ አንድ ጊዜ የተደረገን ክስተት መደጋገም፣ የአንድን ማኑስክሪፕት ተመሳሳይ አንቀጽ በድጋሚ ማሰባሰብ የጽሑፍ መስመርን መዝለል የግርጌ ማስታወሻንና ለየምዕራፉ በአዘጋጆች የተሰጡ ርእሶችን የመጻሕፍቱ ክፍል አድርጎ ማካተት ናቸው።»[16] ነገር ግን፣ ልዩ ልዩ ማኑስክሪፕቶች ስላሉ አንዱን ከሌላው ጋር በማመሳከር የተዛደለው ነገር ይታወቃል፣ ይተካልም። በዚያ ላይ የፊደልና የቃላት ግድፈቶች ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት አይለውጡትም፤ ጥቂቶችና ልዩነት ማምጣት የሚችሉ አይደሉምና።[17]

## መልእክቱ ወደ መላው ዓለም የደረሰበት ሁኔታ-Translators

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዓለም ሁሉ መድረስ ስላለበት መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ልዩ ልዩ

---

[16] ዳንኤል ተሾመ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣27-28

[17]የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ባደረጉት ጥናት፣ በሥነ ጽሑፍ ረገድ የተገኘ ግድፈት ከመቶ አምስት ፐርሰንት አልያም ከዚያ በታች እንደሆነ አረጋግጠዋል። ስለሆነም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ መልእክት ላይ ምንም ዓይነት ለውጥም ሆነ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ አልቻሉም። የመጀመሪያውን በእጅ የተጻፈ ጽሑፍ (የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል) ለማግኘት የሚደረገው ጥናት ቴ ቴክስቹዋል ክሪቲሲዝም (texual criticism) በመባል ይጠራል። Gordon D. Fee, *New Testament Exegesis: Revised Edition*, Westminister: John Knox, 1993, p. 40.

ቋንቋዎች ተተርጉሟል:: ሰው ሁሉ አፉን በፈታበት ቋንቋ የእግዚአብሔርን ቃል ማግኘቱና ማንበቡ በዚያም መማሩና መስበኩ ከፍተኛ ግንዛቤን ለማግኘት ይረዳዋል:: በዚህም ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍት በከፍተኛ ደረጃ በመላው ዓለምም ሆነ በአገራችን በኢትዮጵያ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል::[18]

በየትኛውም የትርጉም ሥራ ውስጥ ፍጹምነት አይጠበቅም፤ አንድ ቋንቋ ሌላውን መቶ በመቶ መተካት አይችልምና:: ስለዚህ የትርጉም ልዩነቶች (Translation Varience) ይጠበቃሉ:: ሆኖም የተለያዩ ትርጓሜዎችን እያነጻጸሩ በመጠቀም ትክክለኛውን አሳብ የያዘን ፍቺ ማግኘትም ሆነ በዚያ ፍቺ መገልገልም ሆነ ማገልገል (ማስተማር) ይቻላል::

መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚገባ አንብቦ ለመረዳት ብሎም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሂስ ለመሰንዘር አስቀድሞ የተጻፈበትን መንገድና ሂደት መማርና ማወቅ ያስፈልጋል:: ይህን አለመረዳት፣ ስለማያውቁት ነገር ማውራትን ያስከትላል:: ይህ ደግሞ እብደት ሲሆን፣ እራስንም ሆነ ሌሎችን ለማሳሳት ይዳርጋል::

ስለሆነም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት መንገድና ሁኔታ ለመረዳት አስቀድሞ የተጻፈበትን መንገድና ሁኔታ ለማወቅና ትክክለኛውን ግንዛቤ ለማግኘት መጣር ያስፈልጋል::

**ለ. የሥነ አፈታት (Hermeneutics) እውቀት ማጣት እንዲሁም ለማወቅና በዚህ ለመጠቀም ደንታ ቢስ መሆን**

**የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችና የትርጉም ዘዴዎች**

**የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች**

[18] ዳንኤል ተሾመ፣ *ስለ መጽሐፍ ቅዱስ* 27-28::



መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ መተርጉም የሚፈልጉ ብዙ ነገሮች ይገጥሙናል:: መጽሐፍ ቅዱስን የምንተረጉምባቸው ልዩ ልዩ የትርጉም ዘዴዎች አሉ:: እነዚህን ዘዴዎች ሳንይዝ መጽሐፍ ቅዱስን እናጠናለን ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ወይም የዋህነት ሲሆን፣ በድርጊት ከተሞከረም ወደ ተሳሳተ ፍቺ ወይም ትርጉም ስለምናመራ ግራ መጋባትና መጭበርበርን ነው የምናተርፈው:: ሙስሊም ጸሐፊያን የሚቸገሩበት አንዱ ነጥብ ይህ ነው:: እዚህ ላይ እያንዳንዱ አንባቢ፣ አንባቢ ብቻ ሳይሆን ተርጓሚም መሆኑን ልብ ማለት ይኖርብናል::

መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ሥነ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው:: እነዚህ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥነ ጽሑፎች የራሳቸው የሆነ ባሕርያት አላቸው:: ትርጉም የሚፈለገው እንደ የሥነ ጽሑፉ ዓይነትና ባሕርይ መሆኑም መጤን አለበት:: ከዚህ በታች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን መሠረታውያን የሆኑ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን እንዲሁም እነዚህ ሥነ-ጽሑፎች (የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች) እራሳቸው ትርጉም የሚሰጡበትን ወይም ለትርጉም የሚሆን ብርሃን የሚፈነጥቁበትን ሁኔታ እንመለከታለን::

### 1 ትረካዊ አጻጻፍ (Narration)

ትረካዊ አጻጻፍ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በብዛት የምናገኘው የሥነ ጽሑፍ ዓይነት ሲሆን፣ የራሱ የሆኑ የትርጉም እሴቶች አሉት:: ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹን እንመለከታቸዋለን::

የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ሕይወት ውስጥ ተገልጦ ሥራ ስለ ሠራ፣ በትረካዊ አጻጻፍ መልኩ መቅረቡ መጽሐፍ ቅዱስ በታሪክ ውስጥ የተገለጠ እውነት መሆኑን ያመለክተናል:: በተጨማሪም፣ መልእክቱ ሁል ጊዜ ሕያው መሆኑንና በዛሬው ዘመን ባሉ ሰዎችም ሕይወት ውስጥ ለውጥ (Impact) የሚያመጣ መሆኑን ይጠቁማል:: ይህ እንግዲህ የእግዚአብሐር ቃል መለኮታዊ ጉልበትና ሥልጣን እንዲሁም ታማኝነት ያለው መሆኑን ያረጋግጥልናል:: ዝም ብሎ ከአየር ላይ

ያልወረደ እንዲሁም ከሰዎች ምናብ ያልተገኘ መሆኑን ያመለክተናል::

በትረካዊ አጻጻፍ ውስጥ ጸሐፊው ለአንባቢያን ግልጥ አድርጐ የሚያቀርባቸው (Explicit) ነገሮች አሉ:: አንዳንድ ጉዳዮች ደግሞ ግልጥ ባያደርጋቸውም ከአነጋገሩ (ከአንጻጻፉ) እንድንረዳቸው (Implicit) ለሕሊናችን ይተዋቸዋል::

በታሪካዊ አጻጻፍ ውስጥ አራት መሠረታውያን ነገሮችንም እናገኛለን::[19] የመጀመሪያው፣ አንባቢያን በታሪኩ ውስጥ በአሳብ የመሳተፋቸው ጉዳይ ነው:: ሌላው ደግሞ፣ የታሪኩ መዋቅር ነው:: ታሪኩ ልብን በሚያንጠለጥሉ፣ በሚያስገርሙና በሚያስደስቱም ሆነ በሚያስቈጡ ነገሮች ተዋቅሮ የሚቀርብበት ሁኔታ ነው:: ሦስተኛው ደግሞ፣ ክፍተት የመስጠት ሁኔታ ነው:: የዚህም ጠቀሜታው ጸሐፊው በቀጥታ ሊናገረው ያልወደደውን ነገር አንባቢው በራሱ ክፍተቱን የሚሞላበት ሁኔታ ነው:: የመጨረሻው ደግሞ፣ «በተለያዩ ጉዳዮችና ሁኔታዎች ላይ አንባቢው የሕሊና ዳኝነት የሚሰጥበትና ታሪኩን በአእምሮው ቀርጾ የሚያስቀምጥበት ሁኔታ ነው::»[20]

ትረካዊ አጻጻፍ የነቢያትን፣ የነገሥታትን፣ የካህናትን፣ የሐዋርያትን እንዲሁም የእግዚአብሔር ሕዝቦችን ሕይወት፣ ይህም ሲባል፣ የብርታታቸውንም ሆነ የውድቀታቸውን ትክክለኛ ገጽታ በታማኝነት ያስቃኘናል:: ሰዎች የቱንም ያህል ታላቅ ቢሆኑ ኃጢያተኞች መሆናቸውን ያመለክተናል:: አይሸነግለንም ወይም ደግሞ በብልሃት የተፈጠረ ተረትን እንዲሁም

[19] J. Christ Wright, Evangelical Theological College, *Lecture note*, Mar. 2003.

[20] ጎርደን ፊ. እና ዳግላስ ስቱዋርት የተባሉ የሥነ አፈታት ምሁራን "ወደድንም ጠላን እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነብበት ጊዜ አንባቢ ብቻ ሳይሆን ተርጓሚም ጭምር ነው" ይላሉ:: Gordon D. Fee and Douglas Stuart. *How to read the Bible for all its Worth: A Guide to understand the Bible.* Michigan: Zondervan, 1981. P. 14. ሁል ጊዜ በሥነ አፈታት ተግባር ትጠመዳለህ:: (ገጽ 62)::



የማስተባበልን ሁኔታ አያስቃኘንም:: ይህም የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው:: እግዚአብሔር አይሸነግልም፣ ኃጢአተኛውንም ጻድቅ ነህ አይልም:: ስለሆነም፣ የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ፍጹም የሆነ እምነት የሚጣልበት መሆኑን ያመለክታል::

በትረካዊ አጻጻፍ ውስጥ የታሪኩ ባለቤት እግዚአብሔር በቀጥታ ተገልጦ ሲገኝ ወይም በቀጥታ ሳይገለጥ በውስጠ ታዋቂነት ሊኖር ይችላል:: ከታላላቅ ሰዎች ተግባራት በስተጀርባ እርሱ መኖሩን ለማመልከት በፈለጉ ጊዜ ጸሐፊዎቹ ስሙን ይጠቅሳሉ:: ነገር ግን፣ ከዚህ ታሪክ በስተጀርባ እግዚአብሔር እንዳለ ሰዎች እራሳቸው እንዲያዩ በሚፈልጉበት ጊዜ ተግባራቶቹን ብቻ ገልጠው ያልፋሉ::

**ታሪካዊ አጻጻፍን በተመለከተ ልብ ልንላቸው የሚገቡ መመሪያዎች፤[21]**

1. ታሪካዊ አጻጻፍ ለመሠረተ እምነት አስተምህሮ (Doctrine) በቀጥታም ሆነ እንደፈለግን ልንጠቀምበት አይገባም:: ነገር ግን፣ በቀጥታ አነጋገር ለተሰጠ ዶክትሪን (አስተምህሮ) በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ ገላጭ ምሳሌነት ያላቸውን ድርጊቶች በማስቃኘ ት ትምህርቱን ተጨባጭ አድርገውና አጒልተው እንዲያሳዩን ያደርጋል::

2. ትረካዊ አጻጻፍ ምን ሊደረግ ይገባ ነበር? የሚለውን ሳይሆን የሆነውንና የተከሰተውን ነገር ነው የሚያስቃኘን:: አንድን ታሪክ ካስቀመጠልን በኋላ በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱ ገጸ ባሕርያት ድርጊት ላይከንንም ይችላል::

3. ስለዚህ ሰዎች የሚያደርጓቸው ድርጊቶች ሁልጊዜ መልካም ምሳሌ ላይሆኑ ይችላሉ:: ብዙ ገጸ ባሕርያት መልካምነት ላይታይባቸውም ይችላል:: ስለዚህ፣ ሁሉንም እንደ በጐ ተግባር መውሰድ አይገባንም::

[21] Ibid, 83-84.

4. በትረካዊ አጻጻፍ የቀረቡልን ሥነ ጽሑፎች ተመርጠው የወጡና ያልተሚሉም ናቸው:: የእግዚአብሔር መንፈስ ያነሣሣቸው ጸሐፊያን ቢነገሩ ይጠቅማሉ ብለው ያስፈሩቸው ሲሆን፣ ጥቅል መልእክታቸው ነው ተፈላጊነትም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት የተላለፈው:: አስቀድሞ እንደ ተገለጠው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክትን፣ ታሪኮች በምሳሌነት ያጠናክሩልናል:: በተጨማሪም፣ በትረካዊ አጻጻፍ የቀረቡ ጽሑፎች በውስጣችን ያሉ ወይም የሚመላለሱ ጥያቄዎችን ሁሉ ለመመለስ የተሠሩ አይደሉም::

**ታሪካዊ መጻሕፍትን ስናነብብ ልንወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች፤**[22]

i. ውስጠ ወይራዊ ትርጉምን ለማግኘት የመሞከር ልምምድ ብዙውን ጊዜ የማይቻልና አስቸጋሪ እንዲሁም ወደ ስሕተት የሚመራ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: በክፍሉ ውስጥ የሌለን ትርጉም እንድንሻ የሚያደርገን ስለሆነ፣ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በእርግጥ እንደ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ያሉ ውስጠ ወይራዊነትን የተላበሱ ክፍሎች አሉ:: እንደዚህ ዓይነት ክፍሎች በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥም ይገኛሉ:: ቢሆንም እነዚህ ውስጠ ወይራዊነትን የተላበሱ ክፍሎች ቀላል ትረካ አይደሉም፤ በብዙ ሥዕል የተሞሉና ውስጠ ወይራዊ ትርጉምን የተላበሱ መሆናቸው በቀላሉ የሚለይ ነውና::

ii. ሙሉ የሆነውን ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ ሁኔታ ዘንግቶ ትርጉም የሚሻበት (Decontexualizing) ሁኔታ አደገኛም ሆነ አሳች ነው:: ለትርጉም ፍንጭ የሚሰጡ ብዙ ነገሮችን ትቶ በአንዳንድ ጥቃቅን ነጥቦች ብቻ ላይ ማተኮር ተገቢ አይደለምና ከዚህ መጠበቅ ያስፈልጋል::

iii. ልዩ ትርጉም የመስጠት (Redefinition) እና የማዳቀል (False Combination) ልምምድ ከቶ ሊጠገዱ

[22] Ibid, 83-84.



የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው:: ቀጥተኛ የሆነው ትርጓሜ ለብዙዎች እነርሱ የሚሹትን ነገር ሊልላቸው ሳልቻለ ጊዜና ስሜታቸው በቀዘቀዘ ጊዜ፣ እነርሱ ሊናገሩት የወደዱትን እንዲናገር የማድረግ አደገኛ አዝማሚያና እንደ ቁርጠ ቀጥል ሁሉ፣ አንዱን ነገር ከአንዱ ስፍራ፣ ሌላውን ደግሞ ከሌላ ስፍራ ወስዶ የማገናኘቱ ሁኔታ ብዙዎችን አደገኛ ስሕተት ላይ የሚጥል ነገር ስለሆነ፣ ይህ መገታት አለበት::

iv. እንደ ልዩ የመተርጐሚያ ቍልፎች አድርገን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሉ መጻሕፍትን (Extra Canonical Authority) ለመጠቀም መሞከር አንዱ አደገኛ ልምምድ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢራትን በየትኛውም መጽሐፍ መነጽርነት ለመፍታት መሞከር የዋህነትም፣ ስሕተትም ነው::

V. መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ፣ ከሁሉም ክፍል ለኑሮአችን የሚሆን መሪ ቃል ወይም ዕለታዊ መመሪያ ለማውጣት መሞከር (Moralizing) እንዲሁም ሁሉንም ክፍል ለእራስ እንደ ተሰጠ አድርጐ መተርጐም (Personalizing) ከቶ አይገባም:: እንደዚህ ያሉ ልምምዶች ሁሉ ጸሐፊዎቹን ልብና አእምሮ በቀላሉ እንድንስት ወይም እንዳንፈልግ የሚያደርጉ ናቸው::[23]

## 2. ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ (Poetic)

ሥነ ግጥማዊ አጻጻፍ በውስጡ የሚይዛቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ:: ከነዚህም መካከል የፍቅር ግጥሞች ለምሳሌም (መኃልየ መኃልዩ ዘሰሎሞን)፣ የመዝሙር ግጥሞች ለምሳሌም (መዝሙረ ዳዊት)፣ እንዲሁም ምሳሌያዊ አባባሎች ለምሳሌም (መጽሐፍ ምሳሌ) ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

የእግዚአብሔር ቃል ለሰው ልጆች ሕይወት መሠረውያን የሆኑ መመሪያዎችን የያዘ እንደ መሆኑ መጠን የሰው ልጆችን ልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታዎች ያስቃኙናል:: በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊኖር

[23] Ibid, 83-93.

የሚገባን ግንኙነት (እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብና በፍጹም ኃይልህ ውደድ) በማለት፣ እንዲሁም (በሰውና በሰው መካከልም ሊኖር የሚገባን ግንኙነት) ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ በማለት የሚያስቃኝ ነው። (ዘዳ. 6፡4-6)

ስለዚህም፣ ሰው ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነትም ሆነ ከሰው ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግንኙነት መመሪያም ሆነ ለመመሪያው የሚሆን ምሳሌ (የሕይወትና የድርጊት ምሳሌ) ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል የመኃልየ መኃልዩ መጽሐፍ በሁለት ፍቅረኛሞች ማለትም በባልና በሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባ እውነተኛ ፍቅር ብዙ ቁምነገሮችን የሚያስጨብጥ መጽሐፍ ነው። ስለ ጋብቻ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች ያስተምራል። የሁለቱ ፍቅረኛሞች የፍቅር ግንኙነትም በፍቅርና በጋብቻ ሊተሳሰሩ ለሚዘጋጁትም ሆነ ለተሳሰሩት ሁሉ የሚሰጠው ፋይዳ ቀላል የሚባል አይደለም። ሕይወት ፈርጀ-ብዙ ስለሆነች ለሁሉም የሕይወት አቅጣጫዎች በሚሆን መልኩ ለምሳሌም በትዳር ግንኙነት መልኩ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አሳብና መለኮታዊ ትምህርት መቅረቡ የመጽሐፍ ቅዱስን ክብር የሚያሳጣው ሳይሆን፣ ለሁሉም የሕይወት ገጽታዎች የሚናገር መልእክት ያለው ማለፊያ መጽሐፍ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ያመልካሉ። ይህ አምልኮአቸው ደግሞ በሥነ ግጥምም ሆነ በዜማ የሚገለጥ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጠል የዘመሩዋቸው መዝሙራትን መያዙ፤ እንዲሁም እግዚአብሔርን ባልታዘዙና በኃጢአታቸው ምክንያት በተቀጡ ጊዜ በመከራ ውስጥ ሳሉ የገጠሙዋቸውና ያዜሙዋቸውን የኀዘን እንጉርጉሮዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተታቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የዳበረ ታሪካዊ መሠረት፤ በሕይወት የተፈተሸ መገለጥና መልእክት የያዘ፤ ሁሉንም የሕይወት ገጽታ ቁልጭ አድርጐ የሚያመለክት ተዓማኒነት ያለው መጽሐፍ እንደሆነ ያመለክተናል።



ሰዎች ብዙ ሊማሩዋቸው የሚገቡ ነገሮችን በቀላሉ በተረትና በምሳሌዎች ሲቀበሉም ሆነ ሲይዙ ይስተዋላሉ። ልዩ ልዩ ሕዝቦች ሊያስተላልፉት የሚሹትን ማኅበራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ መልእክቶች በምሳሌዎች ሲያስተላልፉ ይስተዋላሉ። የእግዚአብሔር ሰዎችም ይህንኑ በምሳሌያዊ አጻጻፍ የመጠቀም ልምምድ በየጊዜው እያዳበሩ ከመምጣታቸውም በላይ በዚሁ የአጻጻፍ ዘዴ በመጠቀም ቅዱሳት መጻሕፍትን ጽፈውልናል። ምሳሌያዊ የአጻጻፍ ዘዴ ልብን ሊነኩ በሚችሉ ሥዕላዊ ቃላት የሚጠቀም በመሆኑ ምክንያት አንባቢ በቀላሉ ሊረሳቸው የማይችሉ እውነቶችን ለማስተላለፍ ይረዳል። ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃል ውበትም ሆነ ተዓማኒነት ማረጋገጫ እንጂ፣ እንደ ድካም የሚታይ ምልክት ከቶ ሊሆን አይችልም።

## 3. ትምህርታዊ አጻጻፍ (Didactic)

ትምህርታዊ አጻጻፍ እንደ ሕግጋት፣ ትእዛዛትና መመሪያዎች ያሉ የመገለጥ ክፍሎች የሚጻፉበት የአጻጻፍ መንገድ ነው። በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት፣ በነቢያት መጻሕፍትና በአዲስ ኪዳን መልእክቶች ውስጥ ትምህርታዊ የሆኑ ክፍሎች በብዛት ይገኛሉ። እነዚህም ክፍሎች በቀጥታ መመሪያ የሚሆኑ ጉዳዮችን ከነአፈጻጸማቸው በዝርዝር የሚይዙ ናቸው።

በትምህርታዊ አጻጻፍ (ክፍሎች) ውስጥ ልዩ ልዩ ሕግጋትን፣ መመሪያዎችን (Principles)፣ ትምህርቶችን፣ መረጃዎችን፣ አሳቦችንና የልዩ ልዩ መመሪያዎችን እናገኛለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ አስተምህሮ በትምህርታዊ ክፍሎች ውስጥ ነው በብዛትም ሆነ በጥልቀት የሚገኘው። ከታሪካዊ ክፍሎች ይልቅ መሠረተ እምነት (Doctrine) የሚወሰደው (ሊወሰድ የሚገባው) ከትምህርታዊ ክፍሎች ነው። በትምህርታዊ አጻጻፍ የሚጻፍ ነገር በቀጥታ እንደ ሕግና መመሪያ እንዲሁም መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰድ ነው።

ለምሳሌ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ ማገልገል፣ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ

መሞት፣ ከሙታንም የመነሳት ጉዳይ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ በታሪካዊ አጻጻፍ ተጽፎ ይገኛል:: እነዚህም የመገለጥን ታሪካዊ መሠረት የሚያስጨብጡንና ትምህርታዊ አጻጻፍ በኩል ለሚሰጡ መመሪያዎች እንደ መግቢያም ሆነ መሠረት (Foundation) የሚያገለግሉ ናቸው:: ሐዋርያቱ በጻፉዋቸው መልእክቶቻቸው በታሪካዊ አጻጻፍ የተቀመጡ (የተሰጡ) እውነታዎችን ምንነት እያብራሩና አንድምታቸውን ወይ ም ለእኛ የሚሰጡትን ፋይዳ እየተነተኑ ያስተምሩናል፤ ለመገለጦቹ ሊኖረን የሚገባ ምላሽን ያስቀምጡልናል:: ስለዚህም፣ በትምህርታዊ አጻጻፍ በኩል የተሰጡ ትምህርቶችን በቀጥታ ለሕይወት መመሪያነት (Life Principles) ስንወስዳቸው፤ በትረካዊ አጻጻፍ የተሰጡ ክፍሎችን ደግሞ ለትምህርቱ ታሪካዊ መነሻ (Historical background)፣ መግቢያ (Introduction) እንዲሁም ማብራሪያ ምሳሌ አድርገን እንወስዳቸዋለን:: ስለዚህም፣ ያለ ትምህርታዊ ክፍሎች መነሻነት ከታሪክ ብቻ ተነሥተን መሠረተ እምነት አንቀርጽም ማለት ነው::

## 4. አቡቀለምሲሳዊ-ራእያዊና ሕልማዊነትን የተላበሰ

በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ውስጥ ለምሳሌም እንደ ዮሐንስ ራእይ፣ ትንቢተ ዳንኤልና ትንቢተ ሕዝቅኤል ያሉ ትንቢታዊ መጻሕፍት፣ ራእይንና ሕልምን የተላበሱ ክፍሎች ይገኛሉ:: እነዚህ ክፍሎች የተጻፉበት መንገድ በመጠኑም ቢሆን ታሪካዊ አጻጻፍን ይምሰል እንጂ፣ ራሱን የቻለ የአጻጻፍ መንገድ ወይም ዘዬ ነው:: ይህ መንገድ ራእያዊና ሕልማዊነትን የተላበሰ የአጻጻፍ ዘዴ በመባል ይጠራል::

ራእያዊና ሕልማዊነት የተላበሰ አጻጻፍ (አቡቀለምሲሳዊ ሥነ ጽሑፍ) ትንቢታዊ ገጽታው ይበዛል:: ሊሆን ወይም ሊገለጥ ያለን ማኅበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ (በምድር ላይ ሊመጣ ያለን ታሪካዊ ክስተት) ሥዕላዊ የሆኑ ብዙ መግለጫዎችን በመጠቀም ያመለክታል:: ለምሳሌ ያህል ትንቢተ ዳንኤል 2 ላይ ያለውን በሕልምና በራእይ መልክ የመጣ (ቁጥር 28) ትንቢታዊ



መልእክት መመልከት እንችላለን:: ይህ ሕልም ወይም ራእይ ንጉሥ ናቡከደነፆር ያየው ታላቅና ብልጭልጭታው የበዛ ምስል ነው:: የምስሉ ራሱ ጥሩ ወርቅ፣ ደረቱና ክንዶቹ ብር፣ ሆዱና ወገቡም ጭኖቹም ብረት፣ እግሮቹም እኩሉ ብረት እኩሉም ሸክላ ነበር:: በዚህ ሕልም ውስጥ አንድ ድንጋይ እጅ ሳይነካው ከተራራ ላይ ተነቅሎ ያን ምስል እንደ መታው፣ ወርቁም፣ ብሩም ናሱም፣ ብረቱም ሸክላውም በአንድ ላይ እንደ ተፈጩና በንፋስ ተጠርጉ እንደ ተወሰደ፣ ድንጋዩም ታላቅ ተራራ ሆኖ ምድርን ሁሉ እንደ ሞላ እንመለከታለን::

በዚህ በንጉሥ ናቡከደነጻር ሕልምና ራእይ ውስጥ እንደምንመለከተው ራእያዊና ሕልማዊነትን የተላበሰ አጻጻፍ ትንቢታዊም ሆነ ውስጠ ወይራነትን የተላበሰ ሆኖ እናገኘዋለን:: የሚፈታውም ሥዕላዊነትን የተላበሱ ነገሮችን እያንዳንዳቸውን በመተርጐም ነው:: በሌላ አባባል ከሥዕሎቹ በስተጀርባ ተደብቀው ያሉ ትርጉሞችን መሻት ነው:: እርግጥ ነው ይህን ሕልምም ሆነ ራእይ ለመተርጐም በዳንኤል መጽሐፍ ላይ እንደምንመለከተው መለኮታዊ መገለጥና ጥበብ ማግኘት ያስፈልጋል::

ነቢዩ ዳንኤል እግዚአብሔር በሰጠው መገለጥና ጥበብ ላይ ተመሥርቶ ይህን ራእይና ሕልም ሲተረጉም፣ ምስሉ አራት መንግሥታትን እንደሚያሳይ፤ በወርቅ ከተመሰለው የባቢሎናውያን መንግሥት ጀምሮም ተራ በተራ እነዚህ መንግሥታት እንደሚነሡ፣ በመጨረሻም፣ ሁሉን በመታችውና በፈጨችው ድንጋይ የተመሰለው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደምትነግሥና ሁሉን ፈጭታ በማይፈርስ ዘላለማዊ መንግሥትነት ጸንታ እንደምትኖር ያሳስበናል:: ወርቁ የባቢሉን መንግሥት ምሳሌ ነው፤ ብሩ የፋርስ መንግሥት ምሳሌ ነው፤ ነሐሱ የግሪክ መንግሥት ምሳሌ ነው:: ድንጋዩ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተተከለው የእግዚአብሔር መንግሥት ባይገለጥም በዳኑት ቅዱሳን ኅብረትና (በቤተ ክርስቲያን) በመካከላቸው በሚገዛው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት በምድር ላይ

ጀምሮአል (Inagurated)፤ ወደ ፍጻሜውም (Consummation) ይቸኩላል:: ለዚህ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር፣ «በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም ያለው::(ማቴ 16:18)

ይህ ክፍል በብዙ ሥዕል የተሟላ ሲሆን፣ ሥዕሎቹም በውስጣቸው ደብቀው የያዙዋቸው መልእክቶች አሉ:: ለምሳሌም ምስሉ አራት ዓይነት ገጽታ አለው:: ይህ አራት መንግሥታትን የሚያመለክት ነው:: የአራቱ ገጽታዎች መለያየት አንዱ መንግሥት በክብር ከሌላው እንደሚበልጥ፣ በተጨማሪም አራቱ መንግሥታት ያላቸውን ልዩነት ያመለክተናል:: ምስሉን መትቶ የፈጨውና ኋላም ታላቅ ተራራ የሆነው ድንጋይ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ኃይል፣ ይህም በሰው እጅ ያልመጣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጊዜ የተገለጠ መሆኑን ያሳየናል:: ከእነዱ መንግሥት ማለትም ከባቢሎን መንግሥት ውጭ ያሉት ሁሉ፣ ሕልሙ በታየበት ጊዜ ገና ያልተገለጡና ሲገለጡ ያሉ በመሆናቸው በዚህ ራእያዊና ሕልማዊነት በተሳበሰው ክፍል ውስጥ በስፋት የተቀመጠው ትንቢታዊ መልእክት መሆኑን ያመለክተናል::

ሽቡቀሰብሲሳዊ (ራእያዊና ሕልማዊነትን የተላበሰ) አጻጻፍ ሌላ ገላጭ ባሕርይው የመጨረሻው ዘመን ሁኔታ ማዕከላዊ የማድረጉ (Eschaltological) ጉዳይ ነው:: በዚህ በዳንኤል መጽሐፍ ላይ እንደምንመለከተው ከባቢሎን መንግሥት ይጀምርና እስከ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ድረስ ያለውን ሁኔታ ገና ሳይገለጥ በፊት አስቀድሞ ያመለክታል::

## 5. ፍልስፍናዊ አጻጻፍ (Philosophical)

መጽሐፍ ቅዱስ ከያዛቸው የአጻጻፍ ዓይነቶች አንዱ ፍልስፍናዊ አጻጻፍ ነው:: መጽሐፈ መክበብ በዚህ መንገድ ወይም ዘዴ የተጻፈ መጽሐፍ እንደ ሆነ መመልከት እንችላለን::

ፍልስፍናዊ አጻጻፍ ስንል ሕይወትን በፈርጀ ብዙነትዋ የማየትና የማሳየት ብሎም የማቅረብ ጠባይን



የተላበሰ ማለት ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ የእያንዳንዱን ነገር አንጻራዊ ጠቀሜታ (Relative Importance) ማሳየት አንዱና ወሳኙ ተግባር ነው:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አንጻራዊ ጠቀሜታ ያለው ነገር ሁሉ ወይ ገለልተኛ (ጠቀሚም ሆነ ጉዳት የማያመጣበት) አሊያም ደግሞ አንጻራዊ ጉዳት የሚያመጣበት ሁኔታ ወይም አጋጣሚ እንዳለ ያመለክተናል::

ፍልስፍናዊ አጻጻፍ በየትኛውም አቅጣጫ የሚራገብን ጽንፈኛ አስተሳሰብና ግትር አቋምን የሚቃወም እንዲሁም ነገሮች ካላቸው አስፈላጊነት በላይ በተጋነነ መልኩ እንዳይተረኩላቸው የሚቃወም ነው:: ማንኛውም ነገር የሚያበረክተው አንጻራዊ ጠቀሜታ እንዳለውና ሰዎች ይህን በማሰብ ሚዛናዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የሚያደርግበትን የዚህን የፍልስፍናዊ አጻጻፍ መልክ ለምሳሌነት ያህል ሁለት ክፍሎችን ከመክብብ መጽሐፍ በመውሰድ እንመልከት::

«እጅግ ወይም ጥቂት ቢበላ የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው፤ የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፍን ይከለክለዋል::» (መክ. 5:12)

«ጥበብ ከርስት ጋር መልካም ነው፤ ፀሐይንም ለሚያዩ ሰዎች ትርፍን ይሰጣል::» (መክ. 7:11)

«ከመልካም ሽቱ ከመልካም ስም ከመወለድ ቀንም የሞት ቀን ይሻላል::» (መክ. 7:1፡8)

መጠነኛ ግንዛቤን ለመፍጠር ያህል፣ ከላይ የተቀመጡትን ፍልስፍናዊ በሆነ መልኩ የተጻፉልንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መለኮታዊ መልእክቶች በመተንተን እንመለከታቸዋለን::

አንድ ተራ ሠራተኛ ማለትም ባለ ሀብት ያልሆነ ሰው ደስተኛም ሆነ በጐ የሆነ ገጽታ ያለው ተደርጐ አይታይም:: ድህነት የራሱ የሆነ በጐ ገጽታ ወይም አንጻራዊ ጠቀሜታ እንዳለው በኅብረተሰቡ የጋራ ግንዛቤ (World View) ውስጥ አይንጸባረቅም፤ ድህነት ሁል ጊዜ የሚነገርለት ጉጂ ጐኑ ብቻ ነው:: በአንጻሩ ደግሞ ባለ ሀብት መሆን ከስኬ ታማኝነት ጀምሮ ብብዙ

አምንታዊ ገጽታው ሲታይ ነው የሚስተዋለው፤ እውነቱ ግን ከዚህ በጥቂት የተለየ መሆኑ ግልጥ ነው። የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ እውነቶችን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንያዝ የሚል አቋምን ማዕከላዊ አድርጐ ሲያስተምር ወይም እርግጥ ሲሰጥ፣ ብዙም በላ ጥቂት፣ የድሀ ወይም የተቀጣሪ እንቅልፍ ጣፋጭ ናት፤ ይህ የድህነት በጐ ጐን ነው ይለናል። በአንጻሩ ደግሞ ባለ ሀብት በሁሉ ነገር የጠገበና የሞላለት ቢሆንም፣ ሙላቱም ሆነ ጥጋቡ በራሱ ከድህነትና ከማጣት የሚበልጥ ቢሆንም፣ ደስተኛ የሚያደርግ ቢሆንም፣ በጐ ገጽታ ብቻ አይደለም የሚታይበት፤ ነገር ግን፣ ይህ ብልጥግናው እንቅልፍን ይከለክለዋል። ብዙ አሳቢና ተጨናቂም ያደርጋል። ይህ ደግሞ በግልጥ የሚታይ የባለጠግነት ጐጂ ጐን ነው ይለናል።

በመቀጠልም፣ ጥበብ ብቻውን ዋጋ እንደ ሌለው፣ እንዲሁ ርስትም ብቻውን ዋጋ እንደ ሌለው ሲያመለክተን፣ ጥበብ ከርስት ጋር መልካም ነው ይለናል። እውቀትና ሀብት ሁለቱን አጣምሮ መያዝ አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክተናል። ሀብት ኖሮአቸው ጥበብ ከማጣታቸው የተነሣ ማድረግ የሚገባቸውን ለማድረግ የሚቸገሩ ብዙዎች ናቸው። ይህን እውነት በፍልስፍናዊ የአጻጻፍ መንገድ በመጠቀም ጸሐፊው ያስተምረናል።

ሽቱ የተቀባ ሰው መልካም ጠረን (የሚስብ ጠረን) አለው፣ ይህም መልካም ነገር ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ የሚበልጥ ነገር አለ። ይህም መልካም ስም ነው። አንድ ሰው መልካም የሆነ ስም ከሌለው በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ስለማይኖረው ሌላ አለኝ የሚለው መልካም ነገር እንደ ሽቱው ሁሉ ማለት ነው፤ ተቀባይነት አይኖረውም ማለት ነው። ተቀባይነት የሌለው ነገር ደግሞ ያለውን ዋጋ ያጣል። ስለዚህ፣ ለመልካም ነገራችን ብቻ ሳይሆን፣ ይህን መልካም ነገራችንን ዋጋ ለሚያሳጣው ነገር ልዩ ግምት ወይም ብልጫ ልንሰጥ ይገባል የሚል ትምህርትን ነው ጸሐፊው በፍልስፍናዊ የአጻጻፍ መንገድ የም ያስተላልፍልን።

በተመሳሳይ መንገድ ከጅማሬ ፍጻሜ፣ ከውልደት ቀን ደግሞ የሞት ቀን እንደሚሻል ወይም እንደሚበልጥ



ጸሐፊው ይነግረናል። የውልደት ቀን መጥፎ ነው አይለንም፤ ጅማሬ መጥፎ ነው አይለንም፤ ጅማሬም ሆነ የመወለድ ቀን መልካም ቢሆንም ፍጻሜና የሞት ቀን ደግሞ የተሻለ ብልጫ ወይም መልካምነት አላቸው ነው ሊለን የፈለገው (የወደደው)። አንድ ነገር መጀመሩ መልካም ሲሆን፣ እያደገና እየዳበረ ሄዶ በጐ የሆነ ድምዳሜ ላይ መድረሱ የሚጠበቅም ሆነ የሚሻል መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው። አንድ ልጅ መማር መጀመሩ መልካም ነው። ነገር ግን፣ ከተማረ በኋላ አጨራረሱ የሚጠበቅ መሆኑ አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም። እስከ መመረቅና በተማረው ትምህርት እራሱንም ሆነ ኅብረተሰቡን መርዳቱ ነው ዋናው ቁምነገር። መጀመር ቀላል ሲሆን፣ መጨረስ ከባድ ነገር ነው። ጀምሮ ማቆምና ጀምሮ መጨረስ እኩል ስፍራ አይኖራቸውም። ስለዚህ ነው ለፍጻሜ የተሻለ ግምት የሚሰጠው።

## 6. ትንቢታዊ (Prophetic)

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የምናገኛቸው ብዙ የትንቢት መጻሕፍት ትንቢታዊ መልእክትን የያዙ ናቸው። ስለ ትንቢታዊ መልእክቶችና መጻሕፍት ባህርያትም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታ ጥቂት መሠረታውያን ነጥቦችን አንሥተን እንነጋገራለን።

ትንቢታዊ መልእክቶች ሁለት መሠረታውያን ነገሮችን ይይዛሉ። አንደኛ፣ ወቅታዊነት ያለውና ሁሉን የሚመለከት መልእክት (Forthtelling) ሲሆን፣ በዚህ መልእክት ውስጥ የንስሐ ጥሪ፣ ወደ እግዚአብሔር አሳብ የሚመለሱበት ጥሪ፣ የተስፋ ቃል...ወዘተ የሚካተቱ ይሆናሉ፤ በተጨማሪም፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችንና ትምህርቶችን እናገኛለን። ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ምሳሌ አድርገን ከትንቢት መጻሕፍት በመውሰድ እንመለከታለን።

### የንስሐ ጥሪ

«ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።» (ኢሳ. 1:18)

«እግዚአብሔርም ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላልና፡-እኔን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ።» (አሞጽ 5:4)

ወደ እግዚአብሔር አሳብ የሚመልስ ጥሪ

«እስራኤል ሆይ ወደ እኔ ተመለስ ይላል እግዚአብሔር ።» (ኤር. 4:1)

«በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፤ እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም» (ኤር. 42: 10-11)

«እሦር በበትር ቢመታህ፣ ግብጽም እንዳደረግ ዘንጉን ቢያነሣብህ አትፍራው ቍጣዬ እስኪፈጸም መዓቴም እስኪያጠፋቸው ድረስ ጥቂት ጊዜ ቀርቶአልና።» (ኢሳ. 10:24-25)

የተስፋ ቃል
«እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ።» (ኢሳ. 1:18)

«... እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና፣ አትደንግጥ አበረታሃለሁ እረዳሀማለሁ። በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ» (ኢሳ. 41:10)

«መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም። » (ኢሳ. 43:25)

ልዩ ልዩ መረጃዎችና ትምህርቶች

«የነገዶችም ስም ይህ ነው ...» (ሕዝ. 48:1-7)

«እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፤ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፤ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን?» (ኢሳ. 58:6)



«በበሩ አደባባይ የሚገሥጸውን ጠሉ፣ እውነትንም የሚናገረውን ተጸየፉ። » (አሞጽ 5:10)

ትንቢታዊ መልእክቶች የሚይዙት ሁለተኛው መሠረታዊ ነገር ትንቢታዊነትን የተላበሰ ወደፊት ሊሆን ያለውን ነገር የሚያመለክት መልእክት ነው። ጥቂት ምሳሌዎችን ወስደን እንመለከለን።

«ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፤ ከሥሩም ቍጥቋጥ ያፈራል። የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል።» (ኢሳ. 11: 1-2)

«በዚያ ቀን ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ በታመነው ስፍራ የተቸከለው ችንካር ይወልቃል፤ ተሰብሮም ይወድቃል። በእርሱም ላይ የተሰቀለው ሸክም ይጠፋል። እግዚአብሔር ተናግሮአልና።» (ኢሳ. 22:25)

ትንቢታዊ መልእክቶች አንዳንድ ጊዜ ሁለቴም ሆነ ሦስቴ ሊፈጸሙ የሚችሉ (Double or Tirple Fulfilment) ትንቢታዊ መልእክቶችን ሊይዙ የሚችሉበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ለምሳሌ የብሉይ ኪዳንዋን ኤልዛቤልን ብንመለከት በየዘመኑ ሊከሰቱ ላሉ አመንዝራዎችና የአመንዝራዎች እናት ለሆኑ ግለሰቦች፣ መንግሥታትና ተቋማት ትንቢታዊ የሆነ መልእክት ያላት ናት። (1ነገ. 18:19፤ ራእይ 2:20-23)

## 7. ስብከታዊ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስብከታዊ መልእክቶችን እናገኛለን። ስብከታዊ መልእክቶች ሰዎችን ለአንድ ዓላማ የማነሣሣትና የማስተባበር፣ በአንድ ጉዳይ ላይ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥና ወደ እግዚአብሔር አሳብ ለማስጠጋት፣ ዕለታዊና ቅጽበታዊ ለውጥን ለማምጣት የሚጠቀሙ ሲሆን፤ ንስሐንና ወንጌልን ማዕከል ያደረጉም ናቸው። የሰባኪውን ስሜትም እንዳለ የሚያቀርቡ ናቸው። አንድን እውነት አጉልተው ለማሳየት ሲሞክሩም ግነታዊነትን ማዕከል ያደረጉ

ቃላትን ይጠቀማሉ:: ብዙውን ጊዜም የአንድን እውነት አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ለማሳየት ይረዳሉ:: በዚህ ጊዜም ሌላውን ተያያዥ እውነት ሳያነሱት ይችላሉ::

ስለሆነም፣ እውነትን አንጻራዊ በሆነ መልኩ የመያዝም ሆነ ከሌላው እውነት ጋር ያለውን ተያያዥነት ሚዛን በጠበቀ መልኩ የማየትም ሆነ አብሮ የማስኬድ ኀላፊነቱ የእኛ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል::

## ፰. የድንቅና ተአምራት ዘገባዎች እንዲሁም ሰላምታ እና ስንብቻ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ብዙ ድንቅና ተአምራቶች የተጻፉበት ወይም የተዘገቡበት የአጻጻፍ መንገድ አለ:: በተመሳሳይ መንገድ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች (ደብዳቤዎች) ብዙ የሰላምታ እና የስንብቻ ቃላትን የያዙ ሆነው እንመለከታቸዋለን::

ድንቅና ተአምራት የተዘገቡባቸውን ክፍሎች ስንመለከት፣ ድንቅና ተአምር የሚሠራው አምላካችን ሕያው የሆነና ዛሬም የሚሠራ (የሚያድንና የሚረዳ) መሆኑን በዋነኝነት እንመለከታለን::

በመቀጠልም፣ ይህ ሕያው የሆነው የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ ተአምራት በመሥራቱ ከአምሮአችን በላይ የሆነ መሆኑን ያመለክተናል:: ደግሞም በሰው ልጆች ሕይወትና ኑሮ ውስጥ አልገባም ብሎ እራሱን ታዛቢ ያላደረገና ንቁ ተሳትፎን (Active) በማድረግ የሰው ልጆችን ሕይወት ጣፋጭ የሚያደርግ መሆኑን ያስገነዝበናል::

እምን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚገባ፣ ፍቅሩንም ሆነ ርኅራኄውን በንድፈ አሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ የሚገልጥ መሆኑን ከሚሠራቸው ድንቃ ድንቆች መገንዘብ እንችላለን::

ይህ ሕያው የሆነና የሚሠራ የፍቅርና የርኅራኄ አምላክ ሕያው የሆነ ግንኙነትን በእርሱና በሕዝቡ መካከል



ብቻ ሳይሆን፣ በሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ውስጥም ይህን የሚያሰፍን በመሆኑ ምክንያት፣ አገልጋዮች እርስ በርስ በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ይሰጣጣሉ:: ስለሆነም፣ በመልእክቶች ውስጥ ያሉ ሰላምታዎችና ስንብቻዎች ይህን ሕያው የሆነ ግንኙነት የሚያሳስቡም ሆነ የሚያመለክቱ ሆነው እናገኛቸዋለን::

የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን የተመለከትንበት ዋነኛ ምክንያቶች ሁለት ናቸው::

1. የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች በቀጥታ ትርጉም የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩ ሲሆን (Giving Meaning)፣

2. የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች በቀጥታ ትርጉም በማይሰጡባቸው ጊዜያት ለትርጉም የሚሆን ብርሃን የሚፈነጥቁበት ሁኔታ መኖሩ ነው (Shaping Meaning)::

## የትርጉም ዘዴዎች (Interpretation Methods)

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ከምናነብባቸው ክፍሎች ውስጥ የጸሐፊያኑን አሳብ ማዕከል ያደረገ ትርጉምን እንሻለን ወይም እንፈልጋለን:: ትርጉምን የምንሻው ወይም የምንተረጉመው የጸሐፊዎቹን አሳብና መልእክት ለማግኘ ት ነው::

ለዚህ ተግባር ደግሞ የሚረዱን የተለያዩ የትርጉም ዘዴዎች አሉ:: እነዚህ የትርጉም ዘዴዎች በጥቅሉ ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለመተርጎም የሚችሉና ሁሉም ስፍራ ላይ የምንጠቀምባቸው አይደሉም::

አንዱ የትርጉም ዘዴ የሚሠራበትም ሆነ የማይሠራበት ቦታ አለ:: በተመሳሳይ መልኩ ሌሎችም የትርጉም ዘዴዎች ተገቢውን ትርጉም የሚሰጡበትም ሆነ የማይሰጡበት ሁኔታ አለ:: ስለዚህ፣ የትርጉም ዘዴዎች ያላቸው ጠቀሜታ አንጻራዊ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል:: በመቀጠልም፣ መሠረታውያን የሆኑ የትርጉም ዘዴዎችን እንመልከት::

1. ቀጥተኛ አተረጓጐም (Literal Interpretation):- ይህ የትርጐም ዘዴ የምናነብበውን ክፍል ሙሉ በሙሉ በቀጥታ የምንተረጉምበት ዘዴ ነው:: ለምሳሌ ያህል «እስራኤልን በምድረ በዳ እንዳለ ወይን ሆኖ አገኘሁት::...እስራኤል ፍሬው የበዛለት የለመለመ ወይን ነው::» (ሆሴዕ 9:10፣10:1) የሚለውን ቃል ወስደን በቀጥተኛ አተረጓጐም ዘዴ ለመተርጐም መሞከር አይገባም:: ምክንያቱም፣ ምድረ በዳ የሚለውና ፍሬው የበዛለት ወይን የሚሉት ቃላት ሥዕላዊ ቃላት ስለሆኑ፣ በሥዕሎቹ ውስጥ ያሉት ፍቺዎች በቀጥታ መተርጐምን ይከለክላሉና:: ስለሆነም፣ ይህ ክፍል በቀጠተኛ አተረጓጐም ዘዴ መተርጐም የለበትም:: በአንጻሩ «ኤፍሬም በተናገረ ጊዜ ፍርሃት ነበር» (ሆሴዕ 13:1) የሚለው ቃል በቀጥታ መተርጐም ይቻላል:: ትርጓሜውም፣ ኤፍሬም የሚሰማና የተከበረ ቃሉም ሞገስ ያለው ነው:: እርሱ በተናገረ ጊዜ ተቀባይነት ያገኛል:: ብዙዎችም ለቃሉ ይታዘዛሉ ማለት ነው::

2. ሥዕላዊ አተረጓጐም (Figurative Interpretation):- ይህ የትርጐም ዘዴ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙ ሥዕላዊ ቃላቶችን ሁሉ በመተርጐም የተሟላ ትርጐምን ለቀጥተኛ አተረጓጐም ዘዴ የሚያላብስና ረዳቱ የሆነ ዘዴ ነው::

ከላይ በሆሴዕ 9:10፣10:1 ላይ ያለውን ክፍል በሥዕላዊ የትርጐም ዘዴ መተርጐም እንደሚገባ ተመልክተናል:: እስራኤልን በምድረ በዳ እንዳለ ወይን ሆኖ አገኘሁት ማለት በምድረ በዳ ያለ ወይን ያልተመቸውና ያላፈራ እንደሆነ ሁሉ፣ እንዲሁ እስራኤልን እግዚአብሔር ሲያገኘው ሳይበዛና ሳያፈራ ማለትም ሳይደላውና ሳይመቸው ነው ማለት ነው::

እስራኤል ፍሬው የበዛለት የለመለመ ወይን ነው ማለት ደግሞ እጅግ የተመቸው፣ ስኬትንና መከናወንን ያገኘ የጥንት ችግሮቹ ሁሉ የተወገዱለት ማለት ነው::

3. ውስጠ ወይራዊ አተረጓጐም (Allegorical Interpredtation):- ዓረፍተ ነገሩን በቀጥታ ስንተረጉም ከምናገኘው ትርጐም ባሻገር ተጨማሪ ትርጐምን አዝሎ የሚገኝ ክፍል ሲገጥመን በተለይም በቀጥተኛ አተረጓጐም ስሜት የሚሰጥ ትርጐም ሲታጣ፣ ለትርጐም የምንጠቀምበት የትርጐም ዘዴ ነው:: ከጽሑፉ ወይም ከንግግር በስተጀርባ ያለን ፍቺ መሻትን ማዕከል ያደረገ የትርጐም ዘዴ ነው:: ለምሳሌ ያህል ሐዋርያው ጳውሎስ «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» (1ቆሮ. 5) ሲል ለቤተ እስራኤላውያን ከአጥፊው የመዳናቸው ምልክትና ምክንያት የነበረው በግ በጥላና በምሳሌነት የክርስቶስን የመስቀል ሞትና የማዳን ምሥጢር ያዘለ መሆኑን በሚያመለክት ትርጓሜ ሲፈታው እንመለከታለን::

4. ሰምና ወርቅ (Wax and Gold) አተረጓጐም:- በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በሁለት ፈርጅ መተርጐም የሚችሉ ክፍሎች አሉ:: እነዚህ ክፍሎች ሰምና ወርቅ የትርጐም ዘዴን ይከተላሉ:: ለምሳሌ ያህል «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ» ዘፍ. 3:15 የሚለው ክፍል በሰምና ወርቅ አተረጓጐም ዘዴ ሲተረጐም ሙሉ ትርጐምን ይሰጣል::

አንደኛው የትርጐም ፈርጅ (ሰሙ) በእባብ ዘርና በሰው ዘር (በሔዋን ዘር) መካከል ያለን ጠላትነት፣ የእባብ ዘር ሰውን የሚነድፍበትን፣ ደግሞም የሰው ዘር የእባብን ጭንቅላት የሚቀጠቅጠበትን ሁኔታ ያመለክተናል::

ሁለተኛው የትርጐም ፈረጅ (ወርቁ) ከእባቡ በስተጀርባ በሚሠራው በእባብ በተመሰለው በዲያብሎስና ከሔዋን ዘር በሚመጣው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ያለን ግንኙነት ያመለክተናል:: ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት:: ጠላት እርስዋን የሚያሳድድበትን ሁኔታ እና የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ እንደ ተባለለት ክርስቶስ የዲያብሎስን ሥራ ሁሉ የሚያፈርስበትን ሁኔታ ያመለክተናል::

5. ጥላና ምሳሌያዊ አተረጓጐም (Shadow and Copy)

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ሲገለጥ ላለው (በአዲስ ኪዳን) እውነት ወይም አካል በጥላና በምሳሌነት ያገለገሉ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም መካከል መብል፣ መጠጥ፣ በዓል፣ ሰንበትና የወር መባቻ ተጠቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን አምስቱን ነገሮች ከጠቀሰ በኋላ ስለ እነዚህ ነገሮች ማንም አይፍረድባችሁ (ማንም እነዚህን ነገሮች አልጠበቃችሁም ሲል አይውቀሳችሁ) ካለ በኋላ፣ እነዚህ ነገሮች ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው ሲል፣ በጥላና በምሳሌነት የተሰጡ ነገሮችን ዛሬ በልዩ ትርጓሜ ማለትም በአካሉ በክርስቶስ የምንመለከታቸው መሆኑን ያሳየናል። ለምሳሌ ያህል አንዱን ብንወስድ፣ ሰንበት የመለኮት ዕረፍትን ያመለክተናል። እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ዐረፈ፣ ስለዚህም እርሱ በመልኩና በአምሳሉ የፈጠራቸው ሰዎች ስድስት ቀን ሠርተው በሰባተኛው ቀን ሲያርፉ በዚያ በዕረፍታቸው ቀን አምላካቸውን ያስባሉ፤ ሥራውን ያደንቃሉ፤ ያመልኩታል፤ ክብርንና ምስጋናን ያመጡለታል። ይህ ለእርሱ ያላቸውን አክብሮትና አምልኮት የሚገልጥ ነው። (ቈላ. 2:16-17)

ወደ አዲስ ኪዳን መለስ ስንል እግዚአብሔር አምላክ ሥራውን (የማዳን ሥራውን) በክርስቶስ ሠርቶ ጨርሶታል፤ ሰዎች በክርስቶስ የተሠራውን ሥራ ሲቀበሉ በእግዚአብሔር ዕረፍት ውስጥ ይጠቃለላሉ። ይህ እንግዲህ በፍጠረት ሥራው እርሱን ከማምለክና ከማክበር ባሻገር፣ በድነት (ደኅንነት) ሥራውም እርሱን የማምለክና የማክበር ሁኔታን ያመለክተናል። ከድነትም (ከደኅንነትም) በስቲያ በክርስቶስ በኩል ቋሚ የሆነ ግንኙነት፦ አምልኮና አገልግሎትን፣ ሁለንተናን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትን ሁሉ የሚጠቀልል ነው።

## 6. ታይፖሎጂ (Typology)

በብሉይ ኪዳን ታሪካዊ መሠረት ያላቸው እውነቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከፊተኛው ትርጓሜያቸው የማይቃረን፤ ነገር ግን፣ ተጨማሪ ትርጉም (Extended



Meaning) ይዘው የሚገለጡበትን ሁኔታ ታይፖሎጂ (Typology) ስንል እንጠራዋለን።

ለምሳሌ እስራኤላዊያን በሙሴ መሪነት ከግብፅ በወጡ ጊዜ አምላካቸው በሠራው ተኣምር የኤርትራ ባሕር ተከፍሎ ውኆች እንደ ግድግዳ ቆመውላቸው በደረቅ መሬት ላይ ተሻግረዋል። ይህ ብሉይ ኪዳናዊ እውነት ነው። ይህን እውነት የመጀመሪያውን ትርጉም ባላጠፋና ባላደበዘዙ መልኩ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲተረጉመው፣ «አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ። ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ» (1ቆሮ. 10:1-2) በማለት ያን ክስተት ከአዲስ ኪዳን የጥምቀት ትምህርት ጋር ሲያቆራኘው እንመለከታለን።

በተመሳሳይ መንገድ የአብርሃም ሕጋዊ ሚስት የምትሆነውን ሣራንና የሕግ ሚስቱ የማትሆነውን አጋርን ይወስድና ስሁለቱ ኪዳኖች ማለትም ለአዲስ ኪዳንና ለብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች ያደርጋቸዋል። ይህ እንግዲህ ታይፖሎጂ ነው። የቀደመውን ትርጓሜ ሳያጠፋ ወይም ሳያደበዝዝ አዲስ ኪዳናዊ ተጨማሪ ፍቺን የሚያስገኝ የትርጉም ዘዴ ነውና። (ገላ. 4:21-31) የቀደመውን በመንተራስ አምሳያውን የምንፈልግበት (የምናወጣበት) ነውና።

## 7. መንፈሳዊ አተረጓጉም (Spiritual Interpretation)

በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ተጨማሪ ትርጉም ማለትም መንፈሳዊ ትርጉሞች የሚሰጡ እውነታዎች አሉ። በብሉይ ኪዳን የፋሲካን በዓል ሲያከብሩ እርሾ ከሌለበት ቂጣ ይመገቡ ዘንድ ታዝዘው ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ኅብረትን ሲያስተምር፣ «በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናክብር (የቅዱሳንን ኅብረት እናድርግ) እንጂ በክፋትና በግፍ እርሾ አይደለም ይላል። የቅዱሳን ኅብረት እንደ እርሾ ሆኖ ሊያበላሸው በሚችል በክፋትና ግፍ ሊደረግ እንደማይገባ፤ ነገር ግን የቅዱሳን ኅብረት ሊመሠረትም ሆነ ሊገነባ የሚገባው በእውነትና በቅንነት ላይ እንደሆነ

ያመለክተናል:: ይህ ትርጓሜ የተገኘው በፋሲካ በዓል አከባበር ወቅት ከሚደረጉ ሥርዓቶች ውስጥ ያለን ድብቅ እውነት በማውጣት ነው፤ ከሚዳዊው ሥርዓት መንፈሳዊውን በማውጣት ነው::[24]

## 8. ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና ሥነ ጽሑፋዊ (Historical, Grammatical and Literary Interpretation) (HGL) አተረጓጐም

ይህ የትርጒም ዘዴ ከቀጥተኛ የትርጒም ዘዴ ጋር የተገናኘ ነው:: ነገር ግን፣ ከቀጥተኛ የትርጒም ዘዴ ጠለቅ ያለና ሰፋ ያለ ትርጓሜን የሚያስገኝ ዘዴ ነው::

ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንተረጉም ታሪካዊ (History) ሁኔታን፣ በጽሑፍ ውስጥ የምናገኘውን ሰዋሰው (Grammer) እንዲሁም ሥነ ጽሑፍ (Litrature) ከግምት አስገብተን ታሪካዊ ሁኔታ የሚሰጠውን ብርሃን፣ ሰዋሰው የሚሰጠንን አቀጣጫ እንዲሁም ሥነ ጽሑፉ (የሥነ ጽሑፍ ዓይነቱ) የሚሰጠንን ለትርጒም የሚሆን ቅርጽ በመጠቀም የትርጒምን ሥራ በተገቢው መንገድ እንድናከናውን የሚረዳን መሠረታዊ የሆነ የትርጒም ዘዴ ነው:: የትርጒም ሂደትን ታሪክ፣ ሰዋሰውና ሥነ ጽሑፍ ይለውጣሉ:: በትርጒምም ላይ ተጽዕኖ ያመጣሉ:: ስለዚህም፣ በቂ የሆነ ሽፋን ሊሰጣቸው ይገባል::[25]

## 9. ዐውደ ንባብን (Contextl) ማዕከል ያደረገ አተርጓጐም

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለምሳሌም ቊጥር ብቻውን ነጥለን (ቆንጽለን) ወስደን ትርጒም ለመስጠት ብንሞክር ታላቅና የከፋ ስሕተት ውስጥ እንወድቃለን:: በዚህ ፋንታ ከዚያ ቊጥር በላይም ሆነ በታች ያሉትን

[24] ዳንኤል ተሾመ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 74-77::

[25] ይህ የትርጒም ዘዴ ለሁሉም የትርጒም ዘዴዎች መነሻም ሆነ መሠረት መሆኑ መጤን ይኖርበታል:: ማርቲን ሉተር አንዱ መጽሐፍ በሌላው የሚተረጎምበትንም ሆነ አንዱ ለሌላው ምስክርነትን የሚሰጥበትን ሁኔታ በተለየ መልኩ ይረዳዋል:: ይህም እንዲህ ሊገለጥ ይችላል፤ አንዱን መጽሐፍ መተርጎም ያለብን ከሌላው ጋር እያመሳከርን ማለትም ከወንጌል ጋር እያመሳከርን ማለት ሲሆን በሌላ አነጋገር ክርስቶስን ማዕከል ባደረገ መልኩ ነው:: ወንጌልም ስንል ጽድቅ በክርስቶስ ጸጋ በእምነት ብቻ እንደሚገኝ የሚናገር ወንጌል ነው::



ቊጥሮችንም ሆነ አንቀጾችን፣ እንዳንዴም ምዕራፎችን፣ በጥቅሉም ዓውደ ንባቡን መሠረት ባደረገ መልኩ ክፍሉን መመልከት፣ ማጤንና መተርጐም ያስፈልጋል::[26]

ዐወደ ንባቡን ልብ ብለን ስንመለከት ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በውስጡ ይዞ ወይም አካቶ እናገኛለን:: ስለዚህም፣ በአንድ ቊጥር ውስጥ የተነገረ ነገረን ከእነዚህ ነገሮች ጋር አያይዘን ስንመለከተው ቁንጽል ያልሆነ፣ የተሟላና በጸሐፊው አእምሮ ውስጥ የታሰበን ነገር ለማግኘት እንችላለን:: ዐውደ ንባብ በውስጡ ከሚይዛቸው ነገሮች አንዱን በምሳሌነት መመልከት አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም፣ በጥናታችን ውስጥ ባህልን (Cultural Context) ለመዳሰስ እንሞክር ደናርብናል::[27]

## 10. ምጸታዊ አተረጓጐም (Irony)

ምጸታዊ የሆነ አነጋገርን በምጸታዊ አተረጓጐም መተርጐም ይገባል:: ምጸታዊ አነጋገር የተባለውን ነገር፣ ተቃራኒ ትርጒም የምንሸበት፣ ወይም ተናጋሪው በቀጥታ ከሚናገረው ንግግር ጐን (በስተ ግራ ወይም በስተቀኝ) ያለን ትርጒም የምንሸበት የንግገር ዓይነት ነው:: አንድ ምሳሌ ወስደን እንመለከት::

እግዚአብሔር አምላክ ለካህናት ሁለት ነገሮችን ሰጥቷል:: አንደኛው ሕዝቡን የሚያስተምሩበትን ሕግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሕዝቡን ከአምላኩ ጋር የሚያስታርቁበትን የመሥዋዕያ አገልግሎት ነው::

[26] Gordon G. Fee and Douglas Stuart, *How to read*, 45-60.

[27] አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስደን ስናጠና በዚያ ክፍል ውስጥ ባህላዊ የሆነ ነገር እናገኛለን:: በዚህ ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ተንጸባርቆ ያለው ባህል የማን ነው? ብለን መጠየቅ የመረዳት አቅማችንን ያሳድጋል:: ባህሉ የአይሁድ ነው ወይስ የግሪክ ወይስ የግሪክ ሮማን የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል:: Gordon D. Fee, *New Testament Exegesis: Revised* Edition, Westminister: John Knox,1993, p. 114. ይህን ባህላዊ ጥናት እንደሚገባ ለማኪያሄድም የአይሁድና የግሪክ ሮማንን ሥነ ጽሑፍ ማንበብ ያስፈልጋል:: 114, 117-118::

የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ሚዛናዊ ለማድረግ እነዚህን ሁለት መሣሪያዎች በእኩልነት መጠቀም አለባቸው:: ሕዝቡ ኃጢአት ሲሠራ መሥዋዕት አቅርቦ የሚያስተሰርይበትን ሥርዓት መፈጸም፣ ሕዝቡ ሁልጊዜ ኃጢአት እንዳይሠራ ሕጉን (የእግዚአብሔርን ቃል) ማስተማር ይጠበቅባቸዋል::

ሆኖም ካህናቱ የመሥዋዕት አቅርቦትንና የማስተሰረይን አገልግሎት ጠበቅ አድርገው ይዘው ሕጉን የማስተማሩን ነገር ችላ ይሉት ጀመር:: ይህም ሕዝቡ የሚያመጣውን መሥዋዕት እጅግ ያበዛው ነበር:: ይህ ደግሞ የካህናቱን ቀለብ ያበዛው ነበር:: ስለዚህም፣ ቀለባችንን እስካበዛው ድረስ ምን ገዶን በሚል መንፈስና ልብ የሕዝቡን ኃጢአት መብዛት እያዩ ዝም ይሉ ጀመር::

ካህናቱ በዚህ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን ለማሳወቅ እግዚአብሔር ምጸታዊ በሆነ አነጋገር ተናገረ:: ይህም «የሕዝቤ ኃጢአት መብል ሆኖላችኋል» (ሆሴዕ 4:8) የሚል ነበር:: ይህ እንግዲህ ኃጢአት ይበላል ማለት አይደለም:: ነገር ግን፣ የሕዝቡ ኃጢአተኛ መሆን፣ ከሚያመጣው የኃጢአት መሥዋዕት መብዛት የተነሣ፣ ካህናቱ ይህን መተዳደሪያቸውና ኑሮአቸው ሊያደርጉት ማቀዳቸውን የሚገልጥ ነው:: ስለሆነም፣ ምጸታዊ ንግግሩን ከግምት አስገብተን የመልእክቱን ትርጉም ለማግኘት ችለናል ማለት ነው::

## የትርጉም ቅኝቶች

ስለ ሥነ አፈታት (Hermenutics) ስንነጋገር፣ ከትርጉም ዘዴዎች ብዙም ባልተናነሰ መንገድ ስለ ትርጉም ቅኝቶች ማሰብ እንዲሁም ለትርጉም ቅኝቶችን የሚገባቸውን ስፍራ መስጠት ይኖርብናል:: የትርጉም ቅኝቶች ትርጉምን ሊቃኙ የሚችሉ እውነታዎች ናቸው:: የትርጉም ቅኝቶች ብዙ ቢሆኑም በርእስ ጉዳዩ ላይ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ያህል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

### 1. የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ እውነትና መልእክት



ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ እውነትም መልእክትም ነው::[28] ይህን ከራሱም ሆነ ከሌሎች አንደበት መረዳት ይቻላል:: እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንድላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፣ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው::[29] (ዮሐ. 5:39) «... ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን፣ ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው::» (ሉቃስ 2:32)

### 2. የእግዚአብሔር ዓላማ

የእግዚአብሔር ዓላማ ሁሉን በፈጠረበት በልጁ ሁሉን መጠቅለል ነው:: የዕብራውያን ጸሐፊ «ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ» ሲል ይናገራል (ዕብ. 1:1-2) ሐዋርያው ጳውሎስም ቁልጭ ባለ መስኩ የ እግዚአብሔርን ዓላማ ሲያስቀምጥልን «...በዘመን ፍጻሜም ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው::» (ኤፌ. 1:10) ይለናል::

### 3. የድነት (የደኅንነት ) መንገድ

ድነትም ሆነ መንገዱ በሥነ አፈታት ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ናቸው:: እምነት ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ለድነት ነው:: ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ነው፣ የኃጢአትን ይቅርታ ለማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ነው:: ስለዚህ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉ እውነታዎች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ስለ ድነት እንድናስብ

---

[28] ሉተር ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ሕግ፣ ታሪካዊ ጉዳዮች፣ ጸሎቶች፣ ስብከቶች፣ ትንቢቶች ወዘተ...ያሉዋቸው መሆናቸውን ቸል አላለም:: ሆኖም ሥነ መለኮታዊ በሆነ መልኩ ሲወሰድ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ዋነኛ መልእክት ወይም ይዘቱ አንድ ብቻ እርሱም ክርስቶስ እንደሆነ ይገነዘባል፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም በዚህ ረገድ ፍጹም የሆነ አንድነት እንዳላቸው ይመለከታል:: Paul Althus, *The Theology of Martin Luthr*, Tran. Robert C. Schultz, Philadelphia, 1966, p. 74.

[29] በዚህ ጥቅስ የተጠቀሱት የብሉይ ኪዳን ምስክሮች በየዘመናቸው ትንቢት ይናገሩ የነበሩ ነቢያት ናቸው:: የመሰከሩለትም ስለ ትንቢት ሁሉ ፈጻሚ ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: (ዮሐንስ ሳንድሼድ፣ *መሰከሩለት፡- የብሉይኪዳን መግቢያ ጥናት፣ መካነ ኢየሱስ የምስራች ድምፅ፡- ስማያታ* ፐሬስ፣ 1990፣ ገጽ 3::)

የሚያደርጉትንና የድነት ጥሪን የሚያስተሳልፉልን ናቸው:: ለዚህ ነው፣ «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቀመዋል» የተባለው::

#### 4. ልዩ ልዩ ገጽ የሆኑ መመሪያዎች

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ገጽ የሆኑ ቃላት፣ መመሪያዎች ወይም አሳቦች አሉ:: ከእነዚህ መካከል ጸጋ፣ እምነት፣ ፍቅር፣ ክርስቶስ፣ መንፈስ ወዘተ... ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ለምሳሌ ያህል ከልዩ ልዩ የኃይል ሥራዎች ድንቅና ተአምራት በስተጀርባ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለ፣ እንዲሁም የሰዎች እምነት እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል:: በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ያሉ ትእዛዛት ጠቅለል ባለ መልኩ ፍቅርን የሚያመለክቱ ናቸው::

የተወሰኑ ትእዛዛት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለን ግንኙነት የሚያመለክቱ ናቸው:: እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አሳብህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ፣ የሚለውን የመጀመሪያዪቱን የፍቅር ሕግ መመሪያ ያመለክተናል::

ቀሪዎቹ ትእዛዛት በሰውና በሰው መካከል ያለን ግንኙነት የሚያመለክቱ ናቸው:: ባልንጀራህን እንደ እራስህ ውደድ የሚለውን የፍቅር ትእዛዝ ወይም መመሪያ የሚያመለክቱ ናቸው::

#### 5. የወንጌሉ ምሥጢር (ዳግም ልደት)

ወንጌል ወይም የእግዚአብሔር የማደኑ የምሥራች ዜና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማዕከል ነው:: የምሥራቹ ቃል (ወንጌል) ምሥጢርነት አለው:: ይህ ምሥጢር ደግሞ የሚገለጠው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው:: ይህን የወንጌል ምሥጢር (ዳግም ልደት) ሥራ የሚያከናውነው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ቀሪውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና የእግዚአብሔርን አሳብ ለመረዳት ደግሞ ዳግም ልደት ቅድመ ሁኔታ ነው:: ዳግም ልደትን ያላገኘ ሰው በራሱ የመረዳት አቅምና እውቀት ወንጌልንም ሆነ የእግዚአብሔርን የልብ አሳብ



ሊመረምርና ሊረዳ ምሥጢሩንም ሊያውቅ አይችልም:: ስለዚህ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ብቸኛ አዳኝነት አምኖ ዳግም ልደትን ያላገኘ ሰው ከቅዱሳት መጻሕፍት የወንጌል ምሥጢርም ሆነ እግዚአብሔርን ዘላለማዊ አሳብ እንደሁም የማዳን ፕሮግራም በከፊል እንኳ ሊረዳ የማይችል መሆኑን ልናስምርበት ይገባል::

#### ሐ. ወደ ክርስትና እምነትም ሆነ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ጨለምተኛ አስተሳሰብን ይዞ መምጣት (Pessimistic Approach)

አንድ ሰው ወደ ክርስትና እምነትም ሆነ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ጨለምተኛ አስተሳሰብን ይዞ ከመጣ፣ የሚሰማውንም ሆነ የሚያየውን ነገር በአዎንታዊ መልኩ በጥራሽ ሊቀበለው አይችልም:: ሁሉንም በአሉታዊ መንገድ ነው የሚመለከተው::

ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ ሙስሊም ጸሐፊያን ምን ማለት እንኳ እንደሆነ በቅጡ የማይረዱትን እውነትና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ በጅምላና በመሰላቸው መንገድ እንደ ስሕተትም ሆነ ብርዘት ሲቆጥሩት ወይም ሲመለከቱት የሚስተዋሉት::

መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የክርስትና እምነት ተሳስቶአል፣ ተበርዞአል፣ እርስ በርሱ የሚጋጩ ነገሮች አሉበት ... ወዘተ እያልን የምናስብና በዚህ መንፈስ እምነቱንም ሆነ መጽሐፉን የምንቀርብ ከሆነ፣ የምናየውንም ሆነ የምንሰማውን ሁሉ አስቀድመን በውስጣችን ለያዝነው አቋም ማስረጃ የሚሆን ስሕተት አድረገን ነው የምንቈጥረው:: ስለዚህ የክርስትና እምነትን እንደ ክርስትና እምነትነቱ፣ መጽሐፍ ቅዱስንም እንደ መጽሐፍ ቅዱስነቱ ለመመልከት በንጹሕ ልብና በበጎ ሕሊና ልንቀርብ ይገባል::

#### መ. መጽሐፍ ቅዱስን በቁርዓን እይታ እና መስፈርትነት ለመመልከትና ለመገምገም መሞከር

ሙስሊም ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስን በቁርዓን እይታእና መስፈርትነት ለመመልከትም ሆነ ለመገምገም ሲጣጣሩ

መታዘብ ችያለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ከቁርዓን መልእክት አንጻር፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን መንገድ ቁርዓን ከተጻፈበት መንገድ አንጻር ለመመልከት፣ ከዚህም በመነሣት ትችት ለመሠንዘር ሲሞክሩ ተመልክቼያለሁ።[30]

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ መጽሐፍ መሆኑ የሚለካው በውስጡ በያዛቸው እውነቶች፣ በብዙ ትውልዶች ሕይወት ውስጥ ትንሽ በትንሽ እየተገለጠና እየሠራ ፍጹምነቱ እየተረጋገጠ በመጠበቱ በጽሑፍ በሰፈረ መገለጡ፣ ለመገለጡም ሆነ ለጽሑፉ የበዙ ትውልዶችና ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ሕያው ምስክርነት መኖር፣ እንዲሁም ዛሬም በውስጡ የያዛቸው እውነቶች የሰውን ልጅ አስተሳሰብና ባሕርይ ብሎም ተግባር የሚለወጡ በመሆኑ እንጂ፣ በአንድ ሰው ሕይወትና በ10 ዓመታት ውስጥ ተገለጠ በተባለ፣ መጻሕፍት ተጽፈው ካለቁና ከተጠናቀቁ ከ625 ዓመታት በኋላ በ10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሲያውም በታሪክ ባልተፈተሸ ሁኔታ በአንድ ሰው አማካይነት መጣ በተባለ መገለጥና መጽሐፍ አይደለም። በፊተኛው በመገለጥ ኋለኛው መገለጥ አይመረምርም። ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ያለውን ስንኳ ብንወስድ፣ በየዘመኑ የተነሡ ነቢያት የግዚአብሔር ሕዝቦችና (ብዙ ትውልዶች) የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊያን እስከ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድረስ ከዚያም አዲስ ኪዳን እስ ኪጻፍ፣ የጌታ ሐዋርያትና የእነርሱ ደቀ መዛሙርት ዘመን ድረስ ስንመለከት በሁሉም የተገለጠ እውነት ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ ሆኖ ነው የምናገኘው።

በዚህ ሂደት ውስጥ ኋለኛው በፊተኛው መገለጥ ይፈተሽ በዚህም ከፊተኛው ጋር እንደ እግዚአብሔር ቃል እየተቈጠረ ይሄድ የነበረው። እንዲህ እንዲህ እያለ የመጻሕፍት ሁሉ መዝጊያ የሆነው የዮሐንስ ራእይ ላይ ተደረሰ። መጻሕፍትም ተሟልተው ስለ ተጻፉ የራእይ መጽሐፍ ሁሉን ዘጋው። በመጻሕፍት ላይ ማንም

[30] ዶ/ር ሐሰን ኢም በፀጊል፣ *ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ ሥስተና እትም 1992፣ ገጽ 5-7።



እንዳይጨምርም ሆነ እንዳይቀንስ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጠ። (ራእይ 22:19)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ ቀድሞ የተሰጡ መገለጦች የተጻፉባቸውን መጻሕፍት ለይቶ በማስቀመጥ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍቶች አረጋግጦልናል (Canonized)። እነዚህም የሙሴ ሕግ፡- አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት የነቢያት፣ ታላላቅና ታናናሽ ነቢያት የጻፉዋቸው መጻሕፍት፣ እንዲሁም መዝሙራት ማለትም በሥነ ግጥምና በዜማ የተሰጡ መጻሕፍት በጥቅሉ 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው። (ሉቃስ 24:44)

የአዲስ ኪዳንም መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን ትምህርቶችና ትንቢታዊ ቃሎች ላይ የተመሠረቱ፣ የጻበሩና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ሥራዎችና በማንነቱ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ በተለይም በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ ከፍተኛ አጽንኦት የሚያደርጉ ሲሆኑ፣ በትንቢታዊነታቸው ካልሆነ በቀር በመሠረታዊ ይዘታቸው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር እጅ ለእጅ የሚያያዙ፣ አንዱ የሌላውን አሳብ የሚደግፍና የሚያብራራ እንደሆነ ግልጥ ነው።[31]

ታዲያ መጻሕፍት ሁሉ ተጽፈው ካበቁና የጽሑፉ ሂደት ከተጠቃለለ በኋላ፣ በተለይም እግዚአብሔር በክርስቶስ በሙላት ከተገለጠና የክርስቶስ ደቀ መዛመርቶች ይህን የመለኮት ምላተ መገለጥ (ቈላ. 2:8) ከዘገቡና ከጨረሱ በኋላ፤ ሁሉም ከተዘጋ በኋላ ከብሉያትም ሆነ ከአዲሳት ጋር የማይገጥም መገለጥ ይዞ የመጣ ሰውና መገለጡ በብሉያትና በአዲሳት ሲፈተሽ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከነቢያት አምላክ ከእግዚአብሔር እንዳልወጣ የተረጋገጠ መገለጥ እንዴት ተቀባይነት ሲያገኝ ይችላል? ከዚህም አልፎ እንዴት የመገለጦች ሁሉ መፈተሻ ሲሆን ይችላል? ከብሉያትና ከአዲሳት በኋላ የመጣ ስለሆነ

[31] በሐዋርያት ስለ ክርስቶስ መድኃኒትነት ሲያስረዱን ሁል ጊዜ ብሉይ ኪዳንን መሠረት በማድረግ ነው። ነቢያት ሁሉ ስለ እርሱ ተናግረዋልና ከድንግል በመወለዱ፣ የሰውን ችግር ተካፋይ በመሆኑ፣ ስለ ሰው ኃጢአት መከራን በመቀበሉ፣ ከሙታን በመነሣቱ የተነገሩለት የተስፋ ቃላት በሙሉ ፍጻሜ አግኝተዋል የሚለውን አሳብ በየመልእክታቸው ተደጋግሞ እናገኘዋለን። ዮሐንስ ሳንድቤድ፣ *መሰክሩለት*፣ ገጽ 7-8።

የብሉያትም ሆነ የአዲሳት መመዘኛ መስፈርት ክቶ ሊሆን አይችልም፣ ይህ የሕልም እንጀራ ነውና!!

**ሠ. በስሜታዊነትና በወገናዊነት መንፈስ ደግሞም ሥነ ትምህርትን ማዕከል ባላደረገ መልኩ ለትችት መነሣት::**

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት የሚነሣ ሰው ቢያንስ ቢያንስ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሚዛናዊ የሆነና በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: የሚያነሣቸውን ነጥቦች በስሜት ሳይሆን በሥነ ትምህርታዊ (Academic) ገጽታቸው ማየት የሚችል መሆን አለበት::

በተመሳሳይ መልኩ ለትችት የሚነሣ ሰው ከዘረኝነት ወይም ከወገናዊነት አስተሳሰብ የጸዳ መሆን አለበት:: ሙስሊም ጸሐፊያን የክርስትናን እምነት ወይም የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክትና አገልግሎት ለእስራኤላውያን ብቻ የመጣ እንደሆነ፣ ነገር ግን ለመላው ዓለም የመጣ መልእክት የመሃመድ መልእክትና አገልግሎት እንደሆነ አድርገው ለመመልከት ሲጣጣሩ ተመልክቼያለሁ:: አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንም ከዐውደ ንባባቸውና ከጸሐፊው አሳብ ውጭ እየቆነጸሉ በመውሰድ ሲጠቃቅሱ ተመልክቼያለሁ::[32]

«ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ» ማቴ. 15:24 «ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ::»

እነዚህን የመሳሰሉ ክፍሎችን ብቻ ከወሰድናቸው የኢየሱስና የደቀ መዛሙቶቹ አገልግሎት ለአይሁድ (ቤተ እስራኤል) ብቻ እንደሆነ፣ ልናስብም ሆነ ልንደመድም እንችላለን:: ነገር ግን፣ ጥቅሶቹን በዐውደ ንባባቸው፣ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ (በኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮና አገልግሎት) መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ግንዛቤ፣ እንዲሁም የጸሐፊውንና የጸሐፊዎቹን አሳብ (Authorial Intention) ከግምት አስገብተን ስንተረጉም ከዚህ የተለየ ትርጉምን እናገኛለን:: ይህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎትና ተልዕኮ የሚጀምረው

[32] አቡ ሱመያ፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997፣ ገጽ 40-47::



በአይሁድ ሕዝቦች እንደሆነ ያመለክተናል፣ እንጂ በአይሁድ ሕዝቦች ላይ ብቻ ያተኮረና የተገደበ እንዳልሆነ ያመለክተናል:: ከአይሁድ ጀምሮ ወደ አሕዛብ ሁሉ እንደሚሄድ ያመለክተናል::

ለዚህ እንደ ማስረጃ አድርጌ የማቀርበው ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተልዕኮና አገልግሎት ሌሎች የመጽሐፍ ቅድስ ክፍሎች የሚናገሩትን ሚዛን አስጠባቂ እውነታዎች በመጥቀስ ነው::

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ፣ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ::» (የሐዋ. 1:8)

«ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡- እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው :: እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::» (ማቴ. 28:18-20)

«እንዲህም አላቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ::» (ማር. 16:15)

«ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር:: በዓለም ነበር:: ዓለሙም በእርሱ ሆነ ዓለሙም አላወቀውም:: የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም:: ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው::» (ዮሐ. 1:9-12)

> «እንዲህም አላቸው ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል:: በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ **ሁሉ** ይሰበካል ተብሎ እንደሁ ተጽፎአል:: እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ::» (ሉቃስ 24:46-48)

የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት በአይሁድ ሕዝቦች መካከል ተጀምሮአል:: ትምህርቱ ሥራውና ምሳሌነቱ በሙሉ ተሰጥቷል:: ስለ ሰው ልጆችም የኃጢአት ስርየት በመስቀል ላይ ሞቷል:: ይህ ሁሉ በአይሁድ ሕዝብ መካከል የተከናውነ ጉዳይ ነው::

ይህ እንግዲህ የሚያሳየን አገልግሎቱ በአይሁድ ሕዝብ መካከል እንደ ጀመረ እንጂ፣ አገልግሎቱ ለአይሁድ ሕዝቦች ብቻ የሆነና የተገደበ እንዳልነበረ ነው:: ከላይ ለምሳሌነት የወሰድኳቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንደሚከተለው በመተንተን ለማሳየት እሞክራለሁ:: የሐዋ. 1:8 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት በሐዋርያቱና በደቀ መዛሙርቱ አገልግሎት በኩል የሚቀጥል መሆኑን ይህም ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ወደ ይሁዳ ከዚያም ወደ ሰማርያ እንደሚቀጥልና በመጨረሻም እስከ ዓለም ዳርቻ እንደሚዘልቅ ያመለክተናል::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በምንመለከትበት ጊዜ የጌታ ደቀ መዛሙርት የወንጌል ስብከትን ሥራ ከኢየሩሳሌም እንደ ጀመሩ የሐዋ. 2፣ በመቀጠልም፣ ወደ ይሁዳ እንደ ሄዱ (የሐዋ. 8:1) ከዚያም ወደ ሰማርያ እንዳቀኑ (የሐዋ. 8:1) በመጨረሻም፣ ወደ ቀሪው ዓለም እንደ ተጓዙና ወንጌል (የሐዋ. 9:31) እንደ ሰበኩ እንመለከታለን::

የማቴዎስ ወንጌል 28:18-20 ስንመለከት ሐዋርያት ወንጌልን ወደ አሕዛብ ሁሉ ይዘው እንዲሄዱ በማጥመቅና በማስተማር አሕዛብን ለክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር (ተከታዮች) እንዲያደርጉ ማዘዙን (Commessioned)፣ ያመለክተናል:: በተጨማሪም፣ ጌታ ኢየሱስ ይህን የወንጌል ሥራ በሚያከናውኑበት ጊዜ ሁሉ ማለትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከወንጌል ሠራተኞች እንደማይለይም ሆነ አብሮአቸው እንደሚገኝ ተስፋ ሰጥቷቸዋል:: ይህም ተስፋ መፈጸሙን የሚያመለክቱ በቂ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ:: ጌታ ኢየሱስ ከወንጌል ሠራተኞች ሳይለይ አብሮአቸው እንደነበርና እንዳጸናቸው፣ እንዲሁም እንዳበረታቸው እንመለከታለን::



«በፊተኛው ሙግቴ አንድ ስንኳ አልደረሰልኝም:: ሁሉም ተዉኝ እንጂ፣ ይህንም አይቍጠርባቸው ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ:: ከአንበሳ አፍም ዳንሁ» (2ኛ ጢሞ. 4:16-17)

«...ሳውል ሳውል ሆይ ስለምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ፣ ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ? አለው:: አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስሃል አለው::» (የሐዋ. 9:4-5)

በአሕዛብ መካከል የተተከሉትን ታላላቆቹን ሰባቱን የእስያ አብያተ ክርስቲያናትም ሕይወት ጌታ ኢየሱስ ይመለከት እንደ ነበረ፣ በአንድ በኩል ብርቱ የሆነውን ጐናቸውን አስመልክቶ እያደነቀ ሲያበረታታቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ደካማ የሆነ ጐናቸውን እየነቀፈ ይህን እንዲያስተካክሉ ንስሐም እንዲገቡ ይጠይቃቸው እንደ ነበረ፣ በዚህም አጠቃላይ ያሉበትን ሕይወት እያሳየና ወደፊት በየትኛው መንገድ መመላለስ እንዳለባቸው ምሪት እየሰጠ አብሮአቸው የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጠላቸዋል (ራእይ 2-3)::

ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል በማለት ከምዕራፍ 2-3 ላይ ለሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት፦ ለኤፌሶን፣ ለሰምርኔስ፣ ጴርጋሞን፣ ትያጥሮን፣ ሰርዴስ፣ ፊልድልፍያ፣ ሎዶቅያ የሚናገረው በመካከላችን መመላለሱና መገኘቱ እሙን መሆኑን ያረጋገጠው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በመቀጠልም፣ በመጽሐፉ መዝጊያ አካባቢ ይህ ጌታ፣ «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ::

አልፋና ኦሜጋ ፊተኛው ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ .... እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ

መልአኬን ላክሁ፣ እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።» (ራእይ 22:12-13፤16) በማለት እርሱ ከምእመናን ሁሉ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሁሉ ጋር እንዳለና፤ ሁሉን እንደሚመለከት፣ ሊፈርድም እንደሚመጣ ሲያስታውቃቸው እንመለከታለን።

እንደ ሉቃስ 24:46-48 እና ዮሐ. 1:9-12 ያሉት ክፍሎችም እንደ ቀደም ተከተላቸው የሚከተሉትን አሳቦች ያስጨብጡናል። ክርስቶስ መከራ እንደሚቀበል፣ እንደሚሞትና በሦስተኛውም ቀን ከሙታን እንደሚነሣ በመጨረሻም፣ በስሙ ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ እንደሚሰበክ በቅድሚያ ስንመለከት፣ በመቀጠል ደግሞ፣ ምንም እንኳ ክርስቶስ በአይሁድ ሕዝቦች መካከል የተመላለሰና ያገለገለ ቢሆንም እርሱ ወደ ዓለም ሁሉ የሚመጣ (የመጣ) ብርሃን እንደ ነበር፣ የገዛ ወገኖቹ ባይቀበሉትም ለተቀበሉትና በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣንን እንደ ሰጣቸው እንመለከታለን። ይህም ክርስቶስ ወደ ዓለም ሁሉ የመጣ የዓለም ብርሃን መሆኑን ያረጋግጥልናል።

ስለሆነም፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ለአይሁድ ሕዝቦች ብቻ የተወሰነ እንዳልነበረ፣ ነገር ግን አገልግሎቱ ከአይሁድ እንደ ጀመረ፣ በመቀጠልም፣ ወደ ሕዝቦች ሁሉ እንደ ደረሰ ከእግዚአብሔር ቃል በስፋት መመልከት የምንችል የመሆኑን እውነታ አጽንኦት ልንሰጠውና ልናሰምርበት እንደሚያስፈልግ ላሳስብ እእወዳለሁ።

ከዚህም ጋር በተያያዘ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ከአይሁዶች ይጀምር፣ በእነርሱም ላይ ያተኩር እንጂ፣ ሌሎችን ያካተተ መሆኑን ልብ ልንል የምንችልበትን እውነታ ከዚህ በታች ባለው ሥዕል እንደሚከተለው አሳያለሁ።



| | |
|---|---|
| ለአይሁድ ሁሉ (ማቴ. 15:24) | ለአሕዛብ (የአሕዛብ ከተሞች-ገሊላ፣ ዛብሎንና ንፍታሌም)-ማቴ. 4:12-16፤ ማቴ. 15:21-28፤ ማቴ. 9:18-26 |

## የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት

ለሳምራውያን (በከፊል አይሁድና በከፊል ሳምራውያን ለሆኑ ሕዝቦች)
ዮሐ. 4 እና የሐዋ. 8

መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ ብዙ ሕዝቦችን እናገኛለን። ለምሳሌም ያህል አሞራውያን፣ ኢያቡሳውያን፣ ጌርጌሳውያን ኤውያውያን፣ ኬጢያውያን፣ ከነአናውያን፣ ፌርዛውያን ግብፃውያን (ዘጸ. 3:8) አማሌቃውያን፣ ሞዓባውያን፣ እስራኤላውያን፣ ፍልስጥኤማውያን (ዘጸ. 3:8) ምድያማውያን ... ወዘተ ተጠቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ።

እግዚአብሔር አምላክ፣ «ከሴቲቱ የሚወለደው ራስህን ይቀጠቅጣል» (ዘፍ. 3:15) የሚል የተስፋ ቃልን በእባብ ተንኮል (በሰይጣን ማሳት) ምክንያት ለወደቁ ሰዎች ስለ ሰጠ፣ ይህን የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ነበር አብርሃምን

አብራም ተብሎ ከሚጠራበት ከከለዳዊያን ዑር ጣዖት አምላኪያን ከሆኑ ሕዝቦች መካከል የጠራው፣ ሕዝብ ያደረገው፣ አዎን ይህን ተስፋውን ለመፈጸም እስራኤልን ከእርሱ (በእርሱ በኩል) ያመጣው።

ብዙዎቻችን የእስራኤል መጠራትና መመረጥ እንደሁም የአብርሃም መጠራትና መመረጥ ምሥጢሩ አይገባንም። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ የራሱ ለማድረግና (በድነት) ፕሮግራሙ ውስጥ ለማካተት፣ እንዲሁም ሌሎችን ለመተው የሚፈልግ እንደሆነ እናስባን።

እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። አብርሃምን ሲጠራው አብርሃምንና የእርሱ ዘሮችን ብቻ ሊባርክ ሳይሆን፣ «የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» (ዘፍ. 12:3) እንደ ተባለለት በምድር ላይ ላሉ ልዩ ልዩ ነገዶች (በዘመናችን አጠራር ደግሞ ብሔር ብሔረሰቦች) ሁሉ የመዳኛ ምክንያትና መንገድ ሊያደርገው ነው። ከእርሱ አባትነት የተነሣ (በአባትነቱ ውስጥ) የሚመጣ ወይም የሚገለጥ ድነት አለና።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «በአንተ ወይም በእርሱ» የሚለው ቃል በውስጡ ነጠላ እንጂ፣ የብዙ ቁጥርን ያልተሸከመ ስለሆነ ከአብርሃም ዘር ስለሚመጣና ትኩረትን ሁሉ ሊወስድ ስለሚገባው መሢሕ የሚናገር መሆኑን፣ በትምህርቱ በሰፊው ገልጦታል። ይህም፣ «ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚናገር ለዘሮቹም አይልም። ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፦ ለዘርህም ይላል እርሱም ክርስቶስ» (ገላ. 3:16) በሚል ቃል ተቀምጦልናል።

ስለዚህ፣ አብርሃምና ዘሮቹ በተለይም እንደ ሕዝብ የተመሠረተችው እስራኤል ለዓለም ብርሃንን (የአንድ አምላክ መኖርንና የእርሱንም ፍጹም የሆነ ፈቃድ) ሲፈነጥቁ ኖረዋል። ነቢያቶቻቸውም አልፎ አልፎም ቢሆን እንደ ነነዌ ያሉ የአሕዛብ ከተሞችን በእግዚአብሔር ቃልና በትንቢታዊ መልእክት ማገልገላቸው ይታወሳል (ትንቢተ ዮናስን ተመልከት)።



ይህ እንግዲህ፣ በአንዱ ሌላውን የመድረስ መለኮዊ አሠራር ነው።

ነገር ግን፣ ብዙዎች ይህንን እውነትና ብርሃን ከእስራኤል በመቀበል ፈንታ የራሳቸውን የጣዖት (የብዙ አማልክት) አምልኮ በመምረጣቸውና በመከተላቸው የብርሃኑ ተጠቃሚ ካለመሆናቸውም በላይ የብርሃኑ ጠላቶች ሆነው ተመላልሰዋል።

ይህ እውነትም መገለጥ ስለ ነበረበት ብዙ ሕዝቦች የእግዚአብሔር ሕዝብ (እስራኤል) ጠላቶች ሆነው የተመላለሱበት ሁኔታ፣ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረጉት ውጊያ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ በዚያን ጊዜ ከነበሩ ሕዝቦችና መንግሥት ጋር ያደረጉዋቸው ውጊያዎች ሁሉ ተጽፈው ይገኛሉ። ከእነዚህ ሕዝቦች መካከል እስከ ዛሬ ድረስ ስማቸውን እንኳ ሳይለቁ የኖሩ ሕዝቦች አሉ፤ ዋነኛ ምሳሌም አድርገን ለዚህ የምንጠቅሰው ፍልስጥኤማውያንንና ግብፃዊያንን ነው። በእስራኤላውያንና በፍልስጥኤማውያን መካከል እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቀ ጦርነት መኖሩ ግልጥ ነው፤ ከግብጻውያንም ጋር ቢሆን እስከ ስድስቱ ቀን ጦርነት ድረስ የቀጠለ ፍልሚያ መኖሩ እሙን ነው።

የእስልምና ሃይማኖት በብዙ የዓረብ አገሮች የተስፋፋ በመሆኑ እንዲሁም ግብፅ ወደ ዓረቡ ዓለም በሃይማኖትም ሆነ በዝርያነት የምታዘነብል ስለሆነች፣ ብዙዎች እስራኤልን ከግብፅም ሆነ ከፍልስጥኤም እንዲሁም ከሌሎች የዓረብ አገሮች ጋር ባካሄደቻቸው ጦርነቶች ምክንያት ይጠሏታል። ብሉይ ኪዳን ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን የእስራኤልን ጠላቶች ሽንፈትና ውድቀት በስፋት ያስተምራል። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ሙስሊም ጸሐፊያን የብሉይ ኪዳን እውነቶችን በጥርጣሬ የማየት፣ ተበርዟል የማለት፣ እንዲሁም በጽናት የመጥላትና እውነታዎችን ከወገንተኝነትና ከዘረኝነት አስተሳሰብ ነጥለው ማየት ሲሳናቸው ይስተዋላል።[33]

[33] ከወገንተኝነት አስተሳሰብ አለመፅዳት ስማያዊን እውነት ቀርቶ ምድራዊ እውነታን እንኳ የሚከለክል መሆኑ ለሁላችን ግልጥ መሆኑ አያጠያይቅም።

በእኔ እምነት ለእንደዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሔ ሲሆን የሚችለው የእግዚአብሔርን ትልቅ ዕቅድ ማለትም በአንዱ በአብርሃም በኩል በተገለጠችው እስራኤል በኩል መሚሑን ጌታ ክርስቶስን ማምጣትና በእርሱ ድነትን መሥራትም፣ ከዚያም ይህን ድነት መቀበል የምንችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ይህን ከተረዳን የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እውነቶች ያለ ምንም ችግር መቀበልም ሆነ ማጣጣም እንችላለን። የእግዚአብሔር አሳብ እስራኤልን ብቻ የማዳን ሳይሆን፣ ሁሉን ሕዝቡ ለማድረግ አንዱን ወገን መንገድ አድርጎ እንደሆነ ማሰብ ተገቢ ነው።

## II. ሙስሊም ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብቡ የሚያነሡዋቸው ጥያቄዎችና የሚቸገሩባቸው ጉዳዮች

ሙስሊም ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብቡ ግራ የሚጋቡባቸውም ሆነ ጥያቄ እንዲፈጥርባቸው የሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች አሉ። የአብርሃም በረከት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ ዓለም ሁሉ ስለ ደረሰ በአሁኑ በአዲስ ኪዳን፣ እምነት በዝርያ ወይም በወገን ላይ ሳይሆን፣ በሞቱና በትንሣኤው በሰዎችመካከል ያለን ጠላትነት አስወግዶ አንድ ባደረገን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ፣ ክርስትናን እንደ ዓለም አቀፋዊ የዳኑ ሰዎች ኅብረት እንጂ፣ እንደ ዘረኝነትና ወገናዊነት ማራመጃ ሃይማኖትም ሆነ ኅብረት አድርገን ልንቈጥረው አይገባንም።

### ሀ. የሥላሴ ትምህርት

እግዚአብሔር አምላክ ራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ማለትም ዘላለማዊ በሆነው የሥልጣን ቃሉ አማካይነት ሲገልጥ፣ በመለኮት አንድ ደግሞም በአካል ሦስት አድርጎ ነው። ይህ መለኮታዊ አንድነትና አካላዊ ሦስትነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ላይ የምናገኘው እውነት ነው። እግዚአብሔር የሚለው ቃል በጥቅሉ መለኮታዊ አንድነትን ያመለክተናል። አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም ደግሞ አካላዊ ሦስትነትን ያመለክተናል



(ዮሐ. 4:24፣ ዮሐ. 15:26-27፣ ዮሐ. 14:9-11፣ 2ቆሮ. 13:14፣ ማቴ. 28:20፣ ዘዳ. 6:4)። ሙስሊሞች የሥላሴን ትምህርት በዚህ መልኩ ሊረዱት ስለማይሞክሩ፡- ስለማይፈልጉም ሆነ ስለማይችሉ ግራ መጋባት ውስጥ ይገባሉ።[34]

እነርሱ የሚመስላቸው ወይም ነገሩን የሚረዱት በሁለት መልኩ ነው።

1. በአንድ መለኮት ፋንታ ሦስት መለኮት እንዳለ አድርገው፡- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት አማልክት መስለው ይታዩአቸዋል።

2. ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን ውልደት ከማርያምና ከአምላክ ግንኙነት የመጣ አድርገው የሚያስቡና የሚያስተምሩ ስለሚመስላቸው፣ ከዚህ በመነሣት ሦስቱ አማልክት እግዚአብሔር፣ ማርያምና፣ ኢየሱስ እንደሆኑ አድረገው ነው የሚቈጥሩት። ይህ ነው ስለ ሥላሴ ያላቸው ግንዛቤ፤ ይህ መረዳት ፈጽሞ የተሳሳተ ነው። ክርስትና እንደዚህ ዓይነት ትምህርት ከቶ አያስተምርም።

ነገር ግን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አምላክ አንድ እንደሆነ፣ ሆኖም በሦስት አካል ያለ፣ የሚኖርና የሚገለጥ እንደሆነ አድርጎ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ራሱን በአንድ መለኮትና በሦስት አካል እስከገለጠ ድረስ ይህን መቀበል የአማኝ ግዴታ ነው። እርሱን በእርሱም ልክ ሆነ ከእርሱ በላይ በሆነ መንገድ ማንም ሊገልጠው አይችልምና።

በእስልምናና በክርስትና መካከል ያለው አንድነት ሁለቱም አንድ መለኮት እንዳለ ማመናቸው (መቀበላቸው) ሲሆን፣ ልዩነ ታቸው ደግሞ አንዱ መለኮት በስንት አካል ነው ያለው? የሚኖረው? ወይም ራሱን የገለጠው? የሚለው ላይ ነው።

[34] ዶ/ር ማንህ ሐማድ አልጀሃይኒ፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ፣ አዲስ አበባ፣ ሁዳ ፕሬስ፣ 1994 ገጽ. 11.

ትልቁና ዋነኛው ቁምነገር በአንድ መለኮት መኖር ማመን ነው፡፡ ይህን እውነት መቀበል ነው፡፡ እንግዲህ እውነቱ ይሄ ከሆነ አንዱ ሌላውን በብዙ አማልክት ታምናለህ ብሎ መክሰስ ወይም መወንጀል የለበትም፡፡

ነገር ግን አንድ ነገር ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ይህም የእስልምናው አምላክ በመለኮት ብቻ ሳይሆን፣ በአካልም ጭምር አንድ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የክርስትናው አምላክ በመለኮት ብቻ አንድ ሲሆን፣ በአካል ደግሞ ሦስት ነው፦ አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፡፡ ስለሆነም፣ የክርስትናው አምላክ ከእስልምናው አምላክ የተለየ ነው፣ ወይም በእስልምናና በክርስትና መካከል ያለ የአንድ መለኮት አናኗርም ሆነ መገለጥ ለየቅል ነው ማለት ነው የምንችለው፡፡

ለዚህም ነው የክርስትናው አምላክ መገለጥ (መጽሐፍ ቅዱስና) የእስልምናው አምላክ መገለጥ (ቁርዓን) ሊለያዩ የቻሉት፡፡ ስለሆነም፣ ክርስቲያኖች ያላቸው የመለኮት ማንነት መረዳት ሊለካ፣ ሊፈተሽም ሆነ ሊታይ የሚገባው በቁርዓን መነጽርነት ሳይሆን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ብቻ በመመሥረት ነው፡፡

ስለዚህም፣ ሙስሊም ጸሐፊያንን በቁርዓን አምላካዊ መግለጫና ትምህርት ላይ ተመሥርተው ስለ ሥላሴ ሦስት መለኮትነት እንዲሁም ስለ ክርስትናእምነት በሦስት አማልክት ማመን የሚያስተምሩት ትምህርት መሠረተ ቢስ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም፣ የክርስትና እምነት በእራሱ መገለጥ (መጽሐፍ ቅዱስ) ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ የሚለካውም በዚሁ መገለጥ ትምህርቶች ብቻ ላይ በመመሥረት ስለሆነ ነው፡፡

ለ. የክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች፦ መጽሐፍ ቅዱሳችንን በምናጠናበት ጊዜ ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች የምንማራቸውና የምንረዳቸው ትምህርቶች አሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት



ሲያስተምረን የሚከተሉትን እውነታዎች ይነግረናል፡፡

1. እርሱ ፍጹም ሰው እንደሆነ፣
2. እርሱ ፍጹም አምላክ እንደሆነ (ቈላ. 2:9፤ 1ዮሐ. 5:20፤ ሉቃስ 5:20)፣
3. እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ (ዮሐ. 3:17 35፤ 1ዮሐ. 5:20-21)፣
4. በሰውነቱ ከአብ እንደሚያንስ፣ ነገር ግን፣ በአምላክነቱ ከአብ ጋር እኩል እንደሆነ ያስተምረናል፡፡(ዮሐ. 14:28፤ 1ቆሮ. 15:27-28 ፊል. 2:6፤ 1ዮሐ. 5:20-21)፣

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራዎች ሲያስተምረን የሚከተሉትን እውነታዎች ይነግረናል፡፡

i. ወደዚህ ዓለም የመጣው የጠፉትን የሰው ልጆች ሊፈልግና ሊያድን እንደሆነ (ዮሐ. 3:17 1ጢሞቴ. 1:15)፣

ii. የኃጢአታችንን ዋጋ በመስቀል ላይ በመሞት ከፍሎ በደሙ ነፃ ሊያወጣን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን መሆኑን (2 ቆሮ. 5 :18-19 ሮሜ. 5:8-11)፣

iii. በመስቀል ላይ ስለ እኛ ሞቶ ያፈሰሰው ደሙ ከኃጢአት ሁሉ ነፃ እንደሚያወጣ (1ዮሐ. 1:7 የሐዋ. 20:28 ዕብ. 10:19-20)፣

iv. መዳን የሚቻለው በእርሱ በማመን፣ ለእኛ የሠራውን የድነት ሥራ አምኖ በመቀበል ብቻ እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ (ዮሐ. 3:16-17 ሮሜ. 3:22-24)፡፡

ምንም እንኳ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስና ስለ ሥራዎቹ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን ትምህርቶች የሚያስተምር ቢሆንም፣ ሙስሊም ጸሐፊያን ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ወደ ጐን ጥለው፣ በምትኩ

ስለ ማንነቱም ሆነ ስለ ሥራዎቹ ሌላ የራሳቸውን ትምህርቶች ያስተምራሉ።

ፍጹም ሰውነቱን (ኃጢአት የሌለበት መሆኑን)፣ በአወላለዱ ከሌሎች ሰዎች የተለየ ከመሆኑ በቀር እንደማንኛውም ሰው፣ ሰው ብቻ መሆኑን ተቀብለው፣ መለኮታዊነቱን፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ከአብ ጋር እኩል የመሆኑን እውነት ያስተባብላሉ ወይም ይክዳሉ።

ሁለት መለኮት ሊኖር አይችልም፤ አምላክ አይወልድም አይወለድም፣ አምላክን የሚስተካከለው የለም ይላሉ። ወደዚህ ዓለም የመጣው ነቢይ ሆኖ እንደ ማንኛውም ነቢይ እስልምናን ለማስተማር ነው ይላሉ። እስልምና ከመሃመድ በፊት የተፈጠረ ይመስል ምን ከመሃመድ ብቻ ከአይሁድ እምነትና ክርስትና እምነት ቀድሞ የተፈጠረ ይመስል፣ የፈጣሪን መንገድ ወይም እስልምናን አስተምሮአል ይላሉ።

እርሱ አልሞተም በእርሱ ፈንታ ሌላ ነው የሞተው ይላሉ። ማንም ማንንም አያድንም፤ ሰው የሚድነው የአምላክን ትእዛዛት በመጠበቅ በመልካም ሥራው መብዛት ነው ይላሉ። በጥቅሉ የኢየሱስን ማንነት በፍጹም ሰውነቱ ብቻ፣ ደግሞም ሥራውን በነቢይነቱ ብቻ ይወስኑታል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራዎች፣ ትምህርቶቹና ስለ ራሱ ማንነት የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ የተጻፉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። የእስልምና ሃይማኖት የተነሣው በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ነው። የእስልምና ሃይማኖት ቁርዓን ለኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች፣ ለማንነቱ፣ ለሠራቸው ሥራዎች፣ ስለ ማንነቱ ለተናገራቸው ነገሮች ሁሉ የተሟላም ሆነ በቂና የቅርብ ጊዜ ምስክር ሊሆን አይችልም።

የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ግን በብዙ መልኩ ብቁና የተሟሉ ወቅታዊ ምስክሮች መሆናቸው የተረጋገጠ ነው።



1. በእርሱ ተከታዮች ከዕርገቱ በኋላ ባሉት ከ20 - 65 ዓ.ም ዓመታት ማለትም ከ55 ዓ.ም እስከ 90 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት የተጻፉ ናቸው።

2. በአንድ ሰው ሳይሆን በተለያዩ ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍት ስለሆኑ ከአንድ በላይ የሆኑ ብዙ ምስክሮች አሉት።

3. እነዚህ ጸሐፊያን አንዱን እውነት ከተለያዩ ገጽታዎቹ ጋር የጻፉ ስለሆነ፤ ሙሉ ገጽታ ባለው መልኩ ማንነቱንም ሆነ ሥራውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በማያሻማ መልኩ ያቀርቡልናል። በተጨማሪም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በቀጥታ ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ (የሚያሳዩ) ስለሆኑ፣ ከቁርዓን ይልቅ የተሻለና የበለጠ መረጃ በጉዳዩ ላይ አላቸው።

ወደ ቁርዓን ስንመለስ ግን፦

1. በክርስቶስ ተከታይ የተጻፈ መጽሐፍ አይደለም። በዚያ ላይ እንደ ወንጌላት ከዕርገቱ እስከ 100 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት፣ ማለትም ወዲያው የተጻፈ መጽሐፍ አይደለም። ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ከ610-620 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዓመታትና ከዚያም በጥቂት ዓመታት ዘግይቶ የተጻፈ ነው። ስለዚህም፣ የተሟላ መረጃ የለውም።

2. በአንድ ሰው የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ ለትክክለኛነቱ ሌላ የምናመሰክረው መጽሐፍ ስለሌለ ብቻውን ለምስክርነት አይበቃም።

3. ስለ ክርስቶስ ማንነትና ስለ ሥራው የተወሰኑ ገጽታዎቹን ብቻ ነው የሚያሳየን።

4. ቁርዓን ስለ ኢየሱስ ማለትም የተወሰኑ ገጽታዎቹን በተመለከተ የሚነግረን ነገር ቢኖርም፣ በቀጥታ ስለ ኢየሱስ ማንነትና ስለ ሥራው ሊያስተምር የተጻፈ መጽሐፍ አለመሆኑ ግልጥ ነው።

ስናጠቃልለውም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን ሙሉ ገጽታ ማለትም ሰውነቱንም ሆነ መለኮታዊነቱን እንዲሁም አስተማሪና ነቢያዊ ገጽታውንም ሆነ መሥዋዕትነቱንና አዳኝነቱን ሁሉ በሙላት ስለሚያስተምር፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትም ሆነ ሥራዎች በቀጥታ የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ፣ በብዙ ምስክሮችም የተጻፈና የታመነ መጽሐፍ ስለሆነ ስለ እርሱ ማወቅ የሚፈልግ ሰው በቀጥታ ስለ እርሱ የተሟላ እውነትን ወደሚያስጨብጠው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መምጣት አለበት:: ስለ ክርስቶስ የሆነውን ትምህርት (Christology) በሙላት ማግኘት የሚቻለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና::

ስለ አንድ ነገር እግረ መንገዱን ከሚናገር መጽሐፍ የተሟላ መረጃ እንደማይገኝ ያመነ (ያወቀ) ሰው፣ ስለ ጉዳዩ በሙላት የሚናገረውን መጽሐፍ እንደ ዋና የመረጃ ምንጭ እንደሚቆጥረው ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው::

### ሐ. ሊቀበሉዋቸው የሚከብዱ እውነታዎች (ጉዳዮች)

መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነብቡ ጊዜ፣ አንዳንድ ሙስሊም ወንድሞቻችን ሊቀበሉዋቸው የሚከብዱአቸው ብዙ ነገሮች ይገጥሙአቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስን በመተቸት ከጸሃፊዎቻቸው መጻሕፍት ውስጥ ሊቀበሉት የቸገራቸውን፣ ከዚህም በመነሣት መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የሚጋጩ ነገሮች አለበት፣ ተበርዟአል እንዲሁም ብዙ ስሕተቶች አሉበት ወደሚል መደምደሚያ የደረሱባቸውን ነገሮች ለጥሳሌነት ያህል ጥቂቶቹን ወስደን እንመለከታለን::

መለኮታዊ ተአምራትን እንዲሁም ታሪካዊ ክንዋኔዎችን ለመቀበል መቸገር፣ እግዚአብሔር እንዴት በዚህ መንገድ ውስጥ ሊሠራ ይችላል? እጅግ አስደናቂና አእምሮ ሊቀበላቸው የማይችልን ነገሮች በውስጡ ማቀፉ :- በሚል ርእስ ሥር ሳዲቅ መሃመድ አህመድ የተባሉ ጸሐፊ፣ «ላለመደናገር ማመሳከር» በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ የሚከተሉትን ድንቅና ተአምራት እንዲሁም ታሪካዊ ክስተቶች የማይቀበሉና የሚጠይቁ መሆናቸውን፣ ከእነዚህ ነገሮችም የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስ



ከጊዜ በኋላ የሰው እጅ ገብቶበታል ብለው እንደሚያምኑ ያስታውቃሉ::[35]

#### ተአምራት

1. ያዕቆብ በተላጠ በትር አማካይነት በጎቹን ያስጐመጀበትና በዚህም በጉቹ ሽመልመሌ መሳይና ዝንጉርጉር ነቍጣም ያለባቸው ግልገሎችን የወለዱበትን ተአምርን (ዘፍ. 30:37-39)፣

2. የበለዓም አህያ በሰው ቋንቋ በለዓምን የገሠጸችበትን ተአምር (ዘፍ. 22:28-30)፣

3. ሶምሶን 300 ቀበሮች የያዘበትና የፍልስጥኤማውያንን እርሻ ያቃጠለበት ተአምርን (መሳ. 15:1-5)፣

4. ሶምሶን በአህያ መንጋጋ 1000 ሰዎችን የገደለበትን ተአምር (መሳ. 15:14-15)፣

#### ታሪካዊ ክንዋኔዎች

5. ዳዊት የሳኦልን ልጅ ሜልኮልን ለማግባት የ100 ፍልስጥኤማውያንን ሸለፈት በጥሎሽነት ለንጉሥ ሳኦል ያቀረበበት ታሪካዊ ሁኔታን (ክስተትን) (1ሳሙ. 18:25 -27)፣

6. የመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞንን የፍቅር መልእክት እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመቀበል መቸገር (መኃ. 7:1-9)፣

7. ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ያለውን የግል ግንኙነታቸውን የሚያመለክት የደብዳቤውን መደምደሚያ ለመቀበል መቸገር (2ጢሞ. 4:9-13)፣

---

[35] ሳዲቅ መሀመድ አህመድ፣ *ላለመደናገር ማመሳከር*፣ 1998፣ ገጽ 32-33::

## ለመለኮታዊ ተአምራትና ለታሪካዊ ክንዋኔዎች የተሰጠ መልስ

### የተአምራት መልስ

#### መግቢያ

ስለ አምላክ ስናስብ ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባው ነገር እርሱ ሕያው መሆኑን ነው:: ሕያው ከሆነ ደግሞ የሚሠራ ነው፣ እንጂ በምድር ላይ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ዝም ብሎ ተመልካች አይደለም:: አምላክ የሚሠራ ከሆነ እርሱ የሚሠራው ሥራ ከሰው ሥራ የተለየ ነው የሚሆነው፤ የሚበልጥ ነው የሚሆነው፤ የረቀቀ ነው የሚሆነው፤ የመጠቀ ነው የሚሆነው:: በሌላ አነጋገር ከሰው አእምሮ ችሎታም ሆነ አቅም በላይ የሆነ ነገር ነው የሚሠራው:: ይህ ነው እንግዲህ ድንቅና ተአምራት የሚባለው::

የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ሕያው ስለሆነ ይሠራል:: ሰው የሚችለውን ሳይሆን፣ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ ሥራን ይሠራል፤ ድንቅንና ተአምራትን ያደርጋል:: ለዚህም ነው ዘማሪው፣ «ብቻውን ተአምር የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ» (መዝ. 72:18) ሲል የተናገረው፤ ድንቅና ተአምራት የሰው ልጆችን ችግር የመፍታት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ለአምላክ የሕያውነቱ ማስረጃም ጭምር ናቸው::

በዚህ መንፈስ ከላይ ሙስሊም ጸሐፊያንን ያስቸገሩትን ጥያቄዎች ከተመለከትን ጉዳዩ ከባድ ወይም የተወሳሰበ መሆኑ ቀርቶ ቀላልና ማንም ሰው ሊረዳው የሚችለው ነገር ሆኖ እናገኘዋለን::

ያዕቆብ በተላጠው በትር በኩል ወይም ምክንያትነት የአምላክን ተአምር ሊቀበልና ሊባረክ የቻለው በአስማትም ሆነ በመላምት መንገድ ሄዶ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በሕልሙ ባሳየው መገለጥ እምነና ታዝዞ ነው:: እግዚአብሔር በአጎቱ በላባ አታላይነት የተነሣ የደረሰበትን በደል ስለ ተመለከተ ነው ይህን ሕልም ያሳየው፤ በዚህም ምክንያት ነው ያዕቆብ በመታዘዝ ሊባረክ የቻለው :: (ዘፍ. 31:7-12)



በሰዓም የተባለው ሰው በገንዘብ ተገዝቶ እግዚአብሔር ሊረግመው ያልወደደውን ሕዝብ ለመርገም በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ተቋቁሞታል:: የተመዘዘ ሰይፍ የያዘውን መልአክ እንድታይ ለአህያዋ እግዚአብሔር ዓይኖችዋን ከፍቶላታል:: ስለዚህም፣ አልሄድም ብላ ተኛች፤ ደጋግሞ በደበደባት ጊዜ ደግሞ አህያዋ በሰው ቋንቋ በልዓምን እንድትገሥጸው እግዚአብሔር የአህያዋን አፍ ከፈተላት:: ይህ ተአምር ነው:: በአእምሮ ስናስበው ከባድ ነው:: ከአእምሮ በላይ ነውና!

ቢሆንም፣ ስእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለ ሌለ እግዚአብሔር ይህን አላደረገም (አያደርግም) ማለት አይቻልም፤ በእኔ እምነት ማለት የሚቻለው እኔ በእውነት በእግዚአብሔር ላይ እምነት ስለ ሌለኝ አላምንም ወይም እኔ የማምነው አምላክ ሕያው ስላይደለ፣ ይህን መሥራት አይችልም ነው:: ወይም ሕያው ከሆነው የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር የእኔ አምላክ የተለየም ሆነ ያነሰ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ ነው ማለት የሚቻለው::

የሰምሶንን አገልግሎት ስናስብ ሁልጊዜ በውስጡ በታላቅ ኃይል የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን መንፈስ መዘንጋት የለብንም:: «የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ወረደ» የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ከሠራቸው ተአምራቶች ጋር ተያይዞ ተቀምጦአል:: (መሳ. 14:7፣14:19፣15:14)

ስለሆነም፣ ሰምሶን የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል ስለሚወርድ ሦስት መቶ ቀበሮችን ለመያዝ፣ ሁለት ሁለት አድርጎም ለማሰር ምንም የሚቸግረው ነገር እንደ ሌለ ለመረዳት እንችላለን:: የግድ ሦስት መቶውን ቀበሮዎች በአንድ ቦታ ላይ መሰብሰብ ላያስፈልገው ይችላል:: ሁለት ሁለቱን ይዞ በቅደም ተከተል 150 እርሻዎችን ማቃጠል ይችላል:: የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል በእርሱ ላይ ከወረደ 1000 ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያም በላይ ሰዎችን በአህያ መንጋጋ ሊገድል ይችላል:: በእግዚአብሔር መንፈስ

ኃይል ከሰው ችሎታና አቅም በላይ የሆነ ሥራ ሊሠራ ይችላልና።

ሶምሶን የተጠራው (የተወለደው) እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ከፍልጥኤማውያን ቀንበር ለማዳን እንደሆነ፣ ይህንንም የሚያደርገው በእግዚአብሔር በቀል ውስጥ ሆኖ ስለሆነ፣ ታላላቅ ድሎችን በፍልስጥኤማውያን ላይ እንዲቀዳጅ እግዚአብሔር በመንፈሱ ኃይል ይረዳው ነበር። ስለዚህ፣ ይህ የሚቻል ነገር እንጂ የማይቻል ነገር ተደርጎ መቁጠር የለበትም።

## ለታሪካዊ ክንዋኔዎች የተሰጠ መልስ

ወደ ታሪካዊ ክስተቶች ፊታችንን ስንመልስ፣ መጽሐፈ ቅዱስ ስለ ተጻፈበት መንገድና ሁኔታ፣ በተለይም የታሪክ መጻሕፍት (ትረካዊ አጻጻፍ) ስለ ተጻፈበት መንገድ ስንመለከት ብዙ መመሪያዎችን ተመልክተን ነበር። አሁንም ለማስታወስ ያህል ጥቂቶቹን እንሥተን ለተነሡት ጥያቄዎች መልስ ወደ መስጠቱ እናመራለን። መመሪያዎቹ ማለትም መሠረታውያን የሆኑት፦

1. ታሪኮች በቀጥታ የመሠረተ እምነት ትምህርቶች አለመሆናቸው፣

2. ሰዎች የሚያደርጉዋቸው ድርጊቶች ሁልጊዜ መልካም ምሳሌነት ያላቸው እንደሆኑ ተደርገው መወሰድ እንደ ሌለባቸው፣

3. ታሪካዊ ጽሑፎች ለመታዘዝም ሆነ ላለመታዘዝ ምሳሌ የሆኑ እውነተኛ የሕይወት ገጠመኞችን የሚይዙ መሆናቸው፣

4. ሰዎች ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ኀላፊነት እንደማይወስድ፣ ነገር ግን ሰዎቹ እራሳቸው ኀላፊነት የሚወስዱ መሆኑ... ወዘተ ናቸው።

ወደ ጥያቄው መልስ ስናመራ ንጉሥ ሳኦል፣ ዳዊት፣ የ100 ፍልስጥኤማውያንን ሸለፊት እንዲያመጣ



ማዘዙ የሚያመለክተን ነገር አለ። አንደኛው፣ በዳዊት ላይ ስለሚቀናበት ሙቶ ሰው ለመግደል ሲሄድ እንዲሞት መፈለጉ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፣ በዚያን ዘመን ለንጉሡ ጠላቶቹን የመበቀል ያህል ትልቅ ነገር ስለ ሌለ፣ ዳዊትም የድሀ ቤተሰብ ልጅ በመሆኑ በእርሱ ላይ የወርቅና የብር ጥሎሽ ከሚጣልበት ይልቅ ኀልያድን በገደለበት ጀግንነቱ ንጉሥን የሚያስደስት የተሻለ ማካካሻ (የንጉሡን ጠላቶች መበቀል) ስለሚሆንለት ነው።

ከሶምሶን ታሪክ ላይ እንደ ተመለከትነው ሁሉ የሕዝቡን ጠላቶች የሚበቀልበትን የትኛውንም መንገድ እግዚአብሔር ሳይቃወም ምናልባትም ሊጠቀምበት ይወድድ ይሆናል። ስምሳሌ ያህል ከፍልስጥኤማውያን ሴት ጋር መዋደዱንም ሆነ መጋባቱን ለሶምሶን በመፍቀዱ ለጠብ የሚሆን ምክንያት እንዲሆንለት አድርጎ መጠቀሙ የተገለጠ ነው።

ስለዚህ፣ በዚህ ሰብአዊ ተግባር ውስጥ የራሱን አጀንዳ ሊፈጽም ስለወደደ በዝምታ ውስጥ መሥራት መምረጡን እንመለከታለን። የባልና የሚስት ኀብረትን በአዳምና በሔዋን መካከል የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን፣ በትዳር መካከል ሊኖር የሚገባ ፍቅርን፣ ታማኝነትና፣ ዋጋ መክፈልን፣...ወዘተ ለትውልድ ሁሉ በሚታይ የፍቅረኞች ምሳሌነት በኩል እንዲተላለፈ መደረጉ ለሁለት ነገር የሚጠቅም ነው።

1. ሕያው የሆነ ግንኙትን ለመማር (Living Relationship)፣

2. ተግባራዊ ፍቅርን / አሳባዊ ወይም ንድፈ አሳባዊ/ ያልሆነ ፍቅርን (Practical not theoretical) ለመማር። ይህ በሁለት ፍቅረኞች የፍቅር ልውውጥ መልክ የተጻፈ መጽሐፍ በአያሌው ይጠቅማል ደግሞም የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም የሰው ሕይወት ገጽታዎች የሚዳስስ መሆኑን ያመለክተናል።

በጳውሎስና በጢሞቴዎስ መካከል ስላለው የግል ግንኙ -ትም ስናስብ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል መሆኑን ልንረዳ ያስፈልጋል።

ሀ. የእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ በታሪክ ውስጥና ሕያው በሆነ ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ የመጣበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥልንም ሆነ ተጨማሪ ማስረጃ የሚሰጠን መሆኑን ያመለክተናል።

ለ. ሕያው ከሆነ አምላክ ጋር የተገናኙ ሰዎች ም በበኩላቸው ሕያው የሆነውን ግንኙነት ከሌሎች ጋር የሚካፈሉበትን መገለጥና መልእክት ሲካፈሉ ብሎም ሌሎችንም አገልጋይ አድርገው ሲያሠለጥኑ፣ ሕያው የሆነ በአስተማሪና በተማሪ መካከል ያለ ግንኙነት ሊያደርጉ ግድ የመሆኑን ጉዳይ ያመለክተናል።

ሐ. ሕያው የሆነው መልእክት ሕያው በሆነ ግንኙነት በኩል ወደ እኛ መድረሱን ያሳስበናል። በእንድምታውም የሚያሳስበን ነገር አለው። ይህም እኛም ሕያው የሆነውን መልእክት ለቀጣዩ ትውልድ ሕያው በሆነ ግንኙነት አማካይነት (በመንፈስ ኅብረት) እንድናደርሰው የማነሣሣቱ ሁኔታ ነው።

መ. በሰዎች መካከል የሚሠራ ወይም ሊሠራ የሚወድድ አምላክ በመካከላቸው መልካም የሆነ የግል ግንኙነት እንዲኖር መውደዱ ለሥራው መቃናት የሚያስብ ብልህ አምላክ መሆኑን ያመለክተናል።

ሠ. በሰዎች መካከል መልካም ግንኙነት መኖሩ ሰዎቹ ሰላማዊ የሆነ እምነት ያላቸው መሆኑን ያመለክተናል፤ አምላካቸውም ይህን መፍቀዱ እርሱ የሰላም አምላክ መሆኑን ያመለክተናል።

**መ. የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በቁርዓን መልእክት መስፈርትነት ለመመዘን መሞከር:-**

ሙስሊም ጸሐፊዎች ከሚቸገሩባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በቁርዓን መልእክት መመዘኛ መስፈርትነት ለማየት የመሞከራቸው ጉዳይ ነው።



ይህ በሁለት መልኩ ሊገለጥ ይችላል:-

ሀ. ከቁርዓን መልእክት ውጭ የሆነ ነገር በሚገጥማቸው ጊዜ፣ ይህ ቁርዓን ላይ ስለ ሌለ ትክክል አይደለም ወይም ስሕተት ነው ብሎ ማሰብና ማመን፣

ለ. ቁርዓን በተጻፈበት ወይም ቁርዓናዊ መገለጥ በመጣበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጻፍ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ በቁርዓን መንገድ እንዲመጣ መፈለግ፣ ይህ ባልሆነም ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ የመጣበትንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን መንገድ ትክክል አይደለም ብሎ ማሰብ።

ለምሳሌ የቁርዓን መገለጥ የመጣበት መንገድ ወይም አላህ መገለጥን ለነቢያት የሚሰጥበት መንገድ ሦስት እንደሆኑ፣ እነዚህም ወህይ ማለትም መለኮታዊ ራእይ፣ ከግርዶ ወዲያ ማለትም ነቢዩ አላህን ሳያይ ያለማንም አገናኝነት ድምፁን በቀጥታ የሚሰማበት መንገድና መልክተኛ የሚሆን መልአክን ልኮ ለነቢዩ መልእክትን የሚያደርስበት መንገድ ናቸው። ከዚህ በመነሣት አንዳንድ ሙስሊም ጸሐፊያን የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ተቀባይነት እንዲያገኝ ካስፈለገ፣ እነዚህን ቁርዓናዊ የመገለጥ መምጫ መንገዶች ማሟላት አለበት ሲሉ ለመናገር ይደፍራሉ።[36]

እንደ ተጨማሪ ጥያቄ እንመልከተው

ለምሳሌ ከቁርዓን መልእክት አንጻር ለመመልከት የሚሞከሩበትን ሁኔታ እንመለከት። በዘሌዋውያን መጽሐፍ (15:19-22) ላይ ሴቶች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ከወንዶች መለየት እንዳለባቸው፣ በዚያን ጊዜም ርኩስ እንደሆኑ፣ ወንዶችም ሴቶችን በዚህ ወቅት መንካት እንደ ሌለባቸው፣ ወንዶች በዚህ ወቅት ሴቶችን፣ ልብሳቸውን፣ አልጋቸውንም ሆነ መቀመጫቸውን ቢነኩ እንደሚረክሱ ተነግሯል።

[36] ሳዲቅ መሀመድ አህመድ፣ ላስመደናገር ማመሳከር፣ 1998፣ ገጽ 32-33።

ይሆን አሳብ ከራሳቸው ቁርዓን እስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር ላለመቀበል ወይም ስሕተት ነው ለማለት እንድ ሙስሊም ጸሐፊ ሲሞክሩ፣ «...እንዴት ደግሞ የተኛችበትና የተቀመጠችበትን መኝታዋን የሚነካ ሰው ሊረክስ ይችላል?...ቁርዓን ግን የሚያስተምረው ከአደፍም ይጠይቁሃል እርሱ አስጸያፊ ነው፣ ሴቶችንም በአደፍ ጊዜ ራቁአቸው ንጹሕ እስከሚሆኑ ድረስ አትቅረቡዋቸው...» አዎ ሴት ልጅ ሳትሆን የረከሰችው ወይም የምታስጠይፈው ያ የሚወጣ ነገር ነው:: ደግሞም ሴቶችን በአደፍ ጊዜ ራቁዋቸው የሚለው ጥቅስ የሚያመለክተው መቀመጫዋን፣ መኝታዋንና ልበሷን ከመንካት ሳይሆን ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው:: ይህንን ትርጉም ደግሞ ነቢያችን (ሰ.ወ.ወ) «ኢሳ ነው ኩስ ሽይኢን አልለነካህ (ከግንኙነት በስተቀር ሁሉንም ፈጽሙ» በማለት ሰውየው የወር አበባ ከማየቷ በፊት ከእርሷ ጋር ያደርግ የነበረውን ነገር ሁሉ) አብሮ መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛትና መተሻሸት፣ ማድረግ እንደሚችል ገልጠዋል፤ ሲሉ ጽፈዋል::[37]

## ለዚህ የተሰጠ ምላሽ

የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በዕድሜ ከቁርዓን ጋር የሚነጻጸሩ አያደሉም፤ ቁርዓን ባልነበረባቸው በብዙ ሺህና መቶ በሚቈጠሩ ዓመታት ውስጥ የነበሩና የተገለጡ መለኮታዊ መገለጦች ናቸው:: ስለሆነም፣ በምንም መልኩ መልእክታቸው ከቁርዓን ትምህርት ጋር እንዲመሳሰል መጠበቅ የለበትም:: በሌላ በኩል ደግሞ ያልነበረ መጽሐፍ ትምህርትም ሆነ የአጻጻፍ መንገድ እንዲሁም መገለጡ የመጣበትን መንገድ ሊከተሉ የሚገደዱበት ወይም የሚጠበቁበት ሁኔታ የለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን በሌለባቸው ጊዜያት በራሱ ህልውና የኖረና ዛሬም በዚሁ ህልውናው የሚኖር መጽሐፍ መሆኑ ምንጊዜም ቢሆን መዘንጋት የሌለበት ታላቅ ጉዳይ ነውና!

ቁርዓን ግን ብዙ ነገሮችን ከአይሁድ እምነትና ከክርስትና እምነት (በጥቅሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ)

[37] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 17-18::



የወሰደና በራሱ ያልቆመ ነው:: ሌላው ቢቀር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማለትም አዲስ ኪዳን ከተጻፈና ካለቀ በግምት ወደ 550 ዓመታት በኋላ የተጻፈው ቁርዓን ብዙ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅድስ በወሰደበት ወይም በተጋራበት ሁኔታ የኋለኛው መጽሐፍ ምንጩ ያደረገውን የፊተኛውን መጽሐፍ እንዲሁም የኋለኛው መጽሐፍ መገለጥ ተቀባይ (ነቢዩ መሃመድ) እራሳቸው በብዙ ጉዳዮች ላይ የመሰከሩለትን መጽሐፍ ተበርዟልና ተከልሷል ማለት የራስን እምነትም ሆነ የሃይማኖቱን መጽሐፍ ህልውና በጥያቄ ውስጥ ማስገባት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል::

ነገር ግን አንዳንድ የእስልምና ምሁራን የመጽሐፍ ቅዱስ መበረዝን የማይቀበሉበት ሁኔታ አለ:: ምክንያታቸውም መጽሐፍ ቅዱስ፣ በየፈርጁ በውስጡ በያዛቸው ለያቅል የሆኑ መጻሕፍት ተጽፈው እንዳለቁ ወዲያውኑ በመላው ዓለም የተሠራጨ ስለሆነ፣ ተበርዟል ብሎ መናገር አይቻልም የሚል ነው:: ምክንያቱም፣ በመላው ዓለም በብዙ ቅጂ ተባዝቶ የተበተነ ስለሆነ፣ መበረዝ የሚፈልግ አካል እነዚህን ሁሉ ቅጂዎች በቅድሚያ ማስወገድ ያለበት በመሆኑ ነው:: ይህ ደግሞ በዛሬው ዘመን ያለና በብዙ ቅጂዎች የተሠራጨውን ቁርዓንን ከመላው ዓለም ሰብስቦ ለመበረዝ የመሞከር ያህል ምንአልባትም ከዚያ በላይ የሚሆን እጅግ ከባድም ሆነ የማይቻል ነገር ነው:: በአጭሩ ጉዳዩ የማይታሰብ ነው::[38]

መገለጥ የመጣበት መንገድ በቁርዓን ሦስት ሊሆን ይችላል:: እዚህ ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ ልናነሣ ወይም ትኩረት ሊኖረን አይችልም ወይም አይገባም:: ምክንያቱም፣ ቁርዓን በፈለገበት መንገድ ቢመጣ እኛ ተቃዋሚም ሆነ ደጋፊ የምንሆንበት ሁኔታ የለምና::

ነገር ግን የቁርዓን መገለጥ በመጣበት መንገድ ብቻ ነው ሁሉም መገለጥ መምጣት ያለበት ብሎ ማሰብና

[38] አንዋር መሐመድ፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ይጣረሳልን*፣ አዲስ አበባ፡ ጌጃ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 1997፣ 7-11:: አንዋር እንደ አል-ታባሪ፣ ፋህሩ ዲን ራዚ፣ አቡ ሐሚል አል-ጋዛሊ እና አብደላ የሱፍ አሊ ያሉ ምሁራንን ምስክርነት በግልጥ ያቀርባል::

የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥም በዚሁ መልኩ መምጣት አለበት ብሎ ማሰብ ጅልነት መሆኑን ሳናስምርበት አናልፍም:: ምክንያቱም አንድ ነገር የሌላው ነገር ጥሩ ናሙና መሆን የሚችለው ከሌላው ነገር በፊት የተገለጠ ከሆነ ብቻ ነውና::

እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ ህልውና ላይ የቆመ መጽሐፍ ስለሆነ፣ በቁርዓን ሊገመገም አይችልምና:: ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን ባልነበረበት ዘመን ሁሉ የነበረ መጽሐፍ ስለሆነ፤ ከኋላው በመጣ መጽሐፍ የአጻጻፍ መንገድ ካልተጻፈ ሊባል አይችልምና:: ቁርዓን ስለ አላህ የሚያወራ መጽሐፍ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር (በመለኮት አንድ በአካል ሦስት ስለሆነው አምላክ) የሚያወራ መጽሐፍ ስለሆነ፣ የመለኮታዊ አስተሳሰብ ልዩነት በመካከላቸው አለ:: ስለዚህም፣ አላህ በራሱ መንገድ ሊገለጥ ይችላል:: እግዚአብሔር ደግሞ በራሱ መንገድ ተገልጦአል:: ስለሆነም፣ የአንዱን አምላክ መገለጥ ሊያውም ከኋላ የተነሣውን ወስደን የሌላው፣ ሊያውም ከጥንት ጀምሮ በነቢያቱ በልጁም ሆነ በሐዋርያቱ በኩል በትክክል በብዙ ማስረጃዎችና በታሪክ ውስጥ የተገለጠው አምላክ መገለጥ መስፈርት ማድረግ አይቻልምና:: ቁርዓን ግን በራሱ ህልውና ላይ ያልቆመና በመጽሐፍ ቅዱስ ህልውና ላይ የቆመ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርትነት ሊገመገም ቢችል አያስደንቅም::

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሲነጻጸር የቁርዓን ዕድሜ ትንሽ ነው፣ በዚያ ላይ የአላህ ምስክር አንድ ብቻ:- እራሱ ነቢዩ መሃመድ ብቻ ነው:: ስለዚህ፣ ብዙ ዓመታትን ባስቈጠረው በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁርዓን ቢገመገም ተገቢም ነው የሚጋነንም አይደለም::

መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓን በሌለበት ጊዜያት በሺህዎች የሚቈጠሩ ዓመታት የነበረና፣ ብዙ ትውልዶችን ያገለገለ ብዙም ምስክሮች ያሉት መጽሐፍ ነው:: እነዚህም ምስክሮች:-

- መገለጡ የመጣላቸው ሰዎች፣



- መገለጡን በታሪካቸው ውስጥ ኖረውት ያጣጠሙት ብዙ ትውልዶች፣
- በእግዚአብሔር እስትንፋስ መገለጡን፣ በመገለጡ ሳቢያ በኅብረተሰቡ ውስጥ የመጣውን ለውጥ፣ ስመገለጡ የመታዘዝም ሆነ ያለመታዘዝ ምሳሌ የሆኑ ሰዎችን ታሪክና በአጠቃላይ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ የጻፉ ቅዱሳን ሰዎች፣
- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቀደሙ መገለጦችንም ሆነ መገለጦችን የዘገቡ መጻሕፍትን ስለ እኔ በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙራት እንደ ተጻፈ (ሉቃስ 24;48-49) ብሎ ያረጋገጠበት ሁኔታ፣
- የእርሱን ትምህርቶች ተቀብለው ጌታችን እንዳደረገ ከብሉይ ኪዳን ትምህርቶች ጋር በአዲስ ኪዳን ሥነ አፈታት (Hermenuetics) ብርሃንነት ያስተማሩ ሐዋርያትና ትምህርታቸው (አዲስ ኪዳን)፣
- የሐዋርያት ትምህርትን ወደ ቀጣዩ ትውልድ ጠብቀው ያሸጋገሩ የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶችና በእነርሱም አማካይነት እነዚህን ከጥንት ጀምረው የተሰጡ መገለጦችንና መገለጦቹ የተጻፉባቸውን ትምህርቶችና አዲስ ኪዳናዊ የሥነ አፈታት ጥበብን ሁሉ ይዛ ያለችና ለቀጣዩ ትውልድ እያደረሰች ያለች ቤተ ክርስቲያን፣
- የጥንትዋንም ሆነ የዛሬዋን ቤተ ክርስቲያን ሲመራ የኖረው፣ የሥላሴ አንድ አካል የሆነው ጌታ መንፈስ ቅዱስ፣
- እንዲሁም፣ የእርሱ ማደሪያ የሆኑ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑ ቅዱሳን (አማኞች) ሁሉ፣ ምስክሮቹ ናቸው::

ስለዚህ፣ በብዙ ትውልዶች፣ በብዙ ጸሐፊያን፣ በብዙ ነቢያት፣ እንዲሁም ግዛድና እውነተኛ በሆነው ታሪክ ውስጥ ተፈትኖ ያለፈው የእግዚአብሔር ብቸኛ የሥልጣን ቃል፣ ከጊዜ በኋላ በአንድ ሰውም ሆነ ምስክር ብቻ በኩል በመጣ ትምህርት፣ መገለጥም ሆነ መገለጡ በመጣበት መንገድ የሚመዘንበት ምንም ዓይነት አሳማኝም ሆነ ተቀባይነት ያለው (Logical and Reasonable) ምክንያት የለም::

እነዚህ ሁሉ ምስክርነቶች ያሉት፣ እውነታውም የተመሠረተው፣ በባዶ ነገር ላይ (vaccum) ሳይሆን፣ ነገር ግን፣ በታሪክ ውስጥ የተገለጠው መጽሐፍ፣ ያለ ታሪክና ትውልዶች ምስክርነት በአንድ ሰው የመጣውን መገለጥም ሆነ መጽሐፍ ቢመዝነው እጅግ ያንሰበት ይሆናል እንጂ፣ ከቶ አይበዛበትም::

የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጦች የመጡበት መንገድ ብዙ ነው:: ይህን ወስኖ በቍጥር ማስቀመጥ አይቻልም:: ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር ከአእምሮአችን በላይ ስለሆነ፣ የሚሠራባቸው መንገዶች ውሱን ሊሆኑ አይችሉምና:: ይህን እውነታ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲያመለክት፣ «እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስተውለውም:: በሕልም በሌሊት ራእይ፣ እፍላ እንቅልፍ በሰዎች ላይ ሲወድቅ፣ በአልጋ ላይ ተኝተው ሳሉ፣ በዚያን ጊዜ የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል በተግሣጹም ያስደነግጣቸዋል::» (ኢዮብ 33:14- 16) ይላል::

የዕብራውያን ጸሐፊም፣ ጥቂት እግዚአብሔር የተገለጠባቸውን መንገዶች ሲጠቁም:- «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን::» (ዕብ. 1: 1-2) ይላል::

ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርን የመናገሪያ መንገድ ገድበን፣ እርሱን እራሱን የተገደበ አድርገን ባንመለከት ወይም



ለማሳየት ባንሞክር መልካም ነው:: እግዚአብሔር ውሱን አይደለምና::[39]

በተጨማሪም፣ በቁርዓን ትምህርት መስፈርትነት፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት ሙስሊም ጸሐፊያን በተናገሩት የሴትና የወር አበባ ጉዳይ ላይ መልስ ለመስጠት ያህል:-

1. የአላህ ፍላጎትን፣ ከእግዚአብሔር ፍላጎት ለይቶ መመልከት የተገባ ሆኖ ሳለ፤ የአላህን ፍላጎት፣ በእግዚአብሔር ፍላጎት ላይ በኃይል ለመጫን መሞከር ተላላነት መሆኑን ማመልከት ይቻላል:: ያስፈልጋልም::

2. በእግዚአብሔር እይታ፣ የወር አበባው ብቻ ሳይሆን፣ የወር አበባው የታያት ሴት፣ እንዲሁም አልባሳቶችዋ ፏና የምትገለገልባቸው ቍሳቍሶች ሁሉ፣ እንዲሁም አልባሳትዋና ከገላዋ ጋር የተገናኙ ነገሮች ሁሉ ርኵስ ናቸው::እነዚህንም ሁሉ የሚነካ የረከሰ ነው የሚሆነው:: ርኵስ ማለት፣ እንደኛ ያልተቀደሰ ማለት ነው:: ካልተቀደሰ ነገር ጋር የተነካካና የተገናኘ ነገር ሁሉ ሊቀደስ አይችልም:: እስጠያፊ ለእይታ፣ ማለትም ለሰው እይታ የምንጠቀምበት ቃል ነው:: ርኵስ ስንል ግን ያልተቀደሰ፣ ማለትም ለእግዚአብሔር ያልተለየና የማይቀርብ፣እንዲሁም ለክብሩ የማይሆን ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ይህ በራሱ በእግዚአብሔር እይታ እንጂ፣ በአላህና በነቢዩ እይታ የሚለካና የሚወሰን አይደለም::

3. ምናልባት፣ አላህ፣ የወር አበባውን ብቻ ይሆናል እንደ አስጸያፊ የሚመለከተው:: እግዚአብሔር

[39] ፖል ኢ. ሊትል የተባሉ ጸሐፊ "እግዚአብሔር በብዙ መንገዶች እራሱን ገልጦአል ይላሉ:: ሲዘረዝሩትም:- በፍጥረት ሥራው በታሪክ ውስጥ በተለይም ከእስራኤልና በዙሪያዋ ካሉ ሕዝቦች ጋር ባደረጋቸው ግንኙነቶች ውስጥ በሠራቸው ታላላቅ ሥራዎችና ክስተቶች እንዲሁም በነቢያት ስብከቶችና ትንቢታዊ መልእክቶች በኩል የተገለጠ ሲሆን፣ ሙሉ የሆነውን መገለጡን ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በኩል ሰጥቶናል ይላሉ::" Paul E. Little, *Know What You Beleve*, USA: Victor Books, 1970, p. 8

ደግሞ ከእርሱ ጋር ያለ የትኛውንም ንኪኪ፣ ሊጠላው ቢችል ይህ መብቱ እንደሆነ መቁጠር ወይም መታሰብ አለበት። እርሱ፣ በአሳሀም ሆነ በመሃመድ እይታ ነገሮችን የሚመለከት አይደለም። አሳሀም ሆነ መሃመድ ከመገለጣቸው በፊት፣ ተገልጠ ፈቃዱን የገለጠ መሆኑም መረሳት የለበትም።

4. እስኪ፣ አንድ ነገር እናስብ! አንድ ሰው የወር አበባዋን እያየች ካለች ሴት ጋር አብሮ እንዲተኛ እና እንዲተሻሻት ከመፍቀድና ከቶ እንዲርቅ ከማዘዝ የቱ ይሻላል? አብሮ ከተኛና ከተሻሸ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ የወሲብ ፍላጎቱ፣ በተለይ የወንዱ፣ የማይቀሰቀስበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። ነገር ግን፣ ፈጽሞ ከተለየ ሲፈጠር ከሚችለው መሳሳት የሚታደግ ይሆናል። ስሊዚህ፣ በወር አበባ ወቅት ያለ ግንኙነት ከልብ የማይፈለግ ከሆነ፣ ፈጽሞ መራራቁ፣ አብሮ ከመተኛቱም ሆነ ከመተሻሸቱ የተሻለ መሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው።

5. በመሠረቱ፣ በዘሌ. 15:19-22 የወር አበባ ሴትን እንደሚያረክሳት የተነገረው፣ እንደ ጥላ በጊዜያዊነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተቀረው ሕዝብ የሚለይበትን (የሚቀደስበትን) ከሚያመለክቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ ሆኖ ነው። አካሉ ክርስቶስ ሲገለጥ ግን፣ በአካሉ ውስጥ ያለ የአንድ እውነት አመልካችነት ሚና ብቻ ነው የሚኖረው። በጥላና በምሳሌነት የተሰጡ ሌሎች ብሉይ ኪዳናዊ ትእዛዛት ወይም ሥርዓታዊ ሕጎችም (Cerimonial Laws)፣ እንደዚሁ በአካሉ በክርስቶስ የሚገለጡ እውነታዎችን ጠቋሚ ወይም አመልካቾች ናቸው። ለምሳሌ ያህል፣ እግዚአብሔር ካለወደደው ነገር ጋር አለመተባበርን ያመለክተናል። ይህ አዲስ ኪዳናዊ ቋሚ መልእክቱ ሲሆን፣ ጥላው ግን በብዙ መልኩ በብሉይ ኪዳን ተገልጦአል። የሴት ወግ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ነገሮች ለምሳሌም፣ ፈሳሽ ያለበትን ሰው ወይም ለምጽ ያለበትን ሰው



መንካት...ወዘተ በሚሉ አሳቦች ተቀምጦአል። (ዘሌ. 13 ከለምጽ ደዌ ጋር የተቆራኘ ቋቁቻ፣ እባጭም ሆነ ቁረቁር የሚያረክሱ መሆናቸው ተገልጦአል። እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት እግዚአብሔር የማይወድዳቸውን ተግባራት ነው። በዚህም፣ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያጐድፍ፣ ስሙን በከንቱ የሚያስጠራ ተግባር ከሚፈጽም፣ ግለሰብም ሆነ በአማኝ ስም የተጠራ ቡድን መለየት እንደሚያስፈልግ እንረዳለን። ይህ እንግዲህ የጥላው አመልካችነት ያረፈበት አካልን ማዕከል ያደረገ አተረጓጐምን በመከተል የሚገኝ፣ አዲስ ኪዳናዊ መልእክቱ ነው።

ለምሳሌ ያህል፣ ሐዋርያው ጳውሎስ የአባቱን ሚስት የተገናኘውን ሰው ከመካከላችሁ አስወግዱ ብሎ የተግሣጽ ምክርና ትእዛዝ የሰጠበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም:-

1. ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ስለሚያቦካ (1ቆሮ. 5:6)፣
2. ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ስለሚያጠፋ (1ቆሮ. 15:33)፣
3. ከክፋዎችና ከተሳሳቱ ሰዎች መራቅ እንደሚገባን ስለ ታዘዝን (1ጢሞ. 6:5)፣
4. በሌሎች ኃጢአት እንዳንተባበር (1ጢሞ. 5:22) በመታሰቡ ነው።

ስለሆነም፣ ከአዲስ ኪዳናዊና ሐዋርያዊ ሥነ አፈታት እሳቤ በመነሣት፣ የሴቶች መርገም፣ ማለትም ለመርከሳቸውም ሆነ ሌላውን ለማርከስ ምክንያት የሆነ ነገር፣ ዛሬ በአዲስ ኪዳን ዘመን ሊያረክስ ለሚችለው፣ ከሰው ልብ ለሚወጣው አሳብ፣ ጥላና ምሳሌነቱ በሰው ልብ ውስጥ ላለ ክፉ አስተሳሰብና ኃጢአት እንደሆነ፣ መታወቅ ይኖርበታል።[40]

[40] በዚህ ረገድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ እዳሪ ሆኖ ከሰውነት ስለሚወጣ ሰውን ሊያረክሰው እንደማይችል፣ ነገር ግን ከአፍ የሚወጣ ሁሉ ከልብ ስለሚወጣ

በወር አበባ ጊዜ ያለ ግንኙነት ዛሬም ቢሆን ከባህልና ከሕሊና አንፃር አስጠያፊነቱ የተጠበቀ ነው:: ነገር ግን፣ ሴቲቱንም ሆነ ከእርስዋ ጋር በመጨባበጥ ንኪኪ የሚያደርጉ ሰዎችን አያረክስም፤ ይህም ሲታወቅ ይገባል:: ምክንያቱም፣ ከአፍ የሚወጣ ነገር ብቻ ሰውን የሚያረክሰው መሆኑ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ በግልጥ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው::

## ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጋጩ ነገሮች እንዳሉ መቍጠር - የአሳብና የአሃዝ ግጭቶች እንዲሁም የስም ግጭት

ሙስሊም ጸሐፊያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ አንድ ጉዳይ የሚያወሩ ሁለት ክፍሎች ላይ የሚታዩ «መጠነኛ ልዩነቶችን በመውሰድ የስም፣ የአሳብና የአሃዝ ግጭቶችን ከልክ ባለፈ መልኩ በማጉላት የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ የመለኮት መጽሐፍነት ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ሲሞክሩም ሆነ ሲጣደፉ ይስተዋላሉ::»

ለምሳሌ ያህል:-

-በ2ኛሳሙ. 10:18 ላይ ያለውን «ሰባክንና»፣ በ1ዜና 19:18 ላይ ያለውን «ሾፋክን»፣ «ፈረሰኛ ን»፣ እግረኛን፣ 700 እና 7000፣

-በ1ኛነገ. 4:26 ላይ «አርባ ሺህ ጋጥ»፣ በ2ኛዜና 9:25 ላይ አራት ሺህ ጋጥ፣

-በ2ኛሳሙ. 8:3-5 ላይ «አንድ ሺህ ሰባት መቶ ፈረሰኞች፣ በ1ዜና ላይ ሰባት ሺህ ፈረሰኞች፣

-የብንያም ልጆች በዘፍ. 46:21 «አሰቤል»፣ በ1ኛ ዜና 7:6 ላይ ደግሞ «ይድኤል»፣

---

የሰውን ሁለንተና እንደሚያረክስ የተናገረበት ሁኔታ በአሳበም ሆነ አሳብን ተከትሎ በሚመጣ ድርጊት ሚፈጸም ኃጢአት ሰውን እንደሚያረክሰው ያስተማረው ትምህርት መልስ ነው::



-የእስማኤል ልጅ በዘፍ. 28:9 ላይ «ማዕሌት»፣ በዘፍ. 36:1-3 ላይ ደግሞ «ቤሴሞት»፣

-በኬብሮን ለዳዊት ስለ ተወለዱ ልጆች በ2ኛ ሳሙ. 3:2-3 «ማኖንያ ደሎሚያ? በ1ኛዜና 3:1 ደግሞ «አምሃንና ዳንኤል»...ወዘተ የሚል ነገር አለና ይህ ልዩነት ስምን መጣ? የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ጥርጣሬና ችግር ውስጥ አይከተውም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎችን ያነሣሉ::

### ለዚህ የተሰጠ ምላሽ

ስነገሩ እነዚህን ብቻ ሳይሆኑ፣ ሌሎች የስምና የአሃዛት እንዲሁም የስፍራ ግጭቶችን በብዛት ነው ለማሳየት የሚሞክሩት፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መስጠት፣ ማብቂያ ለሌለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደ መሞከር ነው::

ለጥያቄዎቹ መነሣት ዋንኛ ምክንያት ወይም ምንጭ የሆኑ ነገሮችን በማሳየት ዘለቄታዊ ምላሽ መስጠት (ማንም በቅንነት ተቀበለውም አልተቀበለው) የሚቻልበትን መንገድ መሸት (ማሳየት) ነው የሚያስፈልገው:: ይህም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን መንገድ ማሳየትና የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓማኒነት ከምን አካያ ሊታይ እንደሚችል የሚያመለክት መመሪያ (Principle) የመስጠት ሁኔታ ነው::

1. መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ደራሲዎች አሉት:: የመልእክቱ ደራሲ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን፣ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ገጽታው ነው:: መልእክቱን በሰው ቋንቋ በልዩ ልዩ የአጻጻፍ መንገዶች /ሥነ ጽሑፍና ስልተ አጻጻፍ /በሕዝቡ ባህልና ታሪክ እንዲሁም አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው በጽሑፍ ያሰፈሩ ደራሲያን ቅዱሳን ሰዎች ናቸው:: ይህ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ሳይሆን፣ ሰብአዊ ገጽታው ነው::

2. መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ቋንቋ፣ እንደ ታሪክና ባህል ባሉ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ የተጻፈ

የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ስለዚህ፣ መልእክቱ (መለኮታዊ ገጽታው) ነው ፍጹምነትን ሊላበስ የሚችለው እንጂ፣ ሥነ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍ ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ልዩ ልዩ የአሃዛትና የስም የቦታ...ወዘተ መረጃዎች ፍጹምነትን ሊላበሱ አይችሉም:: ሰብአዊ ገጽታዎች ናቸውና::

3. ስለዚህ፣ የቦታ፣ የስምና የአሃዛት ልዩነት መከሰቱ እንግዳ ነገር አይደለም፤ ጸሐፊዎቹ የተሰጣቸውን መለኮታዊ መልእክት በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋና በሥነ ጽሑፍ በኩል ስለሚያስተላልፉ፣ በዚያም ዘመን መረጃዎችን እንደ ልብ የማግኘትም ሆነ ወዲያው የመዘገብ ሁኔታ ስለ ሌለ፣ እስኪዘገብም ድረስ በትውስታ መልኩ ወደ ቀጣዩ ትውልድ ስለሚተላለፍ፣ መዘገብ በሚጀመርበት ጊዜ የቦታ፣ የስምና የአሃዛት ልዩነት ሊፈጠር ይችላል::

4. ሆኖም ይህ የመለኮትን መልእክት አይለውጠውም:: ሰባክም ሆነ ሾፌክ፣ ፈረሰኛም ሆነ እግረኛ እንዲሁም 7000 ሆነ 700 መልእክቱ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አያስከትሉም:: የመለኮታዊ ገጽታው ክፍል አይደሉምና:: መለኮታዊ ገጽታው፣ ሙሉ በሙሉ የመለኮት ሥራና ኀላፊነት ነውና::

5. አራት ሺህ ጋጥም ሆነ አርባ ሺህ ጋጥ፣ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ፈረሰኛም ይሁን ሰባት ሺህ ፈረሰኛ፣ ከቁጥር /አሃዝ/ ልዩነት በቀር፣ መሠረታዊ መልእክቱን ሊነኩም ሆነ ሊለውጡ አይችሉም::

6. በተመሳሳይ መልኩ 'አስቤል' ወይም 'ይድኤል' ተብሎ ይጠራ፣ ከብንያም ልጆች አንዱ እርሱ የመሆኑ እውነታን አይለውጠውም:: 'ማዕሴትም' ትባል 'ቤሴሞት'፣ ቁምነገሩ ከእስማኤል ልጆች አንዷ እርሷ የመሆንዋ ጉዳይ ነው:: በኬብሮን ለዳዊት ሁለት ልጆች የተወለዱለት መሆኑ ዓብይ ጉዳይ ነው:: የጆቹ ስም «አይኖንና ደሉካያ» ይሁን ወይም «አይኖንና ዳንኤል ይህ እውነታው ላይ የሚጨምረውም ሆነ ከእውነ ታው የሚቀንሰው ነገር የለም:: በተለይም፣ አሃዛት ስለ እግዚአብሔር



የደኅነትን ሥራ፣ ስለ መዳንና መንግሥተ ሰማያት ስለ መግባት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ማወቅና መጠበቅ፣ በዚህም የሚገኘውን ጥቅም ስለ ማግኘትም ሆነ ስለ ማጣት፣ የሚተዉልን (የሚሰጡን) ፋይዳ የለም:: የእግዚአብሔርን መለኮታዊ መልእክት ለመለወጥ የሚያበቃ ነገር ከቶ የለበትምና::»[41]

## የስም፣ የአሃዛትና የቦታ ግጭቶችን አስመልክቶ የተሰጠ ተጨማሪ ማብራሪያ

1. ለዚህ ችግርና ጥያቄ በዋነኝነት ልንሰጥ የሚገባው መልስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹምነቱ የሚለካው ከመለኮታዊ መልእክቱ አንጻር ስለሆነና የአሃዝና የስም፣ እንዲሁም የቦታ ግጭቶች መለኮታዊ መልእክቱ ላይ ቅንጣት ታህል ተጽዕኖ አያሳድሩም የሚል ነው:: በቀጣይነት የሚከተሉትን እውነታዎች መመልከት ይጠቅማል::

2. አንድ ታሪክ በሁለት ጸሐፊያን በሚቀርብበት ጊዜ ለጽሑፋቸው እንደሚጠቀሙበት መረጃ፣ እንደ ጸሐፊዎቹም ትኩረት መለያየት መጠን፣ በሚጽፉት ለየቅል በሆነ ጽሑፍ ውስጥ መጠነኛ ልዩነት ሊፈጠር መቻሉ የተረጋገጠ ነገር ነው:: ታዲያ ይህ መጠነኛ ልዩነት የሥነ መለከት ልዩነት እስካልሆነና በሥነ መለኮታዊ እሳቤ ላይ ለውጥ እስካላስከተለ ድረስ፣ እንደ አንድ መሠረታዊ ችግር መታየት አይችልም::

3. እነዚህ የአሃዛት፣ የስምና የቦታ ልዩነቶች ሁልጊዜ እንደ መጠነኛም ችግር እንኳ ሊታዩ የማይችሉበት ሁኔታ አለ:: ለምሳሌ ያህል፣ ኢየሱስ በእስራኤል ምድር በሚመላለስበት ጊዜ ብዙ ስፍራዎችን በተለያዩ ጊዜ መርገጡ የታመነ ነው:: ታዲያ በእነዚህ ስፍራዎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት

[41] እነዚህ የአሃዛትና የስሞች እንዲሁም የስፍራዎች መግለጫዎች ሰብአዊ ገጽታዎች ብቻ ስለሆኑ ከመለኮታዊ መልእክቱ ጋር የሚደመሩ አይደሉም:: አስቀድመን እንደ ተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኔነት የሚለካው ከመለኮታዊ ገጽታው አንጻር መሆኑን እንደገና ልብ ልንለው ይገባል::

ሲያልፍ፣ ተመሳሳይ ተአምራትን በአንድ ቦታ ላይ ሊፈጽም ቢችልና አንዱ የወንጌል ጸሐፊ በአንድ ስፍራ ላይ አንድ ዕውር በራ ብሎ ቢጽፍ፣ ሌላው ደግሞ በዚያው ስፍራ ላይ ሁለት ዕውር በራ ብሎ ቢጽፍ፣ ሁለቱም ልክ የማይሆኑት ምክንያት ይኖራል ወይ? በፍጹም ልክ ሲሆኑ መቻላቸው እሙን ነው:: (ተመልከት) ምክንያቱም፣ በመተሳሳይ ስፍራ ላይ በመጀመሪያ ሁለት፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ዕውር አብርቶ ይሆናልና:: አንዱ ጸሐፊ የአንድ ቀን ሥራውን፣ ሌላው ጸሐፊ ደግሞ የሌላውን ቀን ሥራውን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማግኘት ችሎው ወይም ለመጠቀም መርጠው ይሆናልና::

## ረ. የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ቆንጽሎ መውሰድ

ሙስሊሙ ጸሐፊያን ግራ ከሚጋቡባቸው ወይም ግራ ለመጋባት ራሳቸውን ከሚያዘጋጁበት ነገር መካከል አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ቆንጽሎ በመውሰድ፣ ክፍሎቹ በሙላት የያዙትን መልክት መሳት ወይም መቀነስ ነው::

ሊወሰድ የሚችል ልጅን መለየት (Discern) አልመቻልና የጨነገፈ መልእክት ወይም መረጃ ለማየት መጋለጥ ትልቁና ዋነኛ የሚፈታተናቸው ነገር ነው::

ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት:- እዚህ ላይ ከሳዲቅ መሐመድ አህመድ፣ «ላለመደናገር ማመሳከር» ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ አሳቦችን እናያለን::

1. ጸሐፊው፣ ከመሳፍንት መጽሐፍ ምዕራፍ 9፣ ከቁጥር 7 - 13 ያለውን ክፍል ይወስዱና:- «በዛፎች ዙሪያ ንጉሥ ለመምረጥ የተደረገ ውይይት» የሚል ርእስ ይሰጡታል:: ይህን ርእስ በንዑስ አንቀጽ «ቀ» ውስጥ ያስቀመጡት ሲሆን፣ መጋቢ አሳቡ መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ አስደናቂና አእምሮ ሊቀበላቸው የማይችሉ ነገሮችን ማቀፉ የሚል ነው:: እንደምታውም በዚህ ምክንያት ሙስሊሞች እነዚህን መጻሕፍት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ያሉ መጻሕፍት፣ ሙሉ በሙሉ የአላህ ቃል (የፈጣሪ



ለማለት የታሰበ ይመስላል) ናቸው ብለን እናምንም የሚል ነው (ገጽ 20)::[42]

2. ከዘፍጥረትና ከዘጸአት መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አምላክ በስድስት ቀን ውስጥ የፍጥረት ሥራውን ሁሉ የጨረሰበትንና በሰባተኛው ቀን ያረፈበትን መልእክት የያዙ ክፍሎች ይወስዱና (ዘፍ. 2:1-2፣ ዘጸ. 31:17) አምላክ ድካም አልተሰማውም ወይስ ዕረፍትና መተንፈስ አስፈለገው? የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ:: እንደምታው መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ እንደሚደክመውና ከዚህ የተነሣም ዕረፍት ያስፈልገዋል ሲል ያስተምራል የሚል ነው::

3. ጸሐፊው፣ «እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ አዘነ /ተጸጸተ/ /ዘፍ. 6:6/ የሚለውን ክፍል በመውሰድ የሚከተለውን ትርጉም ወይም ማብራሪያ ይሰጡበታል:: በመጨረሻም፣ በክፍሉ ላይ ጥያቄ ያነሣሉ:: በመሠረቱ ተጸጸተ ማለት አንድ ሰው አንድን ድርጊት ያደርግና በኋላ ያደረገው ድርጊት በጠበቀው መልኩ ሳይሆንለት ሲቀር፣ ይጸጸታል:: ይህ ደግሞ ለሰው የተገባ ባሕርይ ነው:: ምክንያቱም፣ ሰው የማንኛውም ነገር ፍጻሜ አስቀድሞ ማወቅ አይችልምና:: አምላክ ግን ሁሉን የሚያወቅ ጌታ ስለሆነ፣ በሚሠራው ሥራ አይጸጸትም:: ታዲያ አምላክ ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ ማለት አግባብነት አለውን?
4. እግዚአብሔርን ስለ ማየት የሚናገሩ ክፍሎችን፣ ለምሳሌም ያህል ያዕቆብ እግዚአብሔርን ያየበትን ሁኔታ (ዘፍ. 32:30)፣ ሙሴና የእስራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ያዩበትን ሁኔታ (ኢሳ. 6: 1-5)፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ፊቱን ሳይሆን፣ ጀርባዉን ታያለህ፣ ያለበትን ሁኔታ (ዘጸ. 33:23)፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በተቈጣቸው ሕዝብ ላይ «በጠላት ፊት እንድ ምሥራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ፣ በጥፋታቸውም ቀን ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አላሳያቸውም» ብሎ የተናገረበትን ሁኔታ (ኤር. 18:17) በመውሰድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ

---

[42] ሳቂቅ አህመድ፣ ላለመደናገር ማመሳከር፣ ገጽ 20::

እግዚአብሔር የሚታይ ነው ብሎ እንደሚናገር፣ ነገር ግን እውነተኛ አምላክ ደካማ በሆነ በፍጡራን ዓይን ሊታይ እንደማይችል፣ ይናገራሉ:: በአንድምታውም የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት ወይም ቢያንስ ቢያንስ ስለ አምላክ ምንነት፣ በተለይም ስለ መታየትና አለመታየቱ ስለሚያስተምረው እውነት ያላቸውን ጥረጣሬም ሆነ ትክክለኛ አይደለም የሚል አሳብ ግልጥ ለማድረግ ይሞክራሉ (ገጽ 71-73)::[43]

5. የኢየሱስ ክርስቶስ (የወልድን) ልጅነት ሲቃወሙ «አምላክ ልጅና ሚስት አያስፈልገውም» ብለዋል:: ሲዘረዝሩትም፣ «ማንኛውም ሰው፣ ልጅ የሚያስፈልገው ካረጀ በኋላ ልጁ የአባቱን ቦታ ተክቶ እንዲጦረው ወይም ደግሞ ከሞተ በኋላ አባት ትቶት የሚሄደውን ንብረት የሚወርስለት ሰው ስለሚያስፈልገው ነው:: እሳህ ግን የሚያረጅ ወይም ደግሞ የሚሞት አምላክ አይደለም:: (አል ፋርቃን 58)» ስለዚህ፣ ለእርሱ ልጅ አያስፈልገውም:: (ገጽ 73-74) ይላሉ:: በመቀጠልም፣ መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ልጅ እንዳለው ይናገራል፣ ለዚህም ዘጸ. 4:22፣ 1ኛ ዜና 22:10 ኤር. 31:9፣ ኢሳ. 54: 4-5፣ ሕዝ. 23:1-4 ማስረጃ ብለው ያቀርባሉ:: በዚህም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን አጠያያቂ ለማድረግ ይሞክራሉ:: እዚህ ላይ ሱለይማን ሙፊሲርም፣ የሚጨምሩት ነገር አለ::[44]

**የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ቆንጽሎ የመውሰድ ልምምድንና አደገኛነቱን አስመልክቶ የተሰጠ መልስ**

ስለ ዛፎች ወይይት የተሰጠ መልስ

መሳፍንት (ምዕራፍ 9ን) ስንመለከት በሕዝቡ አማካይነት በደል የደረሰበት ኢዮአታም የተባለ ሰው ሰባ

[43] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 71-73::

[44] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 73-74:: ሱለይማን ሙፊሲር ፣ ኢየሱስ በቁርዓን፣ ገጽ 7:: ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅና ራሱ እግዚአብሔር በማለት የሥላሴ መርኆ ታራምዳለች:: ማለትም እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ እግዚአብሔርን በአንድ ጊዜ እንደ ልጅ፣ አባትና መንፈስ ቅዱስ ብላ ታቀርባለች::



የሚሆኑ ወንድሞቹ በአቢሜሌክ ተንኮልና ሤራ ታርደው በተገደሉበት ጊዜ በሤራው ተካፋይ ለነበሩ ሰዎች በላያቸው ሊነግሥ የወደደውና እነርሱም ንግሥናውን የተቀበሉለት አቢሜሌክ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ለማመልከት ነው በዚያን ዘመን የነበረ ተረት በመጠቀም መልእክት ሊያስተላልፍ የወደደው:: አቢሜሌክን የሚወክለው የዛፎች ገጸ ባሕርይ የእሾህ ዛፍ ነው:: እሾህ የሚወጋና የማይመች ነው::

ስለሆነም፣ ለንጉሥነት የመረጣችሁት ሰው አይመችም፣ ምርጫችሁ ትክክል አይደለም ነው የሚላቸው:: ይህን ተረት ወስዶ በውስጡ ሊተላለፍ ያሰን መልእክትና መልእክቱን ለማስተላለፊ መነሻ የሆነ ታሪካዊ ሁኔታን ቈርጦ ማውጣት ወይም ቸል ማለት፣ ልክ ዘጠነኛ ወሩን ያለደፈነ ፅንስን ለማስጨንገፍ እንደሚደረግ ያለ ሙከራ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማድረግ ሲሆን፣ ድርጊቱ ተገቢ ያለሆነና ሥነ ትምህርታዊ ያልሆነ (Non – Academic) ልምምድ ነው:: እንደዚህ ዓይነቱን ተግባር ያገሬ ሰው ያላዋቂ ሳሚ...ይለዋል::

መጽሐፍ ቅድስ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት የሚነግረን ብዙ ነገር አለው:: የአንድን ሰው ወይም ሕዝብ ጅማሮ ብቻ ሳይሆን ፍጻሜውንም አስቀድሞ ያውቃል:: ለምሳሌ የትንቢት መጻሕፍት እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ያሉ ክስተቶችን ሁሉ ይዘዋል:: እነዚህ ትንቢቶች በእግዚአብሔር የተሰጡ ስለሆኑ፣ የእርሱን ሁሉን አዋቂነት ያመለክታሉ::

«ቃል ኪዳኔ ከአንተ ጋር ነው፣ ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ:: ከዛሬ ጀምሮም እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፣ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለው:: እጅግም አበዛሃለሁ:: ሕዝብም አደርግሃለሁ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ::» (ዘፍ. 17: 4-6)

«የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፣ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ::» (ኤር. 1:4-5)

«ብሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። እጁንም የሚከለክላት ወይም ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።» (ዳን. 4:35)

«አሁንም ይህችን መዝመር ለእናንተ ጻፉ፣ ለእስራኤልም ልጆች አስተምሩዋቸው። ይህችም መዝሙር በእስራኤል ላይ ምስክር ትሆንልኝ ዘንድ በአፋቸው አድረጓት፤ ለአባቶቻቸው ወደ ማልሁላቸው ወተትና ማር ወደምታፈሰው ምድር ካገባኋቸው በኋላ ከበሉም ከጠገቡም ከደነደኑም በኋላ ሌሎችን አማልክት ተከትለው ያመልካሉ። እኔንም ይንቃሉ፣ ቃል ኪዳኔንም ያፈርሳሉ። ዛሬ ወደማልሁላቸው ምድር ገና ሳላገባቸው የሚያስቡትን አሳብ አውቃለሁና። ብዙ ክፉ ነገርና ጭንቀት በደረሰባቸው ጊዜ ይህች መዝሙር ምስክር ሆና በፊታቸው ትመሰክራለች።» (ዘዳ. 31: 19-21)

እንግዲህ፣ «እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ» ብሎ የእግዚአብሔር ቃል በሚናገርበት ጊዜ «ሰው ከተፈጠረ በኋላ ምን ሊያደርግ እንደሚችል አስቀድሞ አለማወቁንና ያሰበው ነገር በድንገት በገጠመው ጊዜ ማዘኑንና መቆጨቱን እንደሚያመለክት መታሰብም ሆነ መቈጠር የለበትም።

ነገር ግን፣ ከሰው ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት (የፈጣሪና የተፈጣሪ፣ የአምላኪና የተመላኪ፣ እንዲሁም የአባትና የልጅ ግንኙነት) ማድረግን የሚወድድ እግዚአብሔር የሰው ልጆች እጅግ ክፉና የማይመቹት እየሆኑ ሲሄዱ ከእርሱም ጋር ያላቸውን ኅብረትና ግንኙነት በጣም ያበላሹት ሲሄዱ ለእነርሱ ካለው መልካም አሳብና ፍቅር የተነሣ ማዘኑን ነው፣ የሚያመለክተን።

ስለ ሰንበትና የመለኮት ዕረፍት

ቅዱሳት መጻሕፍት (ከላይ ስለ ሰንበት የተጠቀሱ ክፍሎች) እግዚአብሔር አምላክ የፍጥረት ሥራውን ሁሉ በስድስት ቀን ውስጥ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ ሲሉ ነው የሚነግሩን። ሰባተኛ ውንም ቀን ቀደሰው ወይም ስራሱ የሚሆን ቀን አድረጎ ለየው ነው የሚሉን።



አንድ ሰው ሥራውን ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ ማረፉ፣ የግዴታ መድከሙን ወይም መተንፈስ መፈለጉን አያመለክተንም፤ በእርግጠኝነት ግን ሥራውን ስለ ጨረሰ ማረፉን ወይም መሥራት ማቆሙን ያመለክተናል።

እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ ሁሉንም ሥራውን ሠርቶ ጨርሷል። ሥራው ስላለቀ ማቆም ነበረበት። በሌላ አባባል ማረፍ ነበረበት። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ያረፈው ከዕረፍት ተመልሶ ኃይሉን አሳባስቦ የጀመረውን ነገር ለመጨረስ ሳይሆን ሥራው ስላለቀ ነው።

በስምንተኛው ቀን አዲስ ሥራ ጀምሮ ቢሆን ወይ ም የጀመረውንና ያቋረጠውን ሥራ ለመፈጸም ተነሥቶ ቢሆን ኖሮ፣ ለመሆኑ አምላክ ይደክማል ወይ? የሚል ጥያቄ ማንሣት ተገቢ በሆነ ነበር።

እግዚአብሔርን ስለ ማየት

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ፣ መንፈስ ደግሞ ሥጋና አጥንት እንደ ሌሰው በግልጥ ያስተምራል (ዮሐ. 4:24፤ ሉቃስ 24:39)። በተጨማሪም፣ እግዚአብሔርን ያየ (በሥጋ አይኑ ያየ) ማንም እንደ ሌሰ በማያሻማ መልኩ ሲያብራራ፣ «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ ተረከው።» (ዮሐ. 1:18) ይላል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ይታያል ብሎ እንዳስተማረ ተደርጎ የመቈጠሩ ሁኔታ አሳዛኝ ነው።

ስለ አንድ እውነት ወይም ጕዳይ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰን ለመናገር በምንፈልግበት ጊዜ፣ ስለ ጕዳዩ በቀጥታም ባይሆን እግረ መንገድ የሚናገሩ ወይም የሚናገሩ የሚመስሉ ክፍሎችን በመጥቀስ ለመናገር ወይም ለመጻፍ መሞከር፣ ከሙሉው የመጽሐፉ አሳብ

ውስጥ ጥቂት ነገሮችን ብቻ ቆንጽሎ የመውሰድ ልምምድ ነው።

ኢሳይያስ፣ እግዚአብሔርን ያየበት ሁኔታ በራእይ አማካይነት ነው፡ ሙሴና የእስራኤል ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን ያዩበት ሁኔታ ክብሩንና ግርማውን ያዩበትና የተለማመዱበት ሁኔታ ነው። ለምሳሌ ሙሴ፣ በእሳት ቍጥቋጦው መሀል የእግዚአብሔር መልአክ በታየው ጊዜ፣ እግዚአብሔርን አይቶት ነበር። ይህን መገለጥ የዘፍጥረት ጸሐፊ እንደ እግዚአብሔር መገለጥ ወይም መታየት ቈጥሮት እንመለከታለን። ይህንንም፣ «ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶ ነበርና ፊቱን ሸፈነ» /ዘጸ. 3፡6/ ሲል ይገልጠዋል።

አምላክ ልጅና ሚስት አያስፈልገውም ስለሚለው

እዚህ ላይ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ። እነርሱም፡-

- ኢየሱስ ከማርያም በተወለደ ጊዜ አይደለም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው። ልጅነቱ ከዘላለም የሆነ ነው።
- በተወለደ ጊዜ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረው ቃል ሥጋ (ሰው) ሆነ (ዮሐ. 1፡1-14)።
- ስለዚህ፣ ልጅነቱ በዋንኘነት የሚያመለክተን ግንኙነትን፣ ማለትም ዘላለማዊ የሆነ ግንኙነትን ነው
- እዚህ ላይ አብ ማርያምን እንደ ሚስትነት ተጠቅሞ ልጅ እንደ ወለደ (ኢየሱስን) ልናስብ አይገባንም። ምክንያቱም፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በማርያም ማኅፀን ውስጥ እንደ ተፀነሰና እንደ ተወለደ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትም ይሁን በቁርዓን ትምህርት ውስጥ ግልጥ የሆነ ጉዳይ ነውና።

ስለሆነም፣ በሰዎች ልማድና ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመሥርተን እግዚአብሔር (አምላክ) ልጅ አያስፈልገውም ልንል አንችልም። ይልቁንም፣



ልጅነትንና አባትነትን ከምድራዊ ትርጕማቸው በመጠቀም ሆነ በጠለቀ የመጽሐፍ ቅዱስ እሳቤና ትርጓሜ ውስጥ ሆነን መመልከት ይኖርብናል። ይህም፡-

- ዘላለማዊ የሆነ የማይነጣጠል ግንኙነት፣ በመለኮት አንድነትና በአካል ሦስትነት ላይ የተመሠረተና የሥራ ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ነው።

### III. ስለ እስልምናና ስለ ሙስሊም ጸሐፊያን ማወቅ የሚገቡን መሠረታዊ ጉዳዮች

#### ሀ. የእስልምና ሃይማኖት ብዙ ነገሮችን በአይሁድ እምነትና ከክርስትና እምነት የመውሰዱ ሁኔታ፣

-በመጀመሪያ ሙስሊሞች ከአይሁድ እምነት የወሰዱአቸውን ነገሮች እንመልከት።

ሃይማኖታዊ መተጣጠብ ከአይሁድ እምነት የተወሰደ ነው። አወሳሰዱ በቀጥታ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ለአዲሱ እምነት (እስልምና) የሚመች መልኩ ነው።

ስግደትና አቅጣጫው ከአይሁድ እምነት የተወሰደ ነው። አወሳሰዱ በመጀመሪያ በቀጥታ ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም ነበር የሚሰግዱት። በኋላ ወደ መካ ተለውጦአል። ይህ እንግዲህ የፊተኛዪቱ ትእዛዝ በኋለኛዪቱ ትእዛዝ በሚሻርበት አሠራር (Abrogation) የተከናወነ እንደሆነ ነው የሚነገረው።[45]

«የአንድ አምላክ አስተምህሮ»፣ ከአይሁድ እምነት የተወሰደ ነው። ከአይሁድ እምነት በፊትም ሆነ በኋላ ለረጅም ዘመናት መላው ዓለምም ሆነ የዓረቡ ዓለም የሚለማመደው አምልኮ የብዙ አማልክት የሚመለከብት (Polytheism) አምልኮ መሆኑ ግልጥ ነበርና። (ዘዳ. 6፡4)

---

[45] ነቢዩ መሐመድ ሴትየዋ እንዳለችው ወደ ኢየሩሳሌም በቤቱል ቤተ መቅደስ ይሰግዱ ነበር። በኋላም ወደ መካ እንዲዞሩ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸው በስግደት ላይ እያሉ ወደ መካ ዞሩ። ቀመር ሁሴን፣ ሥሕተትንመመለስ- አሪት ወንጌልንና ቁርዓንን በመጥቀስ።

**የብሉይ ኪዳን ነቢያትን እንዳለ ወስደው ነው የራሳቸው ነቢያት ያደረጉዋቸው።**

**-ብመቀጠልም ከክርስትና እምነት የወሰዱዋቸውን ነገሮች እንመለከታለን።**

**ሃይማኖታዊ በዓላትን ከክርስትናው በመመልከት እስላማዊ በዓላትን የማዘጋጀት ሁኔታ ለምሳሌ የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በነቢዩ መሃመድ ልደት በዓል የመለወጥ (Substitution)፣**

**የጾም ልምምድ ከክርስትና እምነት የተወሰደበትና እስላማዊ ትርጉም (እስላማዊ ይዘት) የተሰጠበት ሁኔታ፣ ለዚህ በቂ ማስረጃ ይሆናል።**

**ለ. ቁርዓን ስለ መጽሐፈ ቅዱስ ስለ አይሁድ እምነትና ስለ ክርስትና እምነት ትክክለኛነት መመስከሩ**

**የእስልምና ሃይማኖት መሥራችም ሆነ ታላቅ ነቢይ የሆኑት ነቢዩ መሃመድ በአይሁድ እምነት፣ በክርስትና እምነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አሉታዊ አመለካከት ያልነበራቸው መሆኑን፣ይልቁንም በመልእክታቸው በቁርዓን ውስጥ ብዙ ስፍራ ላይ ከሞላ ጐደል አዎንታዊ አመለካከትና ምላሽን በአይሁድ እምነት፣ በክርስትና እምነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መስጠታቸው ግልጥ ነው።[46]**

**ሐ. ሙስሊም ጸሐፊያን ከታላቁ ነቢያቸው የተሻለ ያውቁ ይመስል የአይሁድ እምነትንና የክርስትና እምነትን ብሎም መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተሳሳተ ወይም ብዙ ስሕተት እንዳለበት መቍጠራቸው።[47]**

**ሙስሊም ጸሐፊያን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው እጅ ገብቶበታል፤ ስለዚህም፣ ተበርዟል (Corrupted) ሲሉ መናገርና መጻፍ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ለመበረዙ ማስረጃ አድርገው አንዳንድ ግራ የገባቸውንና ለአእምሮአቸው የከበዳቸውን ነገር ሁሉ ለመጠቃቀስ ብሎም ለመተንተን ሞክረዋል።[48]**

**መ. ሙስሊሞች ቁርዓንን እንደ ፍጹም እውነት በመውሰድ እስልምናን የአይሁድም ሆነ የክርስትና እምነት ስሕተቶች ማስወገጃ /Correction/ አድርገው መመልከታቸው**

**ሙስሊም ጸሐፊያን፣ ነቢዩ መሃመድ የተላኩት አይሁዶችና ክርስቲያኖች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ያስገቡዋቸውን ስሕተቶች ለማረም እንደሆነ ያስባሉ።**

**ስለዚህ፣ ቁርዓን ከስሕተት የፀዳ፣ የአይሁድንም ሆነ የክርስትና እምነት መጻሕፍትን የተካም ሆነ ያረመ እንደሆነ ያስተምራሉ። ስለዚህም፣ መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ ሳይሆን በቁርዓን ትምህርት መስፈርትነት ለመለካት ይሞክራሉ።**

**መጽሐፍ ቅዱስ የእራሱ የሆነ መገለጥና የመገለጥ አመጣጥ፣ የአጻጻፍ መንገድ (ልዩ ልዩ ሥነ ጽሑፍ) የተጻፈበት ሂደት፣ የትርጉም ዘዴ...ወዘተ ያለው ቢሆንም በራሱ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን መመልከት ትተው በቁርዓን መገለጥና የመገለጥ አመጣጥ እንዲሁም የጽሑፍ ሂደት...ወዘተ ለመመልከት ሲቸገሩ ይስተዋላሉ።**

**ሠ. ለክፍል ሦስት-ለእነዚህ እስተሳሰቦች የተዘጋጀ መልስ**

[46] በፊለጎቻቸውም(በነቢያቱ) ላይ -የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን። ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት-በስተፊቱ ያለቸውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው። የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አ ላህ ባወረደው ሕ ግ ይፍረዱ። አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጠኖቹ እነርሱ ናቸው። (ቁርዓን 5፡ 46-47)-ሱለይማን ሙፈሰር፣ ኢየሱስ በቁርዓን፣ ገጽ 4።

[47] በመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዞአል የሚለው አሳብ ከቁርዓንም ሆነ ከነቢዩ መሀመድ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው።

[48] አንዋር፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 7-18 ይመልከቱ። ሙስሊም ምሁራን መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዞአል የሚለውን አይቀበሉም።

1. የእስልምና ሃይማኖት በኋላ የመጣ እንደ መሆኑ መጠን ከአይሁድ እምነትና ከክርስትና እምነት የወሰዳቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ነው።

2. ቁርዓን ስለ መጽሐፈ ቅዱስ ትክክለኛነት ብዙ ምስክርነቶችን ይሰጣል። ነቢዩ መሃመድም በክርስትና እምነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥላቻ አልነበራቸውም። ይህም እውነት በቁርዓን ውስጥ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው።[49]

ቢሆንም፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት የምናረጋግጠበት ማስረጃችን «እራሱ መጽሐፍ ቅዱስ» እንጂ ቁርዓን ወይም ሳይንስ...ወዘተ አይደለም። በዚህ ረገድ ሁለት ዋቢ ምስክርነቶችን እንመልከት:-

I. መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ 66 መጻሕፍቶችንና ብዙ ትውልዶችን፣ ብዙ ነቢያትንና የእግዚአብሔር ሰዎችን ምስክርነት እንዲሁም የሕይወት ገጽታቸውን ሁሉ የያዘ ስለሆነ፣ እነዚህ ብዙ ማለትም 66 መጻሕፍት፣ ከአርባ የማያንሱ ጸሐፊያን፣ መገለጡ የመጣላቸው በብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ በየፈርጅ ያለፉ ትውልዶች፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮችና ነቢያት...ወዘተ ሁሉ ሕያው የሆኑ ምስክሮቹ ናቸው።

II. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መገለጦች በሰዎች ታሪክ ውስጥ የተገለጡ፣ የሠሩና ለወጥ ያመጡ ስለሆኑ፣ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው የሆነ የታሪክ ምስክርነት ያለው መጽሐፍ መሆኑን ያረጋግጥልናል።

iii. ሙስሊም ጸሐፊያን መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ መጽሐፍ ስለ መሆኑ ይናገሩ፣ መበረዙንም ለማሳየት አንዳንድ የሚመስሉ ነገሮችን ለመጠቃቀስ ይሞክሩ እንጂ አለ የሚሉትን ብርዛት ሳይንሳዊና ተጨባጭ በሆነ መልኩ ሲያቀርቡ አይታዩም።

[49] ዶ/ር ሐሰን ኢም በዐጌል፣ ክርስቲያን ሙስሊም ወይይት፣ ገጽ 8።



ሲረዱት ያልቻሉትንና ግራ የገባቸውን እንዲሁም የከበዳቸውን እውነት ጠይቆ ከመረዳት ይልቅ ተበርዟል ማለትን ፋሽን አድረገውታል ወይም ይመርጡታል።

በመሠረቱ፣ አንዳንድ ሙስሊም ምሁራን መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚለውን አሳብ አይቀበሉትም። ምክንያቱም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ገና ከጥንቱ ከጠዋቱ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በመጣ መገለጥ ሳቢያ የተጻፈ ስለሆነ፣ መገለጡ የመጣለት ሕዝብ በጥንቃቄ ጠብቆ ያቆየው በመሆኑ፣ በተለይም ገና ሳጥንት ከጠዋቱ ወደ መላው ዓለም በብዙ ቅጂ የተሠራጨ እንዲሁም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ የተሠራጨ በመሆኑ ነው።[50]

ሆኖም፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ ዋናው ማስረጃ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከ40 ያላነሱ ጸሐፊያን፣ በ1600 ዓመታት ውስጥ ያለፉ ጸሐፊያን፣ እንደ የሕግ መጻሕፍት አዋቂ ባለ ሊቅ እንደ አሣ አጥማጅ ባለ ሰው፣ በልዩ ልዩ የእውቀት ደረጃ ላይ ባሉ ጸሐፊያን የተጻፈ ቢሆንም፣ ሁሉም ስለ አንድ ታላቅና መሠረታዊ እውነት ለመጻፍ መቻላቸው መለኮታዊው ደራሲ (የመልእክቱ ባለቤት) ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ የተነገረው እውነትን፣ ትክክለኛነት ያረጋግጥልናል።

አንዱ ታላቅ እውነትም:-

- የእግዚአብሔር የደኅንነት ኘሮግራም፣ ማለትም:-
- የመሢሑ መምጣትና የእግዚአብሔርን የደኅንነት ፕ ሮግራም መፈጸም ነው።

[50] በፈለጎቻቸውም(በነቢያቱ) ላይ -የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን። ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት-በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው። የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አ ላህ ባወረደው ሕ ግ ይፍረዱ። አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጠኞቹ እነርሱ ናቸው። (ቁርዓን 5፡ 46-47)-ሱለይማን ሙፈሰር ኢየሱስ በቁርዓን፣ ገጽ 4።

ይህን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በግልጥም ሆነ በአንድምታ ሁሉም ጸሐፊያን ዳስሰውታል:: ሁሉም ይህን ታላቅ እውነት ከተለያየ ገጽታ ሊያቀርቡት ወድደዋል (አቅርበውታል):: ለምሳሌ ወንጌላውያኑ አንዱን ወንጌል በተለያየ እእይታ (ገጽታ) አቅርበውታል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ የመልእክቱ አንድነት የመጽሐፍ ቅዱስን ታማኝነት ያረጋግጥልናል:: ስለዚህ፣ ሌሎች ምስክርነቶች ተጨማሪ ምስክርነቶች ተደርገው ነው መውሰድ (መቈጠር) ያለባቸው::

3. ነቢዩ መሃመድ ስለ አይሁድ እምነት፣ ስለ ክርስትና እምነትና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አሉታዊ ነገር ስላልተናገሩ የዘመኑ ሙስሊም ጸሐፊያን ነቢዩ ያላሉትን ወይም ካሉት ነገር ጋር የሚጋጭ ነገር መናገራቸው:-

I. ያልታመኑ ምስክር ያደርጋቸዋል፣ ሐሰተኛ ያደርጋቸዋል::
II. በቁርዓን ላይ የሚጨምሩ ያደርጋቸዋል::
III. የነቢዩም ሆነ የቁርዓን እውነተኛም ሆነ ታማኝ ተከታይ እንዳልሆኑ ይመስክርባቸዋል::
IV. ትዝብት ላይ ይጥላቸዋል:: ትችታቸውም በሥነ ትምህርት ላይ ያልተመሠረተ (non-academic) እንደሆነ ይገልጥባቸዋል::

ስለዚህም፣ እስልምናን የአይሁድና የክርስትና እምነት ስሕተቶች ማስወገጃ (Correction) አድርጎ መመልከት፣ መሠረተ቎ ቢስና ያልተገባ አጉል መንጠራራት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: ይልቁንም፣ ነቢዩ መሃመድ ብዙ ነገሮችን ከአይሁድ እምነትም ሆነ ከክርስትና እምነት መውሰዳቸው፣ ሁለት አንድምታ ያለው መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል::

i. የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት መቀበላቸውን (ተቀባይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጣቸውን) ለተተኪው ትውልድ ማስተማራቸውን፣



ii. እርሳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ይበደሩ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ከእርሳቸው (ከቁርዓን) የወሰደው ነገር አለመኖሩን፣ በዚህም ለሁለተኛው መገለጥ ሙሉነትም ሆነ ልክነት መስፈርት ካለፈለገ የመጀመሪያው መገለጥ ብቸኛ መስፈርት ሊሆን እንደሚገባ ያመለክትናል::

ምክንያቱም፣ ኋለኛው መገለጥ በፊተኛው መገለጥ ሊሰፈር (ሊመዘን) ይችላል:: ኋለኛው መገለጥ ግን የፊተኛው መገለጥ መመዘኛ መሆን አይችልም:: (ፊተኛው ኋለኛውን አያውቀውም፣ እውቅናም ሊሰጠው አይችልም፣ ኋለኛው ግን ከፊቱ የነበረውን ያውቀዋል፤ እውቅናም ሊሰጠው ይችላል::

IV.ሙስሊም ጸሐፊያን ልብ የማይሉአቸው ወይም ልብ ሊሏቸው የማይወዷቸው ጉዳዮች

ሀ. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ክፍል እንደ አንድ እውነት በመውሰድ የቁራንንና የእስልምና አስተምህሮን በማስረጃ ለማስረገጠ እየጣሩ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደ ተበረዘ አድረጎ ማሰብ:- እነዚህ ሁለት አኪያሄዶች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ተግባራት መሆናቸውን ልብ አለማለት::

አንድ መጽሐፍ የታመነ ከሆነ ሁልጊዜ የታመነ ነው ሊሆን የሚችለው:: ያልታመነ ከሆነ ደግሞ ሁልጊዜ ነው የማይታመን የሚሆነው:: ሆኖም፣ ስንፈልግ የራሳችንን ትምህርት ለማስደገፊያነት፣ ስንፈልግ ብቻ ትክክለኛ መጽሐፍ አድርገን የምንወስደውና ከመሠረታዊ ትምህርታችን ጋር የሚቃረን ሆኖ ስናገኘው ደግሞ ትክክል አይደለም የምንል ከሆነ አካያሄዳችንም ሆነ አስተሳሰባችን፣ «ሲመቸኝ በእጄ፣ ሲፈጀኝ በማንኪያ» እንደ ተባለው ያለ መሆኑን በራሳችን ላይ መመስከራችን ነው::

አንድ ጸሐፊ የታመነ ከሆነ የሚጽፈው ሁሉ እሙን መሆኑ መታወቅ አለበት:: ያልታመነ ከሆነ ደግሞ

እንደ ታመነ ምስክር ተቈጠሮ ከቶ ለማስረጃነት መቅረብ የለበትም።

**ሰ. መጽሐፍ ቅዱስን በቁርዓን እይታ ለመመልከት መሞከራቸው የዋህነት መሆኑን መዘንጋታቸው፤**

የጽሑፉ ሂደት 1600 ዓመታት የፈጀን ጥንታዊ መጽሐፍ በ10 ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከተጻፈ መጽሐፍ ጋር ለማዛመድ ከመሞከር አልፈው ኋለኛውን ከፊተኛውና ከጥንታዊው ለማስበለጥ መከጀላቸው እጅግ የሚገርም ቅጥፈትም ሆነ ዕብለት ነው።

የብዙ ነቢያትና ትውልዶችን ሕይወት የዳሰሰ፣ በብዙ ትውልዶች ሕይወት ውስጥም ተገልጠው እየሠሩ እስከ ዛሬ ድረስ በሕያውነት የኖሩ መጻሕፍትን በአንድ ሰው የሕይወት ዘመን ተገለጠ ከተባለ መጽሐፍ ጋር ለማወዳደር መሞከራቸው ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ቁርዓንን ከቶ የማያውቀው ቢሆንና፣ ቁርዓን ደግሞ ስለ መጽሐፈ ቅዱስ ብዙ የሚናገር ቢሆን፣ ደግሞም የቁርዓን ህልውና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ቢሆን፣ ይህን እውነታ ቸል ማለታቸውና ቁርዓንን የበላይ ለማድረግ መሞከራቸው እብደትም ሆነ የቁም ቅዠት መሆኑ ግልጥ ነው።[51]

[51] እግዚአብሔር በክርስቶስ እራሱን የገለጠበትን ሁኔታ አስመልክተን ስንነጋገር አጂት ፈርናንዶ የተባሉ የነገረ መለኮት አዋቂ የተናገሩትን ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። ይህም፦ ኢየሱስ እንዲሀ አለ--ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። ስም የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሲገለጥ የታሰበን የመለኮት ህሕርይ ነው። ደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል በክርስቶስ ውስጥ ተረድተውታል። ጌታ ክርስቶስ በቁጥር 26 ላይ አሳቡን ይደግመዋል። ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ።ይህን እውቀት የሚያካፍላቸው በሁለት መንገድ፦ በሕይወቱና በትምህርቱ አማካይነት ነው። Ajith Fernanedo, *Jesus Driven Ministry*, Leicester: IVP, 2002. p.154. ይህ እግዚአብሔር እራሱን የገለጠበት ወይም ቃል ሥጋ ሆኖ የመጣበት መንገድ ከሁሉ የላቀና የመጠቀ ሲሆን የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጥም (final revelation) ሆነ መገለጫ መንገድ ነው። ሰዎች ሙሉ በሙሉ መንፈስ የሆነውን እግዚአብሔርመለኮታዊ ባሕርያት በክርስቶስ (ሰው ሆኖ በተገለጠው በእግዚአብሔር ወልድ) በኩል ያለ አንዳች ገደብ ሙሉ በሙሉ ለማየት የቻሉበት ልዩ የመለኮት መገለጥ(unique revelation) ነው። ሆኖም ይህን የመጨረሻና ልዩ የሆነ የመለኮት መገለጥ በደ ኋላ ጥለው ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ትምህርትም ሆነ መልእክት ጋር ከብዙ ማዕከላዊ ጉዳዮች የሚለይ



**ሙስሊም ጸሐፊያን የሚያነሡዋቸው ተጨማሪ ጥያቄዎችና ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች**

**ጥያቄዎች**

1) ወንጌል አንድ ከሆነ ስለምን አራት ወንጌላት፦ የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ሊኖሩ ቻሉ?

2) አህመድ ዲዳት፣ «ኢየሱስ የአምላክን ባሕርይ እንደማይጋራና በምንም መልኩ እግዚአብሔርን እንደማይመስል ለማሳየት እንሞክራለን» ብለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጥቅሶችን በማውጣት የማይመስልበትን ሁኔታ ለማሳየት ከሞከሩና ከዚህ በመነሣት ኢየሱስ የአምላክን የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንደማይጋራና አምላክን እንደማይመስል በማያሻማ መልኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያረጋገጡ መሆናቸውን ይናገራሉ።[52] ስለዚህ ክርስትናም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ምን መልስ አለው?

3) የሥላሴ ፅንስ አሳብ አሁን ባለውም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ቢሆን አለተጠቀሰም። «... ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው...» የሚለው (ማር. 12:29) እና ሌሎች አባባሎች ከናካቴው አሳቡን ይቃወሙታል[53] ብለው ለተናገሩት ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊው መልስ ምንድን ነው?

4) ቀመር ሁሴን፣ ኢየሱስ ከአብ እንደሚያንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ «የምትወዱኝ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና» ይላሉ ኢየሱስ

እንዲሁም ብሉይ ኪዳን ከስሕተት የሚፈርጃቸውን ትምህርቶች መካከል ሊፈርጃቸው የሚችላቸውን ትምህርቶች ይዞ የተገለጠውን ሰውና በእርሱ በኩል የመጣውን ትምህርት የመጨረሻው መገለጥ የሚያደርጉ አልጠፉም።

[52] አህመድ ዲዳት፣ *ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን* ነጋሺ አሳታሚ፣ 1988፣ ገጽ 4-17።

[53] ዶ/ር ማንህ ሐማድ አልጀሃይኒ፣ *ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ* አዲስ አበባ- ሁዳ ፕሬስ፣ 1994፣ ገጽ 18።

በእንደበታቸው:: ይህን ካስተባበልን ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን መጽሐፋቸውን ጭምር ማስተባበላችን ነውና እናስታውስ በማለት ለማስረዳት ሞክረዋል:: ይህን በክርስትና እምነትና በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ እንዴት እንመለከተዋለን?[54]

5) ኢየሱስ እኔ አጽናኙን እልክላችኋል ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሲያብራሩ ክርስቲያኖች ቃሉ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስን ነው ይላሉ:: እስላሞች ደግሞ ይህን በመቃወም ቃሉ የሚያመለክተው «ነቢዩ መሃመድን ነው» ይላሉ:: ይህን አሳባቸውን ሲያጠናክሩትም አዲስ ኪዳን ወስጥ እንደ ተመለከትነው ሁሉ «መንፈስ ቅዱስ» ኢየሱስ ባስተማሩበት ዘመንም ነበር (ማቴ. 12:18 እና 28):: ስለዚህም፣ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ገና ወደፊት የሚከሰት ትንቢት አልነበረም::»[55] ይላሉ:: ለመሆኑ ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ ይኖረዋልን? በተጨማሪም፣ ዶ/ር ማንህአማምድ አልጀሃይኒ ጉዳዩን ሲያብራሩ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት በእርግብ ተመስሎ ነው የመጣው ሲሉ ይናገራሉ::[56] ለዚህ ያለን ምላሽ ምንድን ነው?

6) ተርጓሚ ዘካሪያ አባትነህ ወርቅነህ የትርጉም ሥራቸው በሆነው የአህመድ ሁሴን ዲዳት መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሃመድ የተናገረው ቃል) በሚለው ሥራቸው ውስጥ በገጽ 45 ላይ «መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አፈ-ታሪክ ስለመሆኑ የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1-4 የተጻፈውን መመልከት ይበቃል (ተርጓሚው) ብለዋል::[57] ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ እንዴት እንመለከተዋለን?

[54] ቀመር ሁሴን፣ *ስሕተትን መመለስ*፣ ገጽ 11::
[55] ሱሰይማን ሙፈሲር፣ *ኢየሱስ በቁርዓን*፣ ገጽ 4::
[56] ዶ/ር ማንህ ሐማድ አልጀሃይኒ፣ *ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ*. አዲስ አበባ፣ ሁዳ ፕሬስ፣ 1994 ገጽ 11::
[57] አህመድ ሁሴን ዲዳት፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሃመድ የተናረው ቃል* (ተርጓሚ ዘካሪያ አባትነህ ወርቅነህ)፣ ገጽ 45::



7) ቀመር ሁሴን፣ «ኢየሱስ ሰውን ገነት ማስገባት አልችልም ይላል» ሲሉ ከማቴ. 20:20 ማስረጃ ይሰጣሉ::[58] ለመሆኑ ይህ እውነት ነውን?

8) ቀመር ሁሴን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚጋጩ ነገሮች እንዳሉ ይጠቅሳሉ::[59] ከእነዚህም መካከል አንደኛ፣ ኢየሱስ ከአማኞች ጋር አብሮ ስለሚኖርበት ሁኔታ ሲናገር በአንድ በኩል እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ያሉ ሲሆን (ማቴ. 28:18)፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉ፣ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም ማለቱ (ዮሐ. 12፣8፣ ማር. 14:7)፣ ሁለተኛ፣ ኢየሱስ ፍርድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ሲናገር በአንድ በኩል ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር አልላከውም (ዮሐ. 3:17)፣ ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁም (ዮሐ. 12:14) ያለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣንን ሰጠው ብሏል (ዮሐ. 5:17) ይላሉ:: ለዚህ ያለን ምላሽ ምንድን ነው?

9) ኢየሱስ የኢስላም ነቢይ በሚለው መጽሐፋቸው መሃመድ አጧውርሂማ፣ የበርናባስ ወንጌል ብቸኛ ትክክለኛ ወንጌል እንደሆነ ሲናገሩ ኢየሱስ መልእክቱን ባስተላለፈባቸው ሦስት ዓመታት በአብዛኛው ከእርሱ ባለተነጠለው ደቀ መዝሙሩ የተጻፈውና በአሁኑ ወቅት ሕልውናው የተጠበቀለት ብቸኛ ወንጌል የበርናባስ ወንጌል ነው:: ማርቆስ ወንጌሉን በሚጽፍበት ጊዜ

[58] የትንቢተ ኢሳይያስ 42 እና 60 ትንቢት ስለ መካና በመካ ስለሚኖር ስግደት የተተነበየ ስግደት ነው ሲሉ የእምነታቸውን ታላቅ ልምምድ እውነተኛነት በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት ለማስደገፍ ይሞክራሉ:: (ዑመር አርሲ፣ *ታላቅ ምክር ለአሏሱ ትውልድ፡- ሁለተኛ እትም*፣ አዲስ አበባ፣ 1996፣ ገጽ 9-60::
[59] ቀመር ሁሴን፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር በሙስሊም መነጽር*፣ ገጽ 7::

«ኢየሱስን የማግኘት ዕድል ያላገኘን ግለሰብ ጳውሎስን የመረጃ ምንጭ አድርጎ ይዟል ማለት ያዳግታል:: ነገር ግን፣ እንቱ በርናባስ ስለ ኢየሱስ የነገረውን ለመጻፍ ችሏል ብንል እሳማኝ ማጠቃለያ ሊሆን ይችላል:: በርናባስ በእንቱ ቤት ለሚደረግ ግብግብ በአስተናጋጅነት ሽር ጉድ ማለቱ የማይቀር ቢሆንም አራቱ ወንጌሎች የመጨረሻውን እራት ታሪክ ሲተርኩ በርናባስ ያለመጠቀሱ እንቆቅልሽ አጠያያቂ ነው:: እንድም በአራቱ ወንጌላት ተጠቅሶ ነበር:: ነገር ግን፤ የኋላ ኋላ ሆን ተብሎ ስሙ እንዲፋቅ ተደርጓል ወይም በቦታው አልነበረም:: ምናልባትም በወቅቱ በእስር ላይ በመሆኑም በቦታው ሳይኖር ቀርቶ ይሆናል...»[60] ሲሉ ይናገራሉ:: ለዚህ የሚኖረን መልስ ምንድን ነው?

10) ሙስሊም ጸሐፊያን በተደጋጋሚ ለሚያነሡዋቸው ጥያቄዎች መልስ ይኖር ይሆን? (ብዙዎቹ በአቡ ሱመያ የቀረቡ ናቸው::[61]

ሀ. መስቀሉን ማን ተሸከመ? ስምዖን? ማቴ. 27:32፣ ማር. 15:2፣ ሉቃስ 23:26 ወይስ ኢየሱስ? (ዮሐ. 19:17)

ለ. ሦስት ሰዓት ወይስ ስድስት ሰዓት? (ማር. 15:25፣ ዮሐ. 19:14-15)

ሐ. ሐሞት ወይስ ከርቤ ነው ከወይን ጠጅ ጋር ተደባልቆ ለኢየሱስ የተሰጠው? (ማቴ. 27:34 - ማር. 5:23)

መ. መግደላዊት ማርያም ብቻ ወይስ ከሌሎች ሴቶች ጋር ወደ መቃብር የተኬደው? (ማቴ. 28:1፣ ማር. 16:1-2፣ ሉቃስ 24:10፣ ዮሐ. 20:1)

ሠ. አሥራ አንድ ወይስ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት (ሐዋርያት) ? (ማቴ. 28: 16 - 1ቆሮ. 15 - 4-5)

[60] ሙሐመድ አሚዑሪም፣ ኢየሱስ የኢስላም ነቢይ (ትርጉም ኢድሪስ ሙሐመድ)፣ አዲስ አበባ፡ ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ 1997፣ ገጽ 40-74:: በተለይም 40 43 እና 53::

[61] አቡ ሱመያ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997፣ ገጽ 40-44::



ረ. የበኩር ልጅ እስራኤል ወይስ ኤፍሬም? (ዘጸ. 4:22- ኤር. 31:9)

11) ዶ/ር ሐሰን ኤም በዐጊል ክርስቲያን «ሙስሊም ውይይት» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ «አብርሃም የመጀመሪያው ሙስሊም ነው...አብርሃም አይሁዳዊ አይደለም እርሱ ዕብራዊ ነው:: አብርሃም ከከለዳውያን ዑር የተወለደ ስለሆነ (የአሁንዋ ኢራቅ) ከአይሁድ ይልቅ ወደ ዓረብ የሚያደላ ነበር... አይሁድ የሚለው ስም የአብርሃም የልጅ ልጅ ይሁዳ በምድር ላይ ህልውናን ከገኘ በኋላ የመጣ ነው::...አይሁዶች የተባሉት የይሁዳ ልጆች ብቻ ናቸው...ሙሴም ከይሁዳ ወገን ባለመሆኑ ሌዋዊ እንጂ አይሁዳዊ አልነበረም...ወዘተ ብለዋል:: በተጨማሪም፣ ይህንን መርምረው የደረሱበት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሣት እንዳልነበረ፣ ምክንያቱም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ስለሆነ፣ ዳሩ ግን ቁርዓን ከብርዘት የነፃ በመሆኑ በቁርዓን መለኪያ መስፈርትነት እንደሆነ ይናገራሉ»[62] ለዚህ የሚሰጥ ክርስቲያናዊ መልስ ምንድን ነው?

12) ዶ/ር ሐሰን፣ «የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንኳ አይገኝም:: ኢየሱስ ስለ ሥላሴ ፈጽሞ አላስተማረም:: የሥላሴን ትምህርት ለመቀበል የሚያስችል አንድም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ወይም ማረጋገጫ የለም ...የሥላሴ ትምህርት የእስክንድርያ ተወላጅ በሆነው ግብፃዊ ዲያቆን አትናቴዎስ ተቀምሮ እ.ኤ.አ በ325 ዓ.ም በተካሄደው የኒቂያ ጉባኤ ተቀባይነት ያገኘ ነው ይላሉ? ለዚህ ያለን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ክርስቲያናዊ መልስ ምንድን ነው?

[62] ዶ/ር ሐሰን ኤም በዐጊል፣ ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ ሦስተኛ እትም 1992፣ ገጽ 5-8::

13) ዑመር አርሲ፣ «ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ» በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ 43 ላይ (1) አብርሃም ለመሥዋዕትነት ያቀረበው እስማኤልን ሆኖ ሳለ፣ አይሁዶች ይስሐቅን ነው በማለት መጽሐፋቸው ውስጥ ማስገባታቸውን፣ ይህም እውነት አለመሆኑን በመከራከሪያ ነጥብ ሲያስረዱ፦ «ነገሩ ለይስሐቅ የተባለ ቢሆን ኖሮ አላህ አብርሃምን አንድ ልጅህን አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ አይልም ነበር:: ምክንያቱም፣ በዚህ ወቅት ነቢዩ ኢብራሂም ሁለት ልጆች ይስሐቅና እስማኤል ነበራቸውና::» ብለዋል:: (2) በመቀጠልም አይሁዶች ስለ እስማኤል ያላቸውን (በሳቸው እምነት) የተሳሳተ አስተሳሰብ «አይሁዶች ግን እስማኤል የሕጋዊ ጋብቻ ልጅ ስላልሆነ ተረግሟል፣ ይልቁንም የተባረከው የይስሐቅ ዘር የሣራ ዘር እንጂ ይላሉ:: የዘፍጥረት 17:20 ላይ እግዚአብሔር ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ:: እነሆ ባርኬዋለሁ:: ፍሬያማ አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ አሥራ ሁለት አለቆችን ይወልዳል ይላል::» ይህ አባባል እርግማን ነውን? ትንቢቱም ተፈጽሞአል ይላሉ:: ለዚህ አባባላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነ መለኮታዊ መልስ ይኖር ይሆን?

14. ዑመር አርሲ፣ በዮሐ. 16:12-15 ላይ፣ «... ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል:: የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና::» የሚለውን ቃል ክርስቲያኖች ትንቢቱ ለመንፈስ ቅዱስ ነው ብለው ይሰብካሉ:: ለራሳቸው ሊቀርብ የሚገባ መሠረታዊ ጥያቄ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ከሆነ ከማን ነው የሚሰማውን የሚናገረው? ትንቢቱ በቀጥታ የሚያመለክተው ነቢዩ መሃመድን (ሰ.ዐ.ወ) ነው:: ምክንያቱም፣ በምድር ላይ ከኢየሱስ በኋላ የተነሡ የመጨረሻው ነቢይ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዓለምን ወደ እውነት ሁሉ መርተዋልና::»



ይላሉ:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ በክርስትናዊና በሥነ መለኮታዊ እሳቤ እንዴት ይታያል?

15. ዑመር አርሲ፣ በዮሐንስ ራእይ 19:11 ያለውን «ሰማይም ተከፍቶ አየሁ እነሆም አምባ ላይ ፈረስ የተቀመጠበት የታመነና እውነተኛ ይባላል በጽድቅም ይፈርዳል:: ይዋጋልም» የሚለውን ቃል በመውሰድ ይህ ስለ ኢየሱስ እንደማይናገር፣ ለዚህም ምክንያት ሲሰጡ «የዮሐንስ ራእይ ማለት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ በ98 ዓ.ም የተተነበየ በመሆኑ በማያሻማ መልኩ የሚያመለክተው ስለ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መምጣት ብቻ ነው:: ምክንያቱም፣ ከኢየሱስ በኋላ ሌላ ነቢይ አልተነሣምና:: በተለይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ፦

i. የታመነና እውነተኛ መሐመድ አሚን (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ታማኙ ሙሐመድ ከሚለው የነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) የተሰምዖ አጠራር ጋር ይስማማል::

ii. በጽድቅ ይፈርዳል፣ ይዋጋልም:: ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በትክክል ፈርዷል፤ ተዋግቷልም:: ይህንንም ሃቅ የዓለም ታሪክ ተመራማሪዎች ተገንዝበውበታል:: ነገር ግን፣ የክርስትና ሃይማኖት መመሪያ መዋጋትን ይቃወማል:: ቀኝህን ሲመቱ ግራህን ስጥ ይላል እንጂ ተዋጋ አይልም:: ይላሉ:: ይህን ከክርስትና እምነት፣ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሥነ-መለኮት ትምህርት አንጻር እንዴት እንመለከተዋለን?

16. እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ «ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለውን ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ» ሲል ለእስራኤላውያን የተናገረዋን ቃል በመውሰድ ይህ የተተነበየለት ነቢይ፣ ነቢዩ መሐመድ ስለመሆናቸው ዑመር አርሲ፣ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በመስጠት ይከራከራሉ፦

i. ነቢዩ ሙሴና ነቢዩ መሐመድ ስለሚመሳሰሉ ይህም መመሳሰል አግብተው በመውለዳቸው፣ ምድራዊ ሞት በመሞታቸውና በመዋጋታቸው እንደሆነ፣

ii. ኢየሱስ፣ በክርስቲያኖች አመለካከት ጌታ በመሆናቸው መስፈርቱን አያሟሉም፣

iii. አሳህ ቃልን በነቢዩ መሐመድ አፍ ማድረጉ፣

iv. በአሳህ ስም የሚናገሩ የመጨረሻው ነቢይ መሐመድ ብቻ መሆናቸው፣

v. የአሳህን ቃል ይዘው የመጡትን የነቢዩን ቃል ያልሰሙትን አሳህ የተበቀለላቸው መሆኑ ናቸው ይላሉ::

ለዚህ ያለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ክርስቲያናዊና ሥነ መለኮታዊ መልስ ምንድን ነው?

17. ዑመር አርሲ፣ (ኢሳ. 42 እና 60) ላይ ያሉ ትንቢቶችን ነቅሰው በማውጣት (60:1 3፣60:4-5፣60:6-7፣60:8፣60:10-12፣60:14፣60:15፣60:1722)፣(42:1፣42:4፣42:8-9፣42:12-13፣42:16-17፣42:20-22)፣ ትንቢቶቹ የሚናገሩት ስለ ጽዮን ኢየሩሳሌም ሳይሆን ስለ መካ መሆኑን፣ ስለ ኢየሱስ ሳይሆን ስለ መሃመድ መሆኑን፣ በጥቅሉ በጽዮን (በኢየሩሳሌምና) በኢየሱስ የተፈጸሙ ሳይሆን፣ በመካና በመሃመድ እንደ ተፈጸሙ አድርገው ለማሳየት ይሞክራሉ::

በማጠቃለያቸውም:- «አሁንም ደግመን ደጋግመን ስለ ሁለቱ ትንቢቶች ማለትም ኢሳያስ 42 እና 60ን በተመለከተ ክርስቲያኖችን በጥሞና የምንጠይቀው ትንቢቶቹ ተፈጽመዋልን? ከተፈጸሙ ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንጻር ሲታይ ምን ጠቀሜታ አላቸው? አፈጻጸማቸው ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንጻር ሲታይ ምን ያህል በአምልኮ ሥርዓት ውስጥ እየተሠራባቸው ነው? የማይሠራባቸው ከሆነ ለምን? የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ:: በአጠቃላይ የትንቢቶቹን ፍጻሜ አስመልክተው ለሰነዘሩት ሂስና ላነሡዋቸው ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ክርስቲያናዊና ሥነ መለኮታዊ መልስ ይኖር ይሆን?

18. ዑመር አርሲ፣ በትንቢተ ኢሳ. 60 ላይ ያለን:- «በዚያን ጊዜ የባሕሩ በረከት ወደ አንቺ ስለሚመለስ



የአሕዛብ ብልጥግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ» የሚለውን ቃል ይጠቅሱና ይህ ለጽዮን የተነገረ ትንቢት ከቶ ሊሆን የማይችልበትን መከራከሪያ ነጥባቸውን ያቀርባሉ:: «ይህም:- የባሕሩ በረከት ወደ ጽዮን መጣ ማለት አያስደፍርም:: ምክንያቱም፣ ከጽዮን የሚገኘው የጦር መሣሪያ ብቻ ነው ይላሉ::» በመቀጠልም፣ ትንቢቱ ለመካ የተሰጠ በመካም የሚፈጸም እንደሆነ ማስረጃ ጠቅሰው ያስረዳሉ:: «ይህም:- የባሕሩ በረከት የዚያን ጊዜ ማለትም ይህ ትንቢት የሚተረጎምበት ጊዜ ማለት ነው:: ታዲያ በመካ ዛሬ የሃብት ክምችት ስላለ ሰው ለሥራ ፍለጋ ወደዚያ ይሄዳል» ይላሉ:: ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር እንዴት እንንመለከተዋለን?

19. ዑመር አርሲ፣ (በገጽ 35 እና 36 ላይ) ቁርኣን በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ መከፋፈል እንደሚኖር ተንብዮአል ይላሉ:: እንደ ማስረጃም አድርገው 5:14፣42:14 እና 42:21ን ይጠቅሳሉ:: ይህንንም ለቁርኣን ትክክለኛነት እንደ ማረጋገጫ ያስቀምጣሉ:: ክርስትናም መከፋፈል ስለታየበት ይህን በበጐ ሳይሆን በአፍራሽ መልኩ ለማሳየት በብዙ ሞክረዋል:: ለዚህ ምን ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነ መለኮታዊ ምላሽ ይኖር ይሆን?

20. ዑመር አርሲ፣ (ገጽ 25-26) የሥላሴ ትምህርት ከመሠረታዊው የኢየሱስ ተልእኮ የተቃረነ መሆኑን እንዲሁም ደግሞ ከኒቂያ ጉባኤ በፊት ማለትም ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ 325 ዓ.ም የኒቂያ ጉባኤና የ381 የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ድረስ ኢየሱስ ክርስቶስ የአሳህ መልእክተኛ እንጂ ሌላ ነገር ወይም እነርሱ እንደሚሉት ከፈጣሪ ጋር እኩል ስለመሆኑ የተሰጠ ትምህርት የለም ይላሉ:: ይህንንም በማስረጃ ለማስደገፍ በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ከሚለው የይሖዋ ምስክሮች መጽሐፍ ይጠቃቅሳሉ:: ይህም በ165 በሰማዕትነት የሞተው ጀስቲን ኢየሱስ ሁሉን ከፈጠረ እግዚአብሔር የተለየና የተፈጠረ መልአክ እንደሆነ መናገሩ፣ በ200 ዓ.ም የሞተው ኢራኒየስ፣ ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ በፊት ከእግዚአብሔር የተለየና ያነሰ ህልውና እንደ ነበረው መናገሩ፣ በ215 ዓ.ም

የሞተው የእስክንድሪያው ክሲመንት፣ ወልድ አንዳች ነገር ከማይሳነው ከአብ ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ያለው እንጂ ከአብ ጋር እኩል እንዳልሆነ መናገሩ፣...ወዘተ ናቸው:: ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክና ከሥነ መለኮት ትምህርት አንጻር እንዴት እንመለከተዋለን?

21. ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ «ሦስት ቀንና ሌሊት ቆይቷል ወይስ አልቆየም?» (ሳዲቅ መሐመድ አህመድ ገጽ 157) ይህንን እንዴት ነው የምንመለከተው?

**ለተጨማሪ ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ**

1) ወንጌል አንድ እንጂ አራት አይደለም:: ወንጌል ማለት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለማዳን የሠራውን ሥራ በእምነት ብቻ በመቀበል የሰው ልጆች ዘላለማዊ ሕይወትን የሚወርሱበት መንገድ መከፈቱን የሚያበስር የምሥራች ወይም መልካም ዜና ማለት ነው::

   ይህ መልካም ዜና አንድ ሲሆን፣ በተለያዩ ጸሐፊዎች፣ ሰባኪያን ሲጻፍም ሆነ ሲሰበክ ይችላል:: ታዲያ በተለያዩ ጸሐፊዎች ስለ ተጻፈና በተለያዩ ሰባኪያን ስለ ተሰበከ አንድነቱን አጥቶ አራት ሆነ ሊባል ይችላል? በጭራሽ ይህ እውነት ሊሆን አይችልም::

   አራቱ ወንጌላውያን እንዱን ወንጌል ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ የተሠራውን የድኅነት ሥራ የምሥራች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጽፈውታል:: ስለዚህ፣ አራቱ ወንጌላት ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ በተለምዶ አራት ወንጌላት ይባሉ እንጂ አንዱ ወንጌል (የክርስቶስ ሥራ) በአራት ጸሐፊዎች በኩል የተጻፈበት (በአራት መጻሕፍት ውስጥ የተቀመጠበት) ሁኔታን ነው የምንመለከተው:: ስለዚህ፣ ስለ ወንጌል አራት ሰዎች መስክረዋል ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች አራቱም ጸሐፊዎች በጋራ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል ነው ማለት የምንችለው:: ለዚህም ነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስ እንደ ጻፈው፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ቅዱስ ማርቆስ እንደ ጻፈው፣...ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈውና ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው የሚሉ ርእሶችን በወንጌላት የመጀመሪያው ገጽ ላይ የምንመለከተው:: ስለዚህ፣ አንዱ ወንጌል በአራት ገጽታዎች እንደ ቀረበልን ማሰብ ይገባናል::

   ለምሳሌ ያህል የኢየሱስን አገ.ልግሎት አራት ገጽታዎች እንመልከት:: «የማርቆስ ወንጌል የመጀመሪያው ትኩረት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን የሞተበትን እውነት ማስቃኘት ነው:: ይህም ኢየሱስ ለብዙዎች ድነት (ደኅንነት) ራሱን የሰጠበት ሁኔታ ነው:: (ማር. 10:45) የማቴዎስ ወንጌል ዋና ትኩረት ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከሕዝቡ ጋር የመሆኑን እውነት የሚያስቃኘን ነው:: (ማቴ. 16:18-19፤ 16:18-20)

   የሉቃስ ወንጌል ዓብይ ትኩረት የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልና ሥራዎች በየትኛውም መንገድ የሠሩ ሰዎችን ነፃ የሚያወጡ መሆኑን ማሳወቅ ነው :: (ሉቃስ 4:18፤ 19:10)

   የዮሐንስ ወንጌል መሠረታዊ ትኩረት ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነት ምን እንደሚመስል መግለጡን ማሳወቅ ነው:: ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በተናገራቸው ንግግሮችና በሥራዎቹ ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚገባውን ነገር ገልጧል::

2) አህመድ ዲዳት፣ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ፩ደማይመስል፣ በምንም መልኩም የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንደማይጋራ

ለማሳየት' እንደሚማከሩም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዳረጋገጡ ይናገራሉ። ለዚህ የምንሰጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት - ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ። በሰውነቱ በምድር ላይ ሲመላለስ ምግብ ይበላ ነበር (ሉቃስ 24:41-43)። መንገድ ከመሄድ ይደክመው ነበር (ዮሐ. 4:6)። ሁሉን አያውቅም ነበር (ማቴ. 24:36) ከአብ (ፊል. 2:5-11) ከመላእክትም እንኳ በጥቂት ያንስ ነበር (ዕብ. 2:7፤9)፤ እነዚህን እውነታዎች በመያዝ ነው አህመድ ዲዳትና መሰሎቻቸው ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ባሕርይ አይጋራም ሲሉ የሚደመጡት። የክርስትና እምነት እነዚህን እውነታዎች አይሸሽጋቸውም፤ ደግሞም አያፍርባቸውም። በእነዚህ እውነታዎችም ኢየሱስ ከአብ ጋር ይመሳሰላል ብሎ አያስተምርም ወይም ኢየሱስ በእነዚህ እውነታዎች ከአብ ጋር በባሕርይ ይመሳሰላል ብሎ አያስተምርም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በአምላክነቱ ከአብ ጋር እኩል ነው። ለዚህም ነው፣ «እኔን ያየ አብን አይቷል፣ እኔና አብ አንድ ነን። አብ በእኔ እኔም በአብ እንዳለሁ አታወቁምን» (ዮሐ. 15:9-10) ሲል የተናገረው። እርሱ በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅድስ ይናገራል። ይህም «በመጀመሪያው ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር .... ቃልም ሥጋ ሆነ» (ዮሐ. 1:1-3፤14)። ይህም፣ «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም(ፊል. 2:6) በሚል ቃል ተገልጧል። ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ኃጠአትህ ተሰረየችልህ ብሎ ኃጢአትን አስተሰርዮአል። ኃጢአት ማስተሰረይ ደግሞ የአምላክ ሥራና ሥልጣን ብቻ ነው። በተጨማሪም፣ ለእግዚአብሔር አብ፣



«እውነተኛ የሆንህ አምላክ» በተባለለት መልኩ፣ ለእግዚአብሔር ወልድም፣ «እርሱ እውነተኛ አምላክ የዘላለምም ሕይወት ነው» ተብሎለታል (ዮሐ. 17:3፤1ዮሐ. 5:20)።

ስለዚህ፣ ኢየሱስ ከአብ በሰውነቱ እንደሚያንስ፣ ደግሞም በአምላክነቱ ከአብ ጋር እኩል እንደሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ፦ ሁለቱን ባሕርያቶች ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ታዲያ እውነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ፣ ስለ ሰውነቱ የተነገሩ ነገሮችን ብቻ ወስዶ፣ ስለ አምላክነቱ የሚያወሩ እንዲሁም የአብን ባሕርይ እንደሚካፈል የሚያሳዩ ስፍር ቍጥር የሌላቸው ክፍሎችን ቈርጦ ጥሎ ወይም ችላ ብሎ ኢየሱስ እግዚአብሔርን አይመስልም ባሕርይውንም አይጋራም ማለት እንዴት ይቻላል? ይህ ክህደት ነው፣ ሚዛናዊ ያልሆነ አስተሳሰብም ነው።

3) ዶ/ር ማንፅ ሐማድ አልጅሀይኒ፣ የሥላሴ ፅንስ አሳብ አሁን ባለውም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢሆን አልተጠቀሰም ሲሉ በእውነቱ ምን ማለታቸው እንደሆነ የተረዳ አይመስለኝም። «...ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው...ማር. 12:29» የሚለውንም ቃል ሲጠቅሱ ለሥላሴ ፅንስ አሳብ አለመኖር ማስረጃ ይሆነኛል ብለው ነው። ለመሆኑ የሥላሴ ፅንስ አሳብ መኖር የሚወሰነው መላው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ነው? ወይስ ማር. 12:29ን ብቻ በመንተራስ? በመሠረቱ ማር. 12:29 መለኮታዊ አንድነትን የሚያስተምር ሲሆን፣ ስለ አካላዊ ሦስትነት የሚናገርም ሆነ የሚቃወም አይደለም። የሥላሴ ፅንስ አሳብ ማለትም መለኮታዊ አንድነትና አካላዊ ሦስትነትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ከዚህ በታች እንመለከታለን።

ጌታ ኢየሱስ የጥምቀትን ትእዛዝ ሲሰጥ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ነው ያለው (ማቴ. 28:19-20)። ጌታ ኢየሱስ፣ «ዳሩ

ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» (ዮሐ. 15:26) ሲል የአንዱን አምላክ ሦስት አካላት በግልጥ ያመለክተናል::

ይህን የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስም የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን (2ቆሮ. 13:14) በማለት የቆሮንቶስ ሰዎችን፣ የአንዱ አምላክ ሦስት አካላት የሆኑትን ስማቸውን በመጠቀም ሲባርካቸው የምንመለከተው:: ስለዚህ የሥላሴ ትምህርት ፅንስ አሳብ መጽሐፈ ቅዱሳዊ መሆኑ ቁልጭ ያለ እውነት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል:: ነገር ግን፣ ይህን ፅንስ አሳብ ማለትም የአንድ አምላክ በሦስት አካል መገለጥ፣ በአንድ ስም መጥራት ወይም የአካላቱን የጋራ ስያሜ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተርቱሊያኖስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ሥላሴ የሚል ስያሜን ሲጋራ መጠሪያነት አበርክቷል:: ስያሜው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም፣ ነገር ግን ፅንስ አሳቡና ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ:: ስያሜው እራሱ እንኳ የመጽሐፍ ቅዱሱን አሳብ ሳያዛንፍ ያቀረበ ስለሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ማለት ይቻላል:: አንድ ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚባለው ቃል በቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰፈረ ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስን አሳብ ሳያፋልስ የያዘ፣ የሚያብራራም ሆነ የሚገልጥ ሆኖበመገኘቱ ጭምር ነው::

4. ቀመር ሁሴን፣ የተረዱት ወይም ሊረዱት የወደዱት አንድ እውነት አለ:: ይህም ኢየሱስ በራሳቸው እንደበት «የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና» ብለው አብ ከእርሳቸው (ኢየሱስ) እንደሚበልጥ መናገራቸውን ነው:: ነገር ግን፣ በእኔ እምነት ቀመር ሁሴን ያልተረዱት፣ ምናልባትም ምንጊዜም ሊረዱት የማይወዱት ሌላ እውነት አለ:: ይህም ኢየሱስ በራሳቸው እንደበት፣ «እኔና አብ አንድ ነን እኔን ያየ አብን አይቷል፣ አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ እንዳለሁ አታምኑምን...ወዘተ ማለታቸውን ለማመንና ለመቀበል አለመቻላቸው



ነው:: ኢየሱስን የምናምን ከሆነ ከተናገሩት ነገር ላይ አንዱን ጥለን አንዱን የምናነሣበት ምንም ዓይነት ተቀባይነት ያለው ምክንያት ሊኖረን አይችልምና:: ካሙኑና ከተቀበሉ ሁሉንም ማመንና መቀበል ያስፈልጋል፤ ካላመኑና ካልተቀበሉ ደግሞ ዝም ብሎ በራስ ሃይማኖት መቆም የተሻለ አማራጭ ይሆናል::

5. ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ከሄደ በኋላ አጽናኝ እንደሚመጣ ተናግሮአል:: ክርስቲያኖች፣ አጽናኙ «መንፈስ ቅዱስ» ነው ሲሉ ይናገራሉ:: በአንጻሩ ደግሞ ሙስሊሞች፣ «ነቢዩ መሃመድ» ናቸው ይላሉ:: ሙስሊም ጸሐፊያን አጽናኝ የሚለው ቃል ለመንፈስ ቅዱስ አለመሆኑን ሲያመለክቱ፣ «መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ባስተማሩበት ዘመንም ነበር (ማቴ. 12: 18፣28) ስለዚህም፣ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ገና ወደፊት የሚከሰት ትንቢት አልነበረም፤ በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት በእርግብ ተመስሎ ነው መንፈስ ቅዱስ የመጣው የሚል መከራከሪያ ነጥብ ያነሣሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት (ስለ አጽናኙ መምጣት) የሚናገረው የኢየሱስ ተከታዮች እርሱ ከሄደ በኋላ ብቻቸውን እንደማይሆኑ፣ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ኃይልን እንደሚያለብሳቸው፣ ከእነርሱ ጋር እንዲሁም በውስጣቸው ሆኖ የወንጌል ማደረስን ተልእኮ በብዙ መከራና ችግር ውስጥ ጸንተው ቆመው እንዲያከናውኑ ከማስቻል ጋር በተያያዘ ነው የተነገረው:: በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት በኢየሱስ ላይ በእርግብ መልክ ተመስሎ ከወረደበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ ከቶ አልተነገረም:: ኢየሱስ ባስተማረበት ዘመን አብ እንደ ነበረ ሁሉ እንደሁ መንፈስ ቅዱስ ነበር:: ይህ ታዲያ በምድር ላይ መኖሩን አያመለክትም፤ መንፈስ ቅዱስ አንድን መለኮታዊ ሥራ ለመሥራት በተለያዩ ዘመናት በእግዚአብሔር ነቢያት እንዲሁም ናዝራዊያን ላይ ይወርድ ነበር:: ያንን ሥራ ካከናወነ በኋላ ደግሞ ወደ መጣበት (ወደ ነበረበት) ይመለስ ነበር እንጂ በምድር ላይ አይኖርም ነበር:: ይህ ማለት ደግሞ በስፍራ ሁሉ አይገኝም ማለት አይደለም:: እርሱ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ

ጌታና አምላክ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፤ ነገር ግን፤ ከዚህ በሁሉ ስፍራ ከመገኘቱ ባሻገር ያለውን መገለጥም ሆነ መገኘቱን፤ በዚህም በቋሚነት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ሆኖ በእጃቸው የተለያዩ ድንቅና ተአምራት የሚሠራበትን ሁኔታ በተለይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንንና አጠቃላይ የወንጌል ተልእኮዋን የሚመራበትን ሁኔታ፤ እንዲሁም በልዩ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ማለትም በቅዱሳን ኅብረትም ሆነ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚገለጥ መሆኑን ያመለክታል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በእርሱ ደቀ መዛሙርት ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ስለሚኖረው አጽናኝ ነው የተናገረው፤ ደግሞም ይህ አጽናኝ ሰው እንዳልሆነ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር (የእውነት) መንፈስ እንደሆነ በግልጥ አስቀምጦታል:: «እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው:: ነገር ግን፤ ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ» (ዮሐ. 14: 16-17)::

ክርስቲያኖች አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ነው ሲሉ ጌታ ኢየሱስ ዓለም የማያየውና የማያውቀው ሲቀበለውም የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው ብሎ ባስተማረው ቃል ላይ ተመሥርተው ሲሆን፤ ሙስሊም ጸሐፊያኑ ደግሞ በራሳቸው ግምትና ይሁንታ ላይ በመመሥረት ለነቢያቸው ትክክለኛ በትንቢት የመጣ አገልጋይ መሆን ማስረጃ ለማግኘት፤ ምናልባትም የሚሰማ ካለ ለማሰማት ነው::

መቼም መካመድን ብዙዎች አይተዋቸዋል:: መንፈስ አልነበሩምና፤ በየትኛውም መልኩ ቢሆን ከእኛ ጋርና በውስጣችን ሊኖሩ አይችሉም፤ አምላክ አይደሉምና::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ተስፋ ከሰጣቸው በኋላ «እንሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤
እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ:: (ሉቃስ 24:48-49) ብሏቸው ነበር:: ይህንን እውነት የዘገበው ወንጌላዊ ሉቃስ



በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፤ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፤ በይሁዳም፤ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ:: » (የሐዋ. 1:8) ሲል ጉዳዩን በሚገባ ይገልጠዋል:: ደቀ መዛሙርቱም በኢየሩሳሌም በአንድ ላይ ተሰብስበው በጸሎት የተጉ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ይጠባበቁ ነበር (የሐዋ. 1:12-14)::

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ እንደ ተባለው በበዓለ ኀምሳ ቀን የተሰጣቸው ተስፋ ተፈጸመ:: «በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ:: ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው:: እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው :: በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር::» (የሐዋ. 2:1-4) .

ስለዚህ፤ ስለ አጽናኙ የተሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ሁሉ ወስደን ስንመለከት እርሱ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ፤ ደግሞም ትንቢቱ (ተስፋው) ብቻ ሳይሆን ፍጻሜውም እንደ ተገለጠና ይህ ሁሉ በአንድ ላይ እንደ ተጻፈና ተያያዥነት እንዳለው መገንዘብ ይኖርብናል እንጂ ከአንድ ክፍል ብቻ በመነሣት ቁንጽል አስተሳሰብን ማራመድ አይገባንም፤ ስል ይህን ጥያቄና መልስ በዚህ እደመድማለሁ::

6. መጽሐፍ ቅዱስ በእብዛኛው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አፈ-ታሪክ ስለመሆኑ የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1:1-4 መመልከት ይበቃል ተብሏል:: ሉቃስ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚናገረው የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶችና ሥራዎች እንዴት ከዓይን ምስክሮች እንደ ተቀበለና እንደሚያስተላልፈው ነው:: ሁለተኛ በሆነው የዚህ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ ማለትም (በሐዋርያት ሥራ 1:1-2) ላይ፤ «ቴዎፍሎስ ሆይ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ በረገበት ቀን ድረስ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለ

ጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ...» እያለ ይናገራልና::

ሉቃስ ከዓይን ምስክሮች ብዙ ነገሮችን ወስዶ በቅደም ተከተል አስፈሮአቸዋል:: ይህ አፈ-ታሪክ ሊባል አይችልም:: አፈ-ታሪክ ማለት ምንጩ ምን እንደሆነ የማይታወቅ፣ ምስክር የሌለው እንዲሁም ሳይጻፍ ለብዙ ዘመናት በአፍ ብቻ ሲነገር የቆየ ታሪክ ማለት ነው:: የኢየሱስ መኖር በእስራኤል ምድር፣ ማደጉም ሆነ ማገልገሉ እንዲሁም በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መሰቀሉ ታሪካዊ ሃቅ ሲሆን፣ ከሙታን መነሣቱ ሁሉ እንኳ ከሃይማኖት መጻሕፍት ባሻገር በታሪክ መጻሕፍት እንኳ የተዘገበ ሃቅ ነው:: የዓይን ምስክሮች በሕይወት ሳሉ ነው ወንጌላውያኑ ምስክርነቶቹን ተቀብለው የጻፉት:: ከወንጌላውያን መካከልም እንደ ዮሐንስና ማቴዎስ ያሉት ራሳቸው የዓይን ምስክር ነበሩ:: ስለዚህም፣ ያዩትን ነገር ነው የጻፉት:: ወንጌላት ከ60 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 85 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ተጽፈዋል:: ስለዚህ፣ አፈ-ታሪካዊ ባሕርይም ሆነ መልክ ከቶ የሌለባቸውና ጥራዝ ነጠቅ የሆነ ትችት የተሰነዘረ መሆኑን ለማስገንዘብ እወድዳለሁ::

7. በማቴ. 20:20 ላይ ኢየሱስ ሰውን ገነት ማስገባት አልችልም ብሎ አልተናገረም:: ዳሩ ግን ጥያቄው ለተፈጠረባቸው ሰው እንዲህ ያለ መሰላቸው:: የዘብዴዎስ ልጆች እናት በመንግሥተ ሰማያት ከልጆቹ አንዱን በቀኝ ሌላውን በግራ አስቀምጥልኝ ስትል የሥልጣን ጥያቄ ነው የጠየቀችው:: ጌታ ኢየሱስ በሥጋ በምድር ላይ በተመላለሰ ጊዜ ለእርሱ ካላቸው ቀረቤታ የተነሣ የተጠየቀ ጥያቄ መሆኑን በውል ስላጤነው፣ ጉዳዩ የመለኮት ፈቃድን የሚጠይቅ መሆኑን ለማመልከትና፣ አስተሳሰብዋን ከጥቅማ ጥቅምና ከምድራዊነት ለመመለስ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ይህ ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው ያላት:: አዎን ሰማያዊ የሆነ ሥልጣን በሰማያዊው አምላክ ፈቃድ የሚሰጥ እንጂ በምድራውያን ሰዎች ፍላጎት የሚሰጥ አለመሆኑ የጸና እውነት ነው:: በመንግሥቱ ስለሚሆን የሥልጣን አሰጣጥ ተናገረ እንጂ፣ እኔ መንግሥተ ሰማያት አላስገባም ብሎ አልተናገረም:: ይህ በመስለኛና በዘፈቀደ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጐም ማሰብም ሆነ ማጥላላት ሊወገድ የሚገባ ልምምድ ነው:: ዳሩ ግን፣ እርሱ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ስለ መሆኑ እኔ መንገድና እውነትና ሕይወት ነኝ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም:: (ዮሐ. 14:6) ሲል መናገሩ የሚታወስ ነው:: ደግሞም አብረውት ከተሰቀሉት መካከል አንዱ ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስገባኝ ብሎ በለመነው ጊዜ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ ብሎ እንደ መለሰለት በወንጌል ውስጥ እንመለከታለን:: (ሉቃስ 23:24-25)

8. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከአማኖች ጋር እንደሚሆን ተናግሮአል፤ በሌላ ጊዜና ስፍራ ደግሞ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም ማለቱ እንደሚጋጭ ብዙ ሃያሲያን ያስቡ ይሆናል:: ነገር ግን፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ በምድር ላይ ከእኛ ጋር በሥጋ ይኖራል ማለት አይደለም:: እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእኛ ጋር የሚኖረው በመንፈስ ነው::

እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም ሲል ደግሞ በመንፈስ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር አለመኖሩን አያመለክትም:: ነገር ግን፣ በሥጋ በምድር ላይ ከእኛ ጋር ሁልጊዜ አለመኖሩን ነው የሚያመለክተው:: ስለዚህ፣ በሁለቱ አባባሎች መካከል ቅራኔም ሆነ ግጭት የለም:: ጌታ ኢየሱስ ሁልጊዜ ከእ-ናንተ ጋር እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ እኖራለሁ እንዳለው በመንፈስ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው:: በመንፈስ ሁልጊዜ ከአማኞችና በእጃቸው ከሚሠራው የወንጌል ሥራ ጋር አለ:: እየኖረም ነው:: ነገር ግን፣ እንደ ተናገረው አሁን በአብ ቀኝ ስላለ በሥጋ ከእኛ ጋር የለም::

9. የበርናባስ ወንጌልን ከሌሎች ወንጌላት በብቸኝነት እውነትና የበለጠ ታማኝ ያደረገው መስፈርት ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱን አናገኝም:: ወደ አራቱ ወንጌላት በምንመለከትበት ጊዜ አንድን ወንጌል በተለያየ ገጽታው አቅርበውታል:: ለአንድ ወንጌል አራት ምስክሮች ሆነው እናገኛቸዋለን:: አንዱ ወንጌላዊ ከሌላው የሚለየው በሚያተኩርበትና አጽንኦት በሚሰጥበት

ጉዳይ እንጂ በመሠረታዊ ይዘት አይደለምና። ቤተ ክርስቲያን አራቱን ወንጌላት በቀኖናነት(Canon) እውነትነ ታቸው በመስፈርት በተረናጋገጠበት ሁኔታ ስትቀበል እውነተኛ የእግዚአብሔር የሥልጣን ቃል መሆናቸውን ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችን አስቀምጣ ነው። ይህም በመጻሕፍቱ ውስጥ የተቀመጡ እውነታዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ትምህርቶች መሆናቸውንና ከእርሱም በኋላ ሐዋርያት ያስተማሩዋቸው መሆናቸውን ማዕከል ያደረገ መስፈርት ነው። የማርቆስ ወንጌል በበርናባስ መሪነት የተጻፈ ነው ካልን ግን ስለምን የሚናገረውን ሁሉ እናምንም? አንቀበልም? ከቀሪዎቹ ወንጌላት ጋር ያለውን መሠረታዊ የሆነ የይዘት አንድነት ለምን አንቀበልም? የበርናባስ ወንጌል ተብሎ ከሚጠራውስ ጋር ያለውን ተቃርኖ ስለምን አንቀበልም? እንዴትስ የክርስቶስን አምላክነት የሚቃወመውን የበርናባስ ወንጌልን ትክክለኛ ነው ልንል እንችላለን? ስለዚህ፣ ይህን ሁሉ መመለስ የማይችል ጥያቄ የሚያስነሣ አስተሳሰብ ማራመድ፣ ሆነ ብሎ ወንጌላትን ለመቃወም የታለመ መሆኑን እንገነዘባለን።

10.ሀ.ወንጌላት መስቀሉን «ኢየሱስም» ሆነ «ስምዖን» እንደ ተሸከሙ ይናገራሉ። ይህ ግጭት ሊመስለን ይችላል፤ ነገር ግን፣ ስሕተት ፈላጊ አእምሮ ከሌለን በስተቀር ጉዳዩን በማይጋጭ መልኩ ለማየት ይቻላል። ኢየሱስ ብዙ መከራን ስለ ተቀበለ፣ ስለ ተደበደበና ስለ ተንገላታ የተወሰነ መንገድ መስቀሉን ተሸክሞ ከሄደ በኋላ ፍጹም በሚደክምበት ጊዜ፣ መስቀሉን ተሸክሞ መሄድ ከቶ የማይችልበት ሁኔታ በተፈጠረ ወቅት የሮማ ወታደሮች የቀሬና ሰው የሆነውን ስምዖንን መስቀሉን ተሸክሞ ጌታ ወደሚሰቀልበት ስፍራ እንዲያደርስ ያደረጉበትን ሁኔታ ነው ወንጌላት የሚያመለክቱት። ጸሐፊዎች ሁለቱንም ሆነ አንዱን ቢጽፉ ነገሩ እውነትና የተደረገ ስለሆነ የሚያጠያይቅ አይሆንም። ስለሆነም፣ ሦስቱ ወንጌላውያን የስምዖንን መስቀል መሸከም አተኩረው ሲመለቱ፣ አንዱ ማለትም ዮሐንስ ደግሞ የኢየሱስ መስቀል መሸከም ላይ ማተኮሩን ነው የምንመለከተው፤ ትልቁ ቁምነገር ግን ማንም ይሸከመው ማንም፣ ኢየሱስ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ መሞቱ ነው።



ለ. ወንጌላዊ ማርቆስ፣ ኢየሱስ የተሰቀለው በ3 ሰዓት እንደሆነ ሲናገር፣ ወንጌላዊ ዮሐንስ ደግሞ በ6 ሰዓት እንደሆነ ይናገራል። እነዚህ ሁለቱም የተለያዩ ሰዓቶች ድርጊቱ የተፈጸመባቸው ሰዓታት ናቸው ማለት አይቻልም። ነገር ግን፣ ሁለቱም በድርጊቱ (በኢየሱስ መስቀል፣ ለምን ዓላማ እንደ ተሰቀለ) ይስማማሉ። ትልቁና አንኳሩን ልንመለከተው የሚገባ ነገር ይህ ነው። ወንጌላዊ ሉቃስ መጻሕፍት የተጻፉበትን አንዱን መንገድ (ከጸሐፊያኑ የሚጠበቅና በቅዱሳት መጻሕፍት ሂደት ያበረከቱት ድርሻቸውን) ሲያመለክት፣ «በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን በእኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ...» የሚል ቃላትን ይጠቀማል። የጽሑፉ ሂደት በአንድ ወገን የተካሄደበት አሠራር ጠቅለል ባለ መልኩና በተለይ ለወንጌላት (ታሪካዊነትን ለተላበሱት) የዓይን ምስክሮች ምስክርነትን በመንተራስ እንዲሁም ቅደም ተከተልን ጠብቆ ለመጻፍ የተሞከረበት መሆኑን እንመለከታለን። እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር በመጀመሪያው ታሪኩ ነው የሚፈጸመው፤ ከዚያም ታሪኩ ለትውልዶች መተላለፍ እንደሚገባው ሲታመን ነው ከዓይን ምስክሮች ትውስታ ተወስዶ የሚዘጋጀው። በዚህ ሂደት ላይ በመጀመሪያ የዓይን ምስክሮች ክስተቱ የተፈጸመበትን ትክክለኛ ሰዓት በግምት ብቻ ነው ሊናገሩ የሚችሉት። ምክንያቱም፣ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት እንደ አሁኑ ዘመን በእያንዳንዱ ሰው እጅ ላይ ሰዓት አለመኖሩ ለሁላችንም ግልጥ ነውና። እዚህ ላይ አንዱ ሦስት ሌላው ስድስት ቢል ሊያስደንቀንና ጠጉር ስንጣቂ ይመስል ወይም ስሕተት ፈላጊ አእምሮ የያዝን ይመስል ብዙ ልንነጋገርበት አንችልም። ሌላው ወንጌላት ከተጻፉ በኋላ እስከ 16 ክፍለ ዘመን ድረስ የማተሚያ ቤት ስላልነበረ መጻሕፍት ይባዙ የነበሩት በእጅ እየተገለበጡ ነው። በእጅ ሲገለበጥ ደግሞ አንዳንድ ጥቃቅን ግድፈቶች (Scribal errors) ሊሠሩ መቻላቸው እሙን ነው። ይህ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ሳይሆን በብዙ መጻሕፍት ላይ የሚታይ የጋራ ችግር ነው። በአሁን ዘመን ታይፕ የሚዘላቸውና የኅትመት ማሽን እንኳ የሚያበላሻቸው ነገሮች እንዳሉ ማሰብ የተገባና ሒሲና ያለው ሰው የሚያደርገው ተግባር ነው። ነገር ግን፣ ይህም ሆኖ ጥቃቅኑ ግድፈቶች በመሠረታዊ

እውነቱና በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ላይ ያመጡት ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አለመኖሩ ግልጥ ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክቱ ደራሲ /አመንጪ/ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ከመለኮታዊ ገጽታው አንጻር ፍጹምና እንከን ያልተገኘበት መጽሐፍ መሆኑንም ልብ ማለት ይጠቅማል::

ሐ. በስቅላቱ ጊዜ ከወይን ጠጅ ጋር ከርቤም ሆነ ሐሞት ተደባልቆ ቢሰጠው ሁለቱም መራራ ነገሮች የመሆናቸው ምሥጢር የማይሻርም ሆነ ሊተባበል የማይችል ሃቅ ነው:: የዓይን ምስክሮችም ሆነ ጸሐፊያኑ ሁለት ነገሮች ተደባልቀው ሲሰጡ ነው መመልከትም ሆነ ማሰብ የሚችሉት:: ምክንያቱም፣ አደባላቂዎቹ እነርሱ አይደሉምና:: ነገር ግን፣ በባህላቸውና በወጋቸው ማለትም በዚያን ዘመን የነበሩ ሕዝቦች አንድን ሰው በስቅላት በሚገድሉ ጊዜ የሚጠቀሙበት ልማድ አለ:: ይህም የወይን ጠጅን ከከርቤም ሆነ ከሐሞት ጋር በመደባለቅ የመስጠት ልማድ ነው:: ስለዚህ፣ ድርጊቱን የተመለከተ አንዱ ሰው ወይን ጠጅ ከከርቤ ጋር ሊል ይችላል:: ሌላው ደግሞ ወይን ጠጅ ከሐሞት ጋር ሊል ይችላል:: ስለዚህ፣ ዋናው ነገር መራራ የሆነና በመጠኑም ቢሆን ሥቃዩን እንዲረሳ የሚያደርግ ነገር መሆኑ ስለሆነ፣ ጉዳዩ ስሕተት የመፈለግ እንጂ አደናጋሪም ሆነ የትርጉም ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ አይደለም እንደ ትልቅ ጉዳይና አጠያያቂ ነገር ሆኖ የቀረበው::

መ. አራቱም ወንጌላውያን ወደ ጌታ መቃብር ስለ ሄዱ ሰዎችም ሆነ ስለ አጠቃላይ ገጽታው ባላቸው የመረጃ መጠንና በተመቻቸው ሁኔታና የአጻጻፍ ስልት ተጠቅመው ሲጽፉ የግዴታ አንድ ዓይነት ነገር መናገር (መጻፍ) አይጠበቅባቸውም:: ትልቁና ዋናው ነገር ሴቶች ምን ያህል ግዘን እንደሚያጠብቁና ብዙ ትኩረት ከተቃዋሚ ወገኖች ሊገጥማቸው ስለማይችል በሦስተኛ ው ቀን አስከሬኑን ሽቶ የመቀባት ወጋቸውን ለመፈጸም እግረ መንገዳቸውንም ስለ ጌታቸውና ወዳጃቸው ለማልቀስ የመሄዳቸውን፣ ነገር ግን ባልጠበቁት መንገድ ራሳቸውን የትንሣኤው የመጀመሪያ ምስክሮች ሆነው ማግኘታቸውን ማመልከት ነው:: በዮሐንስ አዘጋገብ ማርያም ወደ መቃብሩ የሄደችው ሁለት ጊዜ ነው::



አንደኛ ብቻዋን፣ ሁለተኛ ለደቀ መዛሙርቱ ከነገረቻቸው በኋላ (እነርሱ በሩጫ ሄደው ተመልክተው ከተመለሱ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ) ማርያም መቃብሩ ጋር ሆና ታለቅስ ነበር:: በዚያን ጊዜ ነው ሁለት ነጫጭ የለበሱ ሰዎች (መላእክቶች) ስለምን ታለቅሻለሽ ብለው የጠየቁዋት ሳሉ እርሷም ጌታዬን ወስደውታል ብላ ከመለሰችላቸው በኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ራሱን ቆሞ ያየችውና ልታነጋግረው የቻለችው:: (20:9-17) ይህን መሰል ሰፋ ያለ ሚና ስለ ነበራት አስቀድማ ከሌሎች ሴቶች ጋር ሄዳ ቢሆን እንኳ የሐንስ ትኩረቱ በእርስዋ ላይ ስላረፈ ክስተቱን ከእርሷ ጋር ብቻ አገናኝቶ ሊጽፈው ይችላል:: ሌሎች ደግሞ ሁሉንም በአንድ ዓይን ብቻ በመመልከት የማንንም ድረሻ ባለማጉላት ክስተቱን በሁሉም ሴቶች ስም ሊጽፉት ችለዋል:: ስለዚህ፣ አጉልተን መመልከት ያለብን ዋናውን ሥዕል (The historical fact of the resurrection) ነው::

ሠ. ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ለአሥራ አንዱ ነው ወይስ ለአሥራ ሁለቱ የታየው ? የሚለው ጉዳይ በማቴ. 28:16 እና በ1ቆሮ. 15:4-5 ባለው ክፍል ላይ አንዱ አስራ አንድ ሌላው አስራ ሁለት ስለሚል፣ እንዴት ይታያል? ለሚለው ጥያቄ ያለን መልስ ይህን ይመስላል:: ማቴዎስ 28 ኢየሱስ ሲያርግ ሲል ያለውን ሁኔታ ነው የሚያመለክተን:: በዚህ ጊዜ ይሁዳ ስለ ሞተ አስራ አንድ ነበሩ:: ስለዚህም፣ አስራ አንዱ ማለት ነበረበት:: ከዚያ በኋላ (የሐዋ. ምዕራፍ 1) ላይ እንደምንመለከተው አስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በይሁዳ ፋንታ በጸሎትና በዕጣ ማቲያስን መተካታቸው ይታወቃል:: ሁለቱን ሰዎች ከብዙዎች የለዩበት መስፈርትም ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ ከእነርሱ ጋር የነበረና የትንሣኤውም ምስክር የሆነ የሚል ነበር:: ሐዋርያው ጳውሎስ ከሁሉ በኋላ የመጣና ጌታን በደማስቆ መንገድ ላይ ያገኘ ሰው ነው:: ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ትንሣኤ መኖር እውነትነትና ብዙ የትንሣኤው ምስክሮች እንዳሉ ሲዘረዝር አስራ ሁለቱ የሚል ቃል ተጠቅሞአል:: አንደኛ ማቲያስ ራሱ የትንሣኤ ምስክር ነው:: ሁለተኛ፣ ከአስራ አንዱ ጋር ተቁጥሮአል:: ይህ እውቅናም ያገኘ ነገር ነው:: ስለዚህ፣

አስራ አንድና አስራ ሁለት የሚለው እንደሚጋጭ ተደርጎ መታሰብም ሆነ መቈጠር የለበትም።

እስራኤልም ሆነ ኤፍሬም የበኵር ልጅ መሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀምጦአል። (ዘጸ. 4:22፣ ኤር. 31:9) እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል የበኵር ልጅ ነው ያለው ለግብፅ ንጉሥ ለፈርዖን ነው (ለግብፃውያንም ሁሉ ነው)። የእስራኤል በኵርነት ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በአጠቃላይ፣ ከግብፃውያን ጋር በተለይ ተወዳድሮ ነው የተገለጠው። እግዚአብሔር አምላክ ኤፍሬም በኵሬ ነው ያለው ከሌሎች አሕዛብ ጋር አወዳድሮት ሳይሆን ከእስራኤል ጋር አወዳድሮት ነው። ይህም፣ «ለእስራኤል አባት ነኝና ኤፍሬምም በኵሬ ነውና» (ኤር. 31:9) በሚል ቃል ተቀምጦአል። ሁሉም ልጅ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ሁሉም በኵር ሊሆን አይችልም፤ በኵር የተለየ ስፍራ የሚሰጠው ልጅን ማንነት የሚገልጥ ነው። ስለዚህ፣ የመረዳት ግጭት ካልተፈጠረብን በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስ የማይጋጭ መሆኑ ገሃዳዊ እውነት እንደሆነ በዚህ ማረጋገጥም ሆነ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ እንችላለን።

11. በመሠረቱ አብርሃም የአይሁድ እምነትም ሆነ የክርስትና እምነት አባት ነው። ለሁለቱ እምነቶች የእምነትን ፈለግ፣ «አብራምም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» እንደ ተባለ (ዘፍ. 15:6፣ ገላ 3:6) እንዲሁም ሳያዩ በእግዚአብሔር ቃል በመታመን እምነታቸውን ለመሠረቱ ሁሉ ማለትም የእምነቱን ፈለግ ለተከተሉ ሁሉ ምሳሌና ናሙና የሆነ ሰው መሆኑን አዲስ ኪዳን ያመለክተናል። ይህም፣ «እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ እወቁ» (ገላ. 3:6-7)፤ በሚል ቃል ተገልጧል። ጌታ ኢየሱስ ከመወለዱና በሥጋ ከመምጣቱ በፊት ማለትም በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ (ፊል. 2:6) ሊያየው እንደ ወደደ፣ እንዳየው፣ በዚህም እንደ ተደሰተና ሐሤት እንዳደረገ (ዮሐ. 8:56) መስክሮአል። ጌታ ኢየሱስ መጽሐፍት ሁሉ ስለ እርሱ እንደሚናገሩ (ዮሐ. 5:39) እርሱ መንገድ፣ እውነትም ሆነ ሕይወት



እንደሆነ አስተምሮአል። (ዮሐ. 14:6) ለዚህም ነው አብርሃም ሊያየው የወደደው። እርሱ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ከነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።» (ዕብ. 1:1-3) ሲል እንደ ተናገረለት የመገለጦች ሁሉ አውራና የመጨረሻው የእግዚአብሔር መገለጫ መንገድ (እግዚአብሔር እራሱ ሥጋ ለብሶ የመጣበት አማኑኤል፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሆነበት) ነው። አብርሃም ከእምነቱ ጽናት የተነሣ ይህን ጌታ ገና የመምጫው ጊዜ ሳይደርስ ለማየት አመነ፣ ለመነ፣ ከእምነቱም የተነሣ የለመነውን ተመለከተ።

ስለዚህ፣ እነዚህ ሁሉ ነገሮችና ማስረጃዎች አብርሃምን የአይሁድ እምነትና በክርስቶስ ማንነትና ህልውና ባርነት፣ ማለትም መንገድነት፣ እውነትነትና ሕይወትነት (ዮሐ. 14:6) እንዲሁም ትንሣኤነት (ዮሐ. 11:25) ላይ የተመሠረተው የክርስትና እምነት ጥንታዊ አባት እንጂ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተመሠረተ ማለትም በግምት አብርሃም ከሞተ ከ5000 ዓመት በኋላ የተመሠረተ እምነት ተከታይ ነው ብሎ ማሰብ አንድም እብደት፣ ሁለትም ጅልነት፣ ሦስትም እጅግ የተሳሳተ አስተሳሰብ፣ እምነትና ትምህርት ነው።

አይሁድ የተባሉት የይሁዳ ማለትም ያያዕቆብ አራተኛው ልጁ፣ የእርሱ ዝርያዎች ወይም ነገዶች ብቻ ናቸው ማለት መሠረታዊ የሆነ ስሕተትና ቅጥፈት ነው። አይሁድ (Jews) እና ይሁዳ (Judea) ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አይሁድ ማለት በጥቅሉ የእስራኤል ሕዝብ ማለት ሲሆን፣ የእስራኤል ሕዝብ በአጠቃላይ የሚጠራበት ተለዋጭ ስም ነው።

ለምሳሌ ያህል የአስቴርንና የመርዶክዮስን ታሪክ ከመጽሐፈ አስቴር ብንመለከት መርዶክዮስ ለአስቴር (ሀደሳ) አጎት እንደ ነበረና አባትና እናቷ የሞተባት

ሴት ስለ ነበረች እንደ አባት ያሳደጋት እርሱ እንደሆነ፣ መርዶክዮስም ከብንያም ነገድ እንደሆነ እንመለከታለን:: (አስ. 2:5-7) መርዶክዮስ ለሐማ መስገድ እንቢ ባለ ጊዜ ሐማ መርዶክዮስን ብቻ ሳይሆን ወገኖቹን ሁሉ ማለትም አይሁድን ሁሉ ለማጥፋት ማቀዱን መጽሐፉ በግልጥ ያስቀምጥልናል (አስ. 3:6):: ስለዚህ፣ ብንያማዊ የሆነም ሰው አይሁዳዊ እንደ ተባለ መገንዘብ ይኖርብናል እንጂ በማናውቀው ነገር እየገባን ልንዘባርቅ እንዲሁም የክርስትና እምነትና ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጣጣል ልንቋምጥም ሆነ ልንጣደፍ አይገባም:: ይህ ማንነታችንን (ሐሰተኝነታችንን) አደባባይ የሚያወጣ ከመሆኑም በላይ ትዝብት ላይ የሚጥለን ነው:: እንደዚህ ዓይነት ዘባራቂ እንዳንሆን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሰጠን «ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ» (2ጢሞ. 2:23) የሚለውን ማሳሰበያ ልብ ማለት ይጠቅማል::

ቁርዓን ብዙ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ የወሰደና ብቻውን መቆም የማይችል (dependent) ምንጭ ስለሆነ፣ ይህን በቅጡ ያልተያዘና የተሳሳተ ትርጒማቸውን ከቁርዓን ነው የወሰድነው ማለት ከንቱ የሆነ የዋህነት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ ከሆነ ደግሞ አንድም ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደ እውነት አድርገው መጥቀስ የማይችሉ መሆኑን፣ መጽሐፋቸውም የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ህልውና ላይ ስለሆነ የተሳሳተ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል:: በዚህ አጋጣሚ የመጀመሪያው ታሪካዊ መጽሐፍና እምነት ከእርሱ እጅግ በጣም ዘግይቶ የመጣውን እምነትም ሆነ መጽሐፍን ለመመርመር የሚጠቅም መመዘኛ ይሆናል እንጂ ሁለተኛውና እጅግ ዘግይቶ የመጣው የመጀመሪያው መጽሐፍንም ሆነ በውስጡ ያሉ ትምህርቶችን የሚገመግምበት መንገድ እንደ ሌለ፣ መመዘኛም ሆነ መስፈርት ሊሆን ከቶ የማይችል መሆኑን ሊያውቁ ይገባል እላለሁ::

2. የሥላሴ አስተምህሮ ጌታ እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን፣ ይህ አንዱ እግዚአብሔር አምላክ በሦስት አካል የሚኖርና ራሱን በሦስት አካል የገለጠ ነው፤ የሚል ነው:: ይህ አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋትም ሆነ በጥልቀት ተገልጦ የሚገኝ



ሲሆን ለአብነት ያህል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጒዳዩ ላይ የሰጠውን ትምህርት መመልከት በቂ ይመስለኛል::

«እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል እርሱም... የእውነት መንፈስ ነው» (ዮሐ. 14:15-17) እዚህ ላይ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እንመለከታለን::

«ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል::» (ዮሐ. 15:26-27)::
እዚህም ላይ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እናገኛለን::

«እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው::» (ማቴ. 28:19-20) ይህም አንዱ አምላክ በሦስት አካል እንደሚኖርም ሆነ እንደሚገለጥ ያመለክተናል::

የሥላሴ ፅንሰ አሳብ ይህ ነው፤ ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመጠን በላይ ነው ያለው:: ነገር ግን፣ ትምህርቱ ሳይሆን ሥላሴ የሚለው ሦስትነትን በአንድነት ለማመልከት ክርስቲያኖች ሁሉ (አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ) የሚጠቀሙበት ስም (ስያሜ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም:: ትምህርቱን ትምህርት የሚያደርገው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአንዱ መለኮት በሦስት አካል መገለጥ እንጂ ሦስትነቱን በአንድነቱ ለመጥራት (በአንድ ላይ ለመጥራት) የሚያስችለው ስያሜ አይደለም:: ይህ ሊታወቅ ይገባል:: ይህን ስያሜ ያበረከተው ሰው ደግሞ ተትናቴዎስ አይደለም:: ነገር ግን ተርቱሊያኖስ የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ነው:: በመሠረቱ አትናቴዎስ ጳጳስ እንጂ ዲያቆንም አይደለም:: «ከሰነፎችና ካልተማሩ ሰዎች ምርመራ ራቅ» (2ኛጢሞ. 2:23) ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ የሚናገረው ይህን መሰሉን ቅዥት ከመቃዠት እንድንጠበቅ ነው::

13. አብርሃም ለመሥዋዕት ያቀረበው እስማኤልን ከሆነ የአብርሃምን እምነት የተከተለው ይስሃቅ ሳይሆን እስማኤል ነው የሚሆነው:: ስለዚህም፣ የአብርሃም እምነት (በአንድ አምላክ የማመንና ከጣዖታት ሁሉ የመራቅን) ልምምድ እስማኤላውያን ወይም ዓረቡ ዓለም ገና ከጥንት ጀምሮ ባስወገዱት ነበር:: ከአብርሃም ዘመን ጀምሮም የነበረ የእስማኤላውያን የሆነና በመካከላቸው የተገለጠ መገለጥና ቅዱስ የሆነ የእምነት መጽሐፍ በኖረና ለትውልድ ሁሉ በተላለፈ ነበር:: የእስልምና እምነት መሥራችና ነቢይ የሆኑት መሃመድም ከእስማኤላውያን ዘንድ ያገኙትን መገለጥ ባጸደቁና ባብራሩ ነበር፣ በአንፃሩ ደግሞ የመጽሐፉ ሰዎች እያሉ ብቻኛ የመገለጥና የመጽሐፍ (የእውነት) ባለቤቶች አይሁዳውያንና ክርስቲያኖች እንደሆኑ፣ በቁርኣን ውስጥ በተለያየ መልኩ ባልመሰከሩም ነበር:: መሃመድ ለዓረቡ ዓለም እስልምናን ባስተማሩ ጊዜ የክርስትናም ሆነ የአይሁድ መጻሕፍት (ብለይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን) ተጽፈው ካበቁ በብዙ መቶና በሺህ ዓመታት የሚቆጠር ጊዜን አሳልፈው ነበር:: ስለዚህ፣ ባይሆን ከብዙ ሺህና መቶ ዓመታት በኋላ የመጣው እምነት ከፊተኛው መጽሐፍ የተወሰኑ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለቀም ለቀም አደረገና የማይፈልጋቸውን ነገሮች ስሕተት ናቸው ወይም ተበርዟል በማለት የይስሐቅን በረከት ለእስማኤል በመስጠት የራሱን እምነት ላዕላይነት ለማመልከት ቁርጦ ቀጥል ሆነ ቢባል ነው የሚያስኬደው::

መቼም አይሁዶች እስማኤል ተረግሞአል ካሉ ለዚህ መልስ ሊሰጡበት የሚገባ ይመስለኛል:: እስማኤል እንደ ተባረከ ይህም ፍሬያማ እንደሚሆንና እንደሚበዛ፣ አስራ ሁለት አለቆችንም እንደሚወልድና ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆን (በዘፍ. 17:20) የተገለጠው እውነት ነው:: ይህ ግን በምድራዊ ኑሮና ሀብት የተባረከ መሆኑን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከእርሱ ጋር ቆሞ ሰማያዊ የሆነ በረከትን መባረኩን አያመለክትም:: ምክንያቱም፣ ይህ በረከት በይስሐቅ በኩል የሚያልፍ የነበረ በመሆኑ ነው:: ለማስተያየትም ይረዳ ዘንድ ዘፍ. 17:20 ስለ እስማኤልም ሆነ ስለ ይስሐቅ የሚነገረውን ክፍለን



ሳይሆን በሙሉ ወስደን እንመልከት:: (ከ18-21 ያለውን ሙሉ አሳብ እንመልከት::)

«እግዚአብሔርም አብርሃምን እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው:: እግዚአብሔርም አለ፡- በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፡- ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፣ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ፣ ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፣ እነሆ ባርኬዋለሁ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ፣ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፣ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ:: ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ::»

ምንም እንኳ በሕጋዊ መንገድ ባይወለድም፣ የአብርሃም ልጅ ስለሆነ ብቻ እስማኤል በምድራዊ ሀብት ተባርኳል:: ነገር ግን፣ ይስሐቅ የተስፋ ልጅ ስለሆነ በሕጋዊ መንገድ ከጋብቻም የተወለደ በመሆኑ፣ በሰው ዕቅድና ፍላጎት ያልመጣና እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ተጠብቆ የተገኘ ስለሆነ በምድራዊ ሀብትም ሆነ በመንፈሳዊ ሀብት (የተስፋውና የቃል ኪዳኑ ትውልድ) በመሆን ተባርኮአል::

14. የእውነት መንፈስ የሚለውን ቃል እንዴት አድርገን ነው እርሱ መሃመድ ነው የምንለው? መሃመድ ሰው እንጂ አምላክ አይደሉምና:: ይህ ትልቅ ስሕተት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነት መንፈስ ብቻ ብሎ ነገሩን ድፍንፍን አላደረገውም:: መንፈስ በዓይን የማይታይ የማይዳሰስም ሆነ የማይጨበጥ ባሕርይ ያለው መሆኑንም «...እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፣ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ::» (ዮሐ. 14:17) ሲል አመልክቷል:: በመቀጠልም፣ አጽናኙ ወይም የእውነት መንፈስ ማን እንደሆነ እንዲህ ሲል በስም አስቀምጦታል፣ «...አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ

ያሳስባችኋል።» (ዮሐ. 14:26) መሃመድ ከእኛ ጋር እንዲሁም በውስጣችን ሊኖሩ አይችሉም፣ ሰው ስለሆኑ ሞተዋልና። በሕይወትም ቢኖሩ በውስጣችን ሊኖሩ አይችሉም። «የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርም፣ እርሱ ያከብረኛል ስለኔ ካለኝ ወስዶ ይናግራችኋል፣ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ» (ዮሐ. 16:13-15) የሚለው ቃል አንድ መሠረታዊ እውነትን ያመለክተናል። ይህም ስተግባር የሚሆን ማነስን (Functional Subordination) ያመለክተናል። ላኪውም ሆነ ተላኪው በማንነትና በሥልጣን እኩል ይሆኑና፣ ነገር ግን አንድን ተልእኮ ከሥላሴ አካላት በስተቀር ሌላ ሰው ወይም ፍጡር የሆነ አካል ሊያከናውነው የማይችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣ አንዱ ላኪ ሌላው ተላኪ ይሆናል። ስለዚህም፣ ተላኪው ሁልጊዜ ላኪውን ያከብራል፣ የላኪውን አሳብ እንደሚያገለግል ሆኖ ይቀርባል፤ በአንድ በኩል የላኪውን አሳብ ማገልገሉ እውነት ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የእራሱን አሳብ ማገልገሉ እውነት ነው፣ በሌላ በኩል የራሱን አሳብ ማገልገሉን አለመግለጡ ለተደራሲያኑ ሥነ ልቡና ጠቃሚ ነው። ላኪውን ለማሳየት መምጣቱ የሰዎችን አሳብ ወደ ሰማይ (በሰማይ ወዳለው አንድ አምላክ) ለመሰብሰብ ይጠቅማልና። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እንደ ተላኪ፣ የአብን አሳብ እንደሚያገለግል አድርጎ ተናግሮአል። «...አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ።» (ዮሐ. 8:28)፤ ልክ በዚሁ ተመሳሳይ መንገድ ነው እርሱ ሲሄድ መንፈስ ቅዱስን ሲልከው ኢየሱስ አብን እንዳከበረ ሁሉ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን (ወልድን) የሚያከብርና ወልድን የሚያሳይ መሆኑን የሚገልጥልን።

15. የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ከኢየሱስ ዕርገት በኋላ የተጻፈ መጽሐፍ ቢሆንም፣ መጽሐፉን በመልአኩ በኩል ያጻፈው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጥ ነው። «ኢየሱስ በመልአኩ ልኮ ለባርያው ለዮሐንስ አመለከተ።» (ራእይ 1:1) ይላልና። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለም ሆነ በሰማይ ፈራጅ መሆኑ ግልጥ ነው። «...ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል» (ኢሳ.



11:3) የተባለለትም ለዚህ ነው። በጽድቅ ይፈርዳል ማለት በትክክል ይፈርዳል ማለት ነው። ሰው ሁሉ ሙሉ በሙሉ በጽድቅ ሊፈርድ አይችልም፣ ሁሉን አዋቂ አይደለምና፤ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ በጽድቅ (በትክክል) መፍረድ የእርሱና የእርሱ ብቻ ተግባር መሆኑ ተነግሮለታል። ራእይ 19:11ን ብቻ ቆንጽለን ሳንወስድ ከቁጥር 11-16 እንኳ ጀምረን ብናነብብ ይህ በአምባ ፈረስ ላይ የተቀመጠውና የታመነው በልዩ ልዩ መግለጫዎች ማንነቱ ተገልጦ እንመለከታለን፡- ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፣ በራሱም ላይ ብዙ ዘውዶች አሉ...ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል...በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው። ከእነዚህ መግለጫዎች መካከል አንዱም ቢሆን መሃመድን አይገልጣቸውም። ነገር ግን፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል ይገልጠዋል። ሌላው ቢቀር ቁርዓን እንኳ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ይመሰክራልና። እነዚህና መሰል መግለጫዎች በራእይ 1:12-16 ተቀምጠውልናልና ልናመሳክር እንችላለን።[63] እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር ስንዝሬ አሳቤን ላጠቃልል እወድዳለሁ፤ ይህም ኢየሱስ በመጀመሪያ ሲመጣ የመጣበት ዓላማ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን፣ ወደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው፣ ምክንያቱም፣ ከመጀመሪያው ምጽአት ጀምሮ እስከ ዳግመኛ ምጽአቱ ድረስ ያለው ጊዜ የምሕረት ጊዜ ነውና። ስለዚህ፣ በዚህ ምጽአቱ በሰዎች ላይ ዘላለማዊ የሆነ ፍርድን አላስተላለፈም። ነገር ግን፣ የምሕረት ጊዜው በሚያልቅና የፍርድ ጊዜ በሚመጣበት ወቅት ማለትም በዳግመኛ ምጽዓቱ በዓለም ሁሉ ላይ ዘላለማዊ ፍርድን ይሰጣል። ይህን ፈራጅነቱን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ቁርዓንም ይመሰክራል።[64]

16. ለእስራኤላውያን ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ተብሎላቸዋል።

---

[63] አቡ ሱመያ፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997፣ ገጽ40-44።

[64] ዶ/ር ሐሰን ኢም በዐጌል፣ *ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ ሦስተኛ እትም 1992፣ ገጽ 5-8።

መሃመድ የዓረቦች ወንድም እንጂ እንዴት አድርገው ነው የእስራኤላውያን ዘር ሊሆኑ የቻሉት? ትንቢቱ በእስራኤላውያን መካከል በዘር ሐረጋቸው ውስጥ ያለ ነቢይ እንደሚመጣላቸው ነው የሚያመለክተን:: ስለሆነም፣ መሃመድ በዚህ ቃል መስፈርትነት ምክንያት ብቻ እንኳ ከጉዳዩ ውጭ ሲሆኑ የተገባ ነው::

እንደ አንተ ያለ ነቢይ የሚለው ቃል በጥቅሉ ሁለት መሠረታውያን ነገሮችን ያመለክተናል:: አንደኛው፣ እግዚአብሔርን ከተራው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከታላላቅ ነቢያትም ሁሉ እንኳ በላይ በተሻለ መንገድ የቀረበና የሚያውቅ ማለት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በእጁ ታላላቅ ተአምራት የሚገለጡበት ማለት ነው:: በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች የሙሴና የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ተመሳሳይነት አላቸው:: በተጨማሪም፣ ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት እንዳወጣ ሁሉ እንዲሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ሁሉ ከዓለም ከኃጢአትና ከሰይጣን ግዛት ነፃ መውጣቱ በእጅጉ ያመሳስላቸዋል::

17. በትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት የምናገኘው ጽዮን የሚለው ቃል ትንቢት አይደለም፤ ስም ነው:: ስለሆነም፣ በዚያ ስም የተጠራ ወገንን ብቻ የሚያመለክት እንጂ ወደፊት የሚመጣ ትውልድን ወይም ሃይማኖትን እንደሚያመለክት ተደርጎ መታየት የለበትም:: በተመሳሳይ መልኩ ስለ ጽዮንም የሚነገር ነገር ሁሉ በዚያን ወቅት ጽዮን በሚባለው ስም የሚጠራውን ወገንና ይህ ወገን ወደፊት የሚገጥመውን ነገር የሚያሳይ ነው:: ለምሳሌ «ለአበራ» ከተባለ በዚያን ወቅት አበራ የሚባለውን ሰው የሚያመለክት እንጂ፣ ወደፊት የሚወለደውን ጀማልን የሚያመለክት አይደለም:: ለመሆኑ ጽዮን ማን ናት? «ጽዮን ሆይ ተነሺ ተነሺ ኃይልሽን ልበሺ፣ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽምና...» (ኢሳ. 52:1-2) ጽዮንና ኢየሩሳሌም ከተሞች ሲሆኑ የሚወክሉት የእስራኤልን ሕዝብ ነው:: በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ያልተገረዘ ሕዝቦች ረግጠዋታልና፣ የምርኮ ዘመን እንዳበቃ (በጥቂት ጊዜ ውስጥ እንደሚያበቃ) የሚያሳይ ትንቢታዊ ቃል ነው:: ትንቢቱም



በዚሁ መልኩ ተፈጽሞአል:: እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ ተመልሰው ካልተገረዙ ሕዝቦች ጸድተው ብዙ ዓመታትንና ትውልዶችን ያስቆጠሩበት ሁኔታ ነው የነበረው::

«ለጽዮን ታዳጊ ይመጣል በያዕቆብም ዘንድ ከኃጢአት ለሚርቁ ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳ. 59:20) ያዕቆብ የእስራኤላውያን አባት ነው:: በያዕቆብም ዘንድ ማለት በእስራኤልም ዘንድ ማለት ነው:: ያዕቆብ እስራኤል ተብሎ ተጠርቷል:: ደግሞም በዚህ ክፍል ላይ እንደምንመለከተው እስራኤላውያን ያዕቆብ ተብለው ተጠርተዋል:: ስለሆነም፣ ኢሳ. 40ም ሆነ 60 ከሌሎች የኢሳይያስ ትንቢት ተነጥለው የማይቆሙና የማይታዩ መሆናቸውን ልናስምርበት ይገባል:: ከ60:1-3 ያለውን «ብርሃንሽ መጥቷልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ አብሪ:: እነሆ ጨለማ ምድርን፣ ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ይሸፍናል ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል፣ ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል:: አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ መውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ::» የሚለውን ክፍል ስንመለከት ከክርስትና እምነት መምጣት በጣም፣ እንዲሁም ከእስልምና እምነት መምጣት እጅግ በጣም ቀደም ባሉት ዓመታት መላው ዓለም በጣዖታት አምልኮ ጨለማ በተተበተበበት ወቅት የአንድ አምላክ አምልኮን ብቻዋን ታራምድ የነበረች እንዲሁም የእራሱን ፈቃድና አሳብ ለሕዝቡ መመሪያ አድርጎ በመጽሐፍ ያጻፈ እግዚአብሔር በመካከሉ ያለ ሕዝብ እስራኤል መሆኑ እምነቱም የአይሁድ እምነት እንደ ነበረ፣ ደግሞ ብዙዎች ወደዚህ ታላቅ ብርሃን ይመጡ እንደ ነበር፣ በዘርና በመወለድ ሳይሆን ግርዘትን ማዕከልም ሆነ ምልክት ባደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ እየገቡ ወደ ይሁዲነት ይለወጡ እንደ ነበር፣ ለዚህም ብዙዎች ከዓለም ዙሪያ ይመጡ እንደ ነበረ የአደባባይ ምሥጢር ነው:: ይህ ፍቺ የሚሻ ሕልም አይደለም ወይም ጠቢብ የሚጠይቅ ምሥጢር አይደለም:: ስለሆነም፣ በኢሳ. 40 እና 60 ብቻ ሳይሆን በመላው የኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ትንቢቶች ለእስራኤላውያን የተሰጡም ሆነ ለእነርሱና በእነርሱ መካከል የተፈጸሙ መሆናቸውን መቀበል ይኖርብናል::

18. «የባሕሩ በረከት ወደ አንቺ ስለሚመለስ የአሕዛብም ብልጥግና ወደ አንቺ ስለሚመለስ የሚለው ቃል ለጽዮን አይደለም» የሚለውን አቋም፣ «ምክንያቱም ከጽዮን የሚገኘው የጦር መሣሪያ ነው» በሚል ደካማ ማስረጃ ምናልባትም የያዙትን አቋም የሚያፈርስ ማስረጃ ማቅረብ ከራስ ጋር እንደ መጋጨትም ሆነ የሚሉትን ነገር በውል እንዳለማወቅ የሚታይ ነገር ነው:: በመሠረቱ የባሕሩ በረከት ከአንቺ ይመጣል አይልም፤ ነገር ግን ወደ አንቺ ይመጣል ነው የሚለው:: ስለዚህም፣ የሀብት ክምችት አለሽ (በይዞታነት የያዝሽው) አይልም፤ ነገር ግን ካለበት ስፍራ ይመጣልሻል ነው የሚለው:: ስለዚህም፣ የሀብት ክምችት ስሌለበት አገር (ወገንና ሕዝብ) የተነገረ ትንቢት መሆኑ ግልጥ ነው:: ማንበብ ለሚችል (በቅጡ መረዳት ስለመደ) የአሕዛብ ብልጥግና ወደ አንቺ ይመጣል የሚለው ቃል ግልጥ ነው:: ከሕዝቦች ሁሉ ወደ አንቺ፣ ካሳመኑ ወገኖች ሁሉ ወደ አንቺ ይመጣል፤ ለምን ቢባል ብርሃንሽ ስለ ወጣ የእግዚአብሔር ክብር በአንቺ ላይ ስለሚታይ....የሚል ምላሽን ነው የምናገኘው:: ስለዚህ፣ ትንቢቱ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ሕዝብና ርስት የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ፣ ጽዮንን የሚያመለክት ነው:: በመጨረሻም፣ ትንቢቱ ውስጥ ሰዎች ከሀብት ክምችት የተነሣ ወደ አንቺ ይመጣሉም ሆነ ሥራ አጦች ወደ አንቺ ይመጣሉ የሚል አሳብ ከቶ የሌለ መሆኑን በማስገንዘብ የዚህን ጥያቄ ምላሽ በዚህ እእደመድማለሁ::

19. በመሠረቱ መከፋፈል በራሱ የችግር ብቻ ሳይሆን የጤናማነት ምልክት የሚሆንበት አጋጣሚም እንዳለ መረዳት ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌም፣ አንድ ወገን የተሳሳተ ትርጕምን ቢከተል ሌላው ወገን ለመመሳሰል ወይም ደግሞ ሰው ሠራሽ ለሆነ አንድነት ሲባል ብቻ እውነተኛውን ትርጕም መልቀቅ የለበትም:: ስለዚህም፣ ልዩነቱን በመጠበቁ ለእውነት መቆሙን ያረጋግጣል:: በሌላ በኩል ደግሞ አስተዳደራዊ በሆኑ ጕዳዮች ላይ ሰዎች የተለያዩ አቋሞችንና አስተሳሰቦችን ቢይዙና ቢያራምዱ ያመቸኛል ያሉትን የአስተዳደር ስልትና ዘዴ በመምረጣቸው ሳቢያ ከሌላው መለየታቸው እንደ ኃጢአትም ሆነ ውድቀት ሲቈጠር ብሎም ለዚህ ሁሉ



ነገር የእምነታቸው መሳሳት ምክንያት እንደሆነ መታሰብ የለበትም:: የተለያየ አስተሳሰብን እንዲሁም አተረጓጕምን ለማራመድ መቻል በበኵ ጐኑ ከተወሰደ የነፃነት ምልክት ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ በግድና በኃይል እንዲሁም በጭቆና እመን አለመባልን ያመለክታል:: ሌላው በክርስትና ውስጥ ያለ መከፋፈል የእስልምና እምነት ከመከሰቱ በፊት በማርስዮናይትስ፣ በአርዮሳውያን እንዲሁም የኤሴቲሲዝምና የኖስቲሲዝም ፍልስፍና በተከተሉ ወገኖች ምክንያት አስቀድሞም የነበረ ጕዳይ ነው:: እንዴት ሆኖ ለመሃመድ ወደፊት የሚመጣ ትንቢት ሆኖ እንደታያቸው ሊገባኝ አይችልም:: ተገልጦ የታየን ነገር ለመተንበይና በዚህም ነቢይ ለመባል ካልቋመጡ በቀር ለእኔ ሌላ ምክንያት አይታየኝም:: ደግሞስ የክርስትናው መለያየት ቀርቶ ራሳቸው የመሠረቱት ሃይማኖት የእስልምናው መከፋፈል ስለምን ሊታያቸው አልቻለም? ሺአ ሙስሊም፣ ሱና ሙስሊም፣ ወግ አጥባቂያን ሙስሊም ብሎም አክራሪ ሙስሊም (Radicals) እንዲሁም ከተለምዶአዊ ሃይማኖቶች (Traditional Religions) ጋር በተቀራኘ መልኩ እስልምናን የሚያራምዱ ልዩ ልዩ ወገኖች (Falk Islam) መኖራቸውን ስለምን በትንቢታቸው ሳይዳስሱት ቀሩ? መቼም የራስን ቤት አዳፍኖ ስለ ሌሎች ማውራት ተገቢ አለመሆኑ አሌ የማይባል ሃቅ ነው:: ስለዚህ ከመከፋፈል በመነሣት ክርስትናን መኮነን ተገቢ ያልሆነና የብልጣብልጦች አኪያሄድ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል::

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ወንጌላት እንደምናገኘው የሥላሴን አስተምህሮ ደግሞ ደጋግሞ አስተምሮታል:: እነዚህ ትምህርቶቹን ከእርሱ ወስደው ለማስተማር በእርሱ ሥልጣን የተሰጣቸው ሐዋርያት (Authoritative Apostles) በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተምረዋቸዋል:: ትምህርቶቻቸውም በመላው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በግልጥ ሰፍረው ይገኛሉ:: ስለዚህ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውንም ሆነ ያላስተማረውን ነገር ወስደው የሚያስተምሩ ወገኖች ትክክለኛውንም ሆነ የተሳሳተውን ትምህርታቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜ ትምህርታቸውን ሁሉ አሜን ብለን መቀበል አንችልም፤ በአንጻሩ ደግሞ ቀና መስሎ

የታዩንን መሠሰድ ደስ ያልተሰኘንበትንም ማናናቅ አይጠበቅብንም:: ማንም ያስተምር ማንም ከእኛ የሚጠበቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ተጽፈው እንደምናገኘው ያስተማራቸውን ትምህርቶች እንዲሁም ሦስት ዓመት ተኩል አሠልጥኖ የሾማቸውንና ያሰማራቸውን የሐዋርያትን ትምህርት በመውሰድ የዘመኑን ማለትም ከሐዋርያት ዘመን በኋላ (ከ95- 100ዓ.ም በኋላ) ያሉትን አስተማሪዎች ሁሉ ትምህርት መመዘን ነው:: የእኛ ተግባር ተመዝነው ያለፉትን ትምህርቶች መቀበል የወደቁትን መጣል ነው:: የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የዛሬዎቹን የይህዋ ምስክሮች ነን ባዮችን ትምህርት መስል የሆነ እንደ አርዮሳውያን ያሉ የስሕተት ትምህርቶች በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያቱ ትምህርቶች እየመዘነች ወድቀውም በማግኘቷ እየጣለች (በመጣልም ላይ ያለች) መሆኑ ከቶ ሲዘነጋ አይገባም:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን እውነት በመመዘኛ ነትና በመስፈርትነት የያዘ ስለሆነ የትኛውንም ትምህርት በዚህ እውነትና መስፈርትነት መመዘን እንደምንችል ሳሳስብ እወድዳለሁ::

21. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛመርቱ ስለ እርሱ በተለይም ስለ ሞቱ የተነገሩ ትንቢቶችን ጠቅሰል አድርጎ ነግሮአቸዋል:: ይህም «...ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል...» (ሉቃስ 24:46) በሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተቀምጦልናል:: በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ ሰንበት ካለፈ በኋላ በሳምንቱ በፊተኛው ቀን ወደ መቃብሩ ሴቶች በመጡ ጊዜ ጌታን በመቃብር እንዳላገኙት፣ ነገር ግን መነሣቱን ከቅዱሳን መላእክት እንደ ተረዱ እንዲሁም መቅደላዊት ማርያም ጌታን እንዳየችው ወንጌላት በስፋትና በጥልቀት ይመሰክራሉ:: ይህን የትንሣኤውን እውነት ልዩ ልዩ ምስክርነቶች ሙስሊም ጸሐፊያን ሲመለከቱ ግራ የሚጋቡበትም ሆነ ጥያቄ የሚያነሡበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህም ኢየሱስ አርብ ሞቶ እሑድ ከተነሣ ከአርብ ዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ በሃያ አራት ሰዓት ስሌት ሲቈጠር እንዴት 72 ሰዓት ወይም ሦስት ቀን ሙሉና ሦስት ሌሊት ሊሞላ ቻለ? ካልሞላስ እንዴት



«በሦስተኛው ቀን ይነሣል» የሚለው ቃል ትክክል ይሆናል? የሚል ነው::

ስለ ሥነ አፈታት በተጻፈው ምዕራፍ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ጠባይ ክስተታዊ እንደሆነ በእንጻሩም ዘመናዊ መረዳትንና ሳይንስን ማዕከል ያላደረገ እንደሆነ በስፋት ተገልጧል:: ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋን ከሳይንሳዊ ሳይሆን ከክስተታዊ አነጋገር መረዳት አንጻር መመልከት ይኖርብናል:: በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ስንመለከተው ሦስት ቀን ማለት አንዱ ቀን የሞተበትና የተቀበረበት፣ በመሀል ያለው ቀን ሁለተኛ ቀን ሲሆን የተነሣበት ቀን ደግሞ ሦስተኛ ቀን በመባል እንደ ተወሰደና አተረጓጐሙም በዚህ መልኩ የሚታይ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል:: ይህ ቀናትን በሳይንሳዊ ሳይሆን በክስተታዊና ተለምዶአዊ አነጋገር የመጥራትም ሆነ የማሰብ ልምምድ ዛሬም ቢሆን የሚሠራበት መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ለምሳሌ ያህል ዛሬ የተቀበረ ሰው ነገ አልፎ ከነገ ወዲያ ማለዳ ሰልስቱ ነው (ሦስተኛው ቀን) ነው ተብሎ ይጠራል:: ስለዚህ፣ የስንብቻ ልቅሶ፣ ቤተ ዘመድ ዘንድ በመሄድ ይደረሳል:: ይህ እንግዲህ 72 ሰዓት ተቈጥሮ አይደለም:: ነገር ግን፣ የተቀበረበትን ቀን (ሰዓቱ ምንም ይሁን) አንድ ብሎ በመቁጠር፣ በመሀል ያለውን ቀን ሁለት በማለት፣ ሦስተኛውን ቀን (ገና ሳይዋገድ ማለዳ ጠዋቱን) ሦስት ብሎ በመቍጠር የሚሆን ወይም የሚደረግ ማኅበራዊ ልምምድ ነው::

ተጨማሪ ሌላ ምሳሌ ለመስጠት ያህል ሐኪሞች እንኳ የታሸገን ቍስል በሦስተኛው ቀን ይፈታል ሲሉ 72 ሰዓት ሲሞላው በሚል ፍቺ ሳይሆን፣ ዛሬ ቍስሉ ታክሞ የታሸገበት፣ ነገ ውሎ የሚያድርበት ከዚያም በሚቀጥለው ቀን የሚፈታበት በሚለው ፍቺ (ትርጓሜ) የሚናገሩበትና ይህን አዘውትረው የሚጠቀሙበት መሆኑ ግልጥ ነው::

## Bibliography

Althus Paul. *The Theology of Martin Luther*, Tran. Robert C. Schultz, Philadelphia, 1966, p. 74.

Brown David. *The Christian Scriptures: Christian and Islam 2*, London:Sheldon Press, 1968. P. 11-19.

*Christian Doctrine.Vol. 1*, Addis Ababa: Mekane Yesus Seminary, 1960, P. 148-150.

Fee Gordon D. and Sturt Daglas. *How to read the Bible for all its Worth: A Guide to understand the Bible.* Michigan: Zondervan, 1981. P. 14.

Fee Gordon D. *New Testament Exegesis: Revised Edition,* Westminister: John Knox,1993, p. 114.

Fernanedo Ajith. *Jesus Driven Ministry,* Leicester: IVP, 2002. p.154.

Little Paul E. *Know What You Beleve,* USA:Victor Books, 1970, p. 8.

Wrigh J. Christ. *Lecture note:* Evangelical Theological College, , Mar. 2003.

*Zondervan hand book to the Bible*, P. 22, 51

ዋቢ መጻሕፍት



ዶ/ር ማገህ ሐማድ አልጀሃይኒ፣ *ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ*፣ አዲስ አበባ፣ ሁዳ ፐሬስ፣ 1994 ገጽ 11።

አህመድ ሁሴን ዲዳት፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሃመድ የተናገረው ቃል* (ተርጓሚ ዘካሪያ አባትነህ ወርቅነህ)፣ ገጽ 45።

ዑመር አርሲ፣ *ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ፡-* ሁለተኛ እትም አዲስ አበባ፣ 1996፣ ገጽ 9-60።

ቀመር ሁሴን፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር በሙስሊም መነጽር*፣ ገጽ 7።

ሙሐመድ አጧዑሪም፣ *ኢየሱስ የኢስላም ነቢይ* (ትርጉም ኢድሪስ ሙሐመድ)፣ አዲስ አበባ፡ ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ 1997፣ ገጽ 40-74።

አቡ ሱመያ፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997፣ ገጽ40-44።

ዶ/ር ሐሰን ኢም በዐጊል፣ *ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት*፣ አዲስ አበባ፡- ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚ፣ ሦስተኛ እትም 1992፣ ገጽ 5-8።

ዳንኤል ተሾመ፣ *ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቁ የሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችና የትርጉም ዘዴዎች* Hermeneutics I፣ አዲስ አበባ፣ 1998። ገጽ 18-19።

Charles, C. Ryire *የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ትምህርት ጥናት*፣ተርጓሚ ሲሳይ ደሳለኝ፣ አዲስ አበባ ላብሲሊ ብሩክ ፊውንዲሽን፣1987። ገፅ 41።

ዮሐንስ ሳንድቬድ፣ *መሰከሩለት፡- የበሉይቢዳን መግቢያ ጥናት*፣ መካነ ኢየሱስ የምስራች ድምፅ፡- ሰማያታ ፐሬስ፣ 1990፣ ገጽ 3።

ዶ/ር ማንህ ሐማድ አልጆሃይኒ፣ ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ አዲስ አበባ፣ ሁዳ ፕሬስ፣ 1994 ገጽ. 11.

ሳዲቅ መሀመድ አህመድ፣ ላለመደናገር ማመሳከር፣ 1998፣ ገጽ 32-33።

አንዋር መሐመድ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ይጣረሳልን፣ አዲስ አበባ፡ ጌጃ ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ 1997፣ 7-11።

አህመድ ዲዳት፣ ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን፣ ነጋሺ አሳታሚ፣ 1988፣ ገጽ 4-17።



## ነቢዩ መሐመድ ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ስለ አይሁድ ወይም ክርስቲያኖች ያላቸውን በጎ ወይም አዎንታዊ አስተሳሰብ በተመለከተ ከቁርዓን ለአብነት ያህል የተወሰዱ ጥቂት ምስክርነቶች

«ወደ እናንተ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፤ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ እርግጥ መጥቶልሃል፣ ከተጠራጣሪዎች አትሁን።»

ሱረቱ 29:46

«የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች በእርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፤ ከነሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፤ በሉም፦በዚያ ወደኛ በወረደው፣ ወደናንተም በወረደው አመንን። አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፤ እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን።»

ሱረቱ 29:46

«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርዓን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኤልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያው ሙሳና ዒሣ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱም በአንድ መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለእርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።»

ሱረቱ 2:136

<<ለነዚያም ወደ አንተ በተወረደውና ከአንተ በፊትም ለተወረደው የሚያምኑ በመጨረሻይቱ (ዓለም) እነርሱ የሚያረጋግጡ ለኾኑት (መሪ) ነው።»

ሱረቱ 2:4

<<የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬን፣ አስታውሱ፤ በቃል ኪዳኔም ሙሉ፤ በቃል ኪዳናችሁ እሞላለሁና፤ እኔንም ብቻ ፍሩ።»

ሱረቱ 2:40

<<የእስራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ መሆኔን አስታውሱ።»

ሱረቱ 2:47